አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋክልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በደብረብርሃን እና በወሎ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ትምህርት ክፍሎች የበሳል ድርሰትና የሥነ-ልሳን ትምህርቶችን (Courses) የሚያስተምሩ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ

በ

ለይላ እሸቱ

የካቲት 2003 ዓ.ም

# በደብረብርሃን እና በወሎ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ትምህርት ክፍሎች የበሳል ድርሰትና የሥነ-ልሳን ትምህርቶችን (Courses) የሚያስተምሩ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋክልቲ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር


ለተግባራዊ ሥነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.
ኤ.ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ


ለይላ እሸቱ


የካቲት 2003 ዓ.ም

# ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ያለምንም መሰልቸት፣ ትሕትና በተሞላበት መንፈስ የጽሑፌን ረቂቅ በማንበብ፣በማረምና የተለያዩ ማስተካከያዎችን በመስጠት እገዛቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ለጌታቸው እንዳለማው (ረዳት ፕሮፌሰር) ልባዊ መስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በትምህርት ላይ እያለሁ የተለያዩ ድጋፎችን ያደረጋችሁልኝ ባለቤቴ ሰይድ መሀመድ እና እናቴ አረጋሽ ሰብስቤ ውለታችሁን ልገልፀው ባልችልም እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

ይህን የትምህርት እድል የሰጠኝና ደመወዜን እየከፈለ ላስተማረኝ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ እና የጥናቱን ወጪ ለሸፈነልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም የሐሳብና የቁሳቁስ (የማቴሪያል) እገዛ ላደረጉልኝ ጓደኞቼ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

በደብረብርሃን እና ወሎ ዩኒቨርሲቲ ጥናቱ ያተኮረባቸው መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም የአስተዳደር አካላት በቀና መንገድ አስፈላጊ መረጃዎችን በመስጠት ስለተባበራችሁኝ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

በመጨረሻም ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ በመጻፍና በማረም ያለመሰልቸት እገዛ ላደረጉልኝ ለወ/ሮ መሰረት መንገሻ እና ለወ/ሪት ስናፍቅሽ ሙሉጌታ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ........ i
ማውጫ ........ ii
የሠንጠረዥ ማውጫ ........ vii
አጠቃሎ ........ viii

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አላማ ........ 4
1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 4
1.4 የጥናቱ ወሰን ........ 5
1.5 የቃላትና የሐረጋት ፍቺ ........ 6
1.6 የምሕፃረ ቃላት ፍቺ ........ 6

ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

2.1 የተከታታይ ምዘና ምንነት ........ 7
2.2 የተከታታይ ምዘና ዓላማ ........ 8
2.3 የተከታታይ ምዘና ባህርያት ........ 9
2.4 የተከታታይ ምዘና መርሆች ........ 11
2.5 የተከታታይ ምዘና ጠቀሜታ ........ 12
2.5.1 ተከታታይ ምዘና ለመምህራን የሚሰጠው ጥቅም ........ 12
2.5.2 ተከታታይ ምዘና ለተማሪዎች የሚሰጠው ጥቅም ........ 13
2.6 በተከታታይ ምዘና እና በተለምዷዊው ምዘና መካከል ያሉ ልዩነቶች ........ 14
2.7 መምህራን ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ለማድረግ ሊከተሏቸው የሚገቡ ነጥቦች ........ 15
2.8 በተከታታይ ምዘና ሂደት የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ........ 17
2.9 የተከታታይ ምዘና ስልቶች /Tools or Techniques of Continuous Assessment) ........ 18
2.10 ተከታታይ ምዘና እና የቋንቋ ትምህርት ........ 25

2.11 በተከታታይ ምዘና ሂደት የነጥብ /ማርክ/ መስጫ ዘዴዎች ........................ 27
2.12 በተከታታይ ምዘና ሂደት የውጤት አተረጓጎም ........................ 30
2.13 ተከታታይ ምዘና ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮች ........ 31
2.14 የቀደምት ሥራዎች ቅኝት ........................ 33

ምዕራፍ ሦስት

የጥናቱ ዘዴ

3.1 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች ........................ 36
3.2 የናሙና አመራረጥ ........................ 36
3.2.1 የዩኒቨርሲቲዎች አመራረጥ ........................ 36
3.2.2 የመምህራን አመራረጥ ........................ 37
3.2.3 የተማሪዎች አመራረጥ........................ 38
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ........................ 39
3.3.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ ........................ 39
3.3.2 የሠነድ ፍተሻ ........................ 40
3.3.3 ቃለ መጠይቅ ........................ 40
3.3.4 የፅሁፍ መጠይቅ ........................ 40
3.4 የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተል........................ 41
3.5 የመረጃ አተናተን ስልት ........................ 41

ምዕራፍ አራት

የመረጃ ትንተና

4.1 መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸውን ግንዛቤ በሚመለከት ከቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................ 42
4.1.1 የተከታታይ ምዘና ምንነትን በተመለከተ የመምህራን ግንዛቤ .......... 42
4.1.2 የተከታታይ ምዘና አስፈላጊነት እና ጠቀሜታን በተመለከተ የመምህራን ግንዛቤ ........................ 43
4.2 የተከታታይ ምዘና እቅድ እና የኮርስ ቢጋር ዝግጅትን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................ 45
4.2.1 የመምህራን ተከታታይ ምዘና እቅድ እና የኮርስ ቢጋር ዝግጅትን በተመለከተ ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ ........................ 45
4.2.2 የተከታታይ ምዘና እቅድ እና የኮርስ ቢጋር ዝግጅት በተመለከተ የመምህራን ምላሽ ........................ 46

4.2.3 የመምህራን የኮርስ ቢጋር ዝግጅትን በተመለከተ ከፅሁፍ መጠይቅ የተማሪዎች ምላሽ ........ 47

4.3 የተከታታይ ምዘና ስልቶችን አጠቃቀም በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 48

4.3.1 የመምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶችን አጠቃቀም በተመለከተ ከክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ........ 48

4.3.2 የመምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶች አጠቃቀም በተመለከተ ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ........ 51

4.3.3 የተከታታይ ምዘና ስልቶች አጠቃቀምን በተመለከተ የመምህራን ምላሽ ........ 54

4.3.4 የመምህራንን የተከታታይ ምዘና ስልቶችን አጠቃቀም በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ ........ 54

4.4 በተከታታይ ምዘና ተግባራት ላይ ተማሪዎችን ማሳተፍ በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 60

4.5 በተከታታይ ምዘና ሂደት የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 63

4.5.1 የመምህራን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ ከክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ........ 63

4.5.2 የመምህራንን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ........ 65

4.5.3 የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ የመምህራን ምላሽ ........ 66

4.5.4 የመምህራንን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ ........ 67

4.6 በተከታታይ ምዘና ሂደት የመመዘኛ መስፈርት ዝግጅት እና የነጥብ /የማርክ/ አሰጣጥን በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 68

4.6.1 የመመዘኛ መስፈርት ዝግጅት እና የነጥብ አሰጣጥን በተመለከተ የመምህራን ምላሽ ........ 68

4.6.2 የመምህራን የመመዘኛ መስፈርት ዝግጅት እና የነጥብ አሰጣጥን በተመለከተ ከፅሁፍ መጠይቅ የተማሪዎች ምላሽ ........ 70

4.7 በተከታታይ ምዘና ሂደት የውጤት አተረጓጎምን በተመለከተ የመምህራን ምላሽ ........ 71

4.8 በተከታታይ ምዘና ሂደት ከተማሪዎች የሚገኙ መረጃዎችን ወይም ውጤቶችን መሰረት በማድረግ የሚደረጉ ድጋፎችን በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..... 73
4.8.1 የተማሪዎች ውጤቶችን መሰረት ያደረጉ ድጋፎችን በተመለከተ የመምህራን ምላሽ ..... 73
4.8.2 መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚያደርጉትን ድጋፍ በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ ..... 74
4.9 የተከታታይ ምዘና ሰነዶች አያያዝ እና አጠቃቀምን በተመለከተ የመምህራን ምላሽ እና ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..... 75
4.10 ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..... 78
4.10.1 ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በተመለከተ የመምህራን ምላሽ ..... 78
4.10.2 መምህራን ተከታታይ ምዘና ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ የሚስተዋሉ ችግሮችን በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ ..... 80

ምዕራፍ አምስት
ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦች
5.1 ማጠቃለያ ..... 83
5.2 የመፍትሔ ሐሳቦች ..... 85
ዋቢ. ጽሑፎች ..... 90

አባሪዎች
አባሪ አንድ፡ የመምህራን ቃለ መጠይቅ ..... 94
አባሪ ሁለት፡ የመምህራን ቃለ መጠይቅ መልስ ..... 96
አባሪ ሦስት፡ የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ..... 110
አባሪ አራት፡ የክፍል ውስጥ ምልከታ ማረጋገጫ ዝርዝር ..... 114
አባሪ አምስት፡ የሰነድ ፍተሻ ማረጋገጫ ዝርዝር ..... 115
አባሪ ስድስት፡ በሁለቱም ዩኒቨርሲቲዎች የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ለስምምነት ስኬል ጥያቄዎች በተናጠል የሰጡት ምላሽ ..... 116
አባሪ ሠባት፡ በሁለቱም ዩኒቨርሲቲዎች የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ስለተከታታይ ምዘና ስልቶች በተናጠል የሰጡት ምላሽ ..... 117

አባሪ ስምንት፡ የደብረብረሃን ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህራን ኮርስ ቢጋር ናሙና ........................................................................ 118
አባሪ ዘጠኝ ፡ የወሎ ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህራን ኮርስ ቢጋር ናሙና ........ 122
አባሪ አስር፡ የደብረብረሃን ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህራን የውጤት ማጠራቀሚያ ቅፅ ናሙና ........................................................................ 124
አባሪ አስራአንድ፡ ከደብረብረሃን ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህራን የተወሰደ የተማሪዎች የግል ሥራ ናሙና ........................................................................ 126
አባሪ አስራሁለት ፡ ከደብረብረሃን ዩኒቨርሲቲ የተወሰደ የተከታታይ ምዘና አተገባበር ደንብ ........................................................................ 130
አባሪ አስራሦስት ፡ ከወሎ ዩኒቨርሲቲ የተወሰደ የተከታታይ ምዘና አተገባበር ደንብ........................................................................ 133

# የሠንጠረዥ ማውጫ

**ገጽ**


ሠንጠረዥ፡ 1. በሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑትን መምህራን አጠቃላይ መረጃ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ....................37

ሠንጠረዥ፡ 2. የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎችን አጠቃላይ መረጃ የሚያሳይ ሠንጠረዥ....................39

ሠንጠረዥ፡ 3. የተከታታይ ምዘና ጥቅምን በተመለከተ ከፅሁፍ መጠይቅ የተማሪዎችን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ....................45

ሠንጠረዥ፡ 4. የመምህራን የኮርስ ቢጋር ዝግጅትን በሚመለከት የተማሪዎችን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ....................47

ሠንጠረዥ፡ 5. የመምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶችን አጠቃቀም በተመለከተ ከምልከታ የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሠንጠረዥ....................49

ሠንጠረዥ፡ 6. የመምህራን የምዘና ስልቶችን መጠቀም በተመለከተ ተማሪዎች ሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ....................55

ሠንጠረዥ፡7. የመምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶች የአጠቃቀም ደረጃን በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ....................57

ሠንጠረዥ፡ 8. የመምህራን ለምዘና ተግባራት ማብራሪያ መስጠትን በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ....................59

ሠንጠረዥ፡ 9. የመምህራን የምዘና ተግባራት ላይ ተማሪዎችን ማሳተፍ በተመለከተ የተማሪዎችን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ....................61

ሠንጠረዥ፡10. የመምህራን ምጋቤ ምላሽ መስጠትን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘውን መረጃ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ....................63

ሠንጠረዥ፡11 የመምህራንን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ የተማሪዎችን ምላሽ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ....................67

ሠንጠረዥ፡12. የመምህራን የመመዘኛ መስፈርት ዝግጅት እና የነጥብ አሰጣጥን በተመለከተ የተማሪዎችን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ....................70

ሠንጠረዥ፡13. መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚያደርጉትን ድጋፍ በተመለከተ ተማሪ_ዎች የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ....................74

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደብረብርሃን እና በወሎ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ትምህርት ክፍሎች የበሳል ድርሰትና የሥነ-ልሳን ትምህርቶችን የሚያስተምሩ መምህራንን የተከታታይ ምዘና አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ከተተኳሪ ዩኒቨርሲቲዎች ሁለት የበሳል ድርሰትና ሁለት የሥነ ልሳን በድምሩ አራት መምህራንና አርባ ስምንት የሁለተኛና የሦስተኛ ዓመት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ጥናቱ ገላጭ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን ምልከታ፣ ሰነድ ፍተሻ፣ ቃለ መጠይቅ እና የጽሑፍ መጠይቅ መረጃ ለመሰብሰብ በአገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም በአሐዛዊና በዓይነታዊ ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡ የጥናቱ ውጤትም ተተኳሪ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ምንነት ፣ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ጥሩ ግንዛቤ ያላቸው፣ ነገር ግን የተከታታይ ምዘና እቅድ የማያዘጋጁና እቅዱንም በኮርስ ቢጋሮች አማካኝነት ለተማሪዎች የማያሳውቁ፣ በተከታታይ ምዘና ስልቶች አጠቃቀማቸው በተወሰኑ ስልቶች ላይ ብቻ የሚያተኩሩ፣ ምጋቤ ምላሽ ሲሰጡ ትክክለኛውን መልስ እና ድክመትን በመናገር ላይ ብቻ የሚያተኩሩ፣ የመመዘኛ መስፈርቶችን ለተማሪዎች የማያሳውቁ፣ የተማሪዎችን ውጤት በመስፈርት ላይ ተመስርቶ (በክራይቴሪያን ሪፈረንስድ) ዘዴ በመተርጎም ለተማሪዎች ድጋፍ በመስጠት በኩል የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህራን የተሻሉ፣ በተከታታይ ምዘና ስነዶች አያያዝ በኩል ድክመት ያለባቸው እና የተከታታይ ምዘናን ለመተግበር የተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ የሥራ ጫና እና የቁሳቁስ (የማቴሪያል) እጥረት ችግሮች ያሉባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህንንም ግኝት መሠረት በማድረግ፣ ለወደፊቱ የጥናቱ ተተኳሪ ዩኒቨርሲቲዎችና መምህራን ለተከታታይ ምዘና አተገባበር ትኩረት እንዲሰጡ አስተያየት በመስጠት ጥናቱ ተጠቃሏል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

### መግቢያ

ምዘና ተማሪዎች ምን ዐወቁ? ምን ተረዱና ምን መሥራት ይችላሉ? የሚሉትን ነጥቦች የምናውቅበት መንገድ ነው፡፡ በተጨማሪም ምዘና ከተማሪዎች የተለያዩ መረጃዎችን ለመሰበስብ፣ ችሎታቸውን ለመለካትና ውሳኔ ለመስጠት እንዲሁም የመማር-ማስተማሩ ሂደት መሳካትና አለመሳካቱን ለመፈተሽ ወይም ለማረጋገጥ ያስችላል (Agrawal፣1994፣363)፡፡

ተማሪዎች በትምህርታቸው ብቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥና አጠቃላይ ሁኔታዎችን ለመፈተሽ ተገቢና አስተማማኝ ምዘና ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ከዚህ በፊት ያገለግል የነበረው የምዘና ስልት/ተለምዷዊው ምዘና/ በአንድ ሴሚስተር ውስጥ አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ ብቻ የሚሰጥ በመሆኑ አመርቂ ውጤት አያስገኝም (ታጠቁ እና ሌሎች :1996፣4)፡፡ ከዚህ ጋር በተያየዘ Shepard (2000፣4) ወቅትን ጠብቆ የሚሰጡ የወሰነ-ትምህረት አጋማሽና ማጠቃለያ ፈተናዎች የተማሪውን የመማር ችሎታና መሻሻል ፣የመርሐ-ትምህርቱን ብቃት እንዲሁም የማስተማሩን ሂደት ውጤታማነት በተመለከተ ወቅታዊና ከትምህርቱ ዓላማ አንፃር አስተማማኝና በቂ መረጃ ሊሰጥ እንደማይችል ይገልፃሉ፡፡

እነዚህ የተጠቀሱት ድክመቶች በተለምዷዊው ምዘና ላይ መስተዋላቸው ደግሞ ሌሎች የምዘና ስልቶች ብቅ እንዲሉ ምክንያት ሆኗል (Ur፣1996)፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ተከታታይ ምዘና ነው፡፡

እንደ Puhl (1997፣3) ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች ከክፍልም ሆነ ከክፍል ውጭ ያገኙትን ዕውቀት፣ክህሎት፣ልምድ፣ ወዘተ. በአግባቡ ስለመገንዘባቸው ለማወቅ በተከታታይ የሚካሄድ የምዘና ስልት ነው፡፡ Farrat (1980፣24) እና Curzon (1990፣135) ደግሞ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን የትምህርት ብቃት ፣መሻሻል ለመገምገም የሚያስችል እንደየክፍል ደረጃው የመማር ማስተማሩ ሂደት አካል ሆኖ ዕለት በዕለት የሚተገበር የምዘና አይነት ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ዕውቀትና ችሎታ ድክመትና ጥንካሬ ፍላጎትና የእለት ተእለት መሻሻል በተከታታይ የሚመዝን በመሆኑ ስለተማሪዎችና መምህራን መረጃ የመስጠት አቅሙ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም አስፈላጊነቱ እና ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በድሩ (1994፣2) ትምህርት ለሀገር እድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ ተማሪዎች የቀሰሙት እውቀትና ክህሎት፣የማስተማሪያ መሳሪያዎችና ዘዴዎች በየጊዜው እየተገመገሙ ተገቢውን የመከላከልና የእርምት እርምጃ መውሰድን ይጠይቃል፡፡ ለዚህ ተግባር በቂ መረጃ የሚገኘው ደግሞ በተከታታይ ከሚካሄድ ምዘና ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

ተከታታይ ምዘና ለቋንቋ ትምህርት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው (Puhl፡1997፣3 እና Heaton 1990፣124)፡፡ ቋንቋን የማስተማር ዓላማ ግቡን ሊመታ የሚችለው የተለያዩ የምዘና ስልቶች በየጊዜው ተግባር ላይ ሲውሉ ነው፡፡ ምክንያቱም በየምዕራፉ የሚሰጡ ፈተናዎች ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ ላይ ያለውን ደካማና ጠንካራ ጎን አያሳዩም ( Hughers፡1989፣1)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና ዘዴዎችን ተጠቅመው ተማሪዎችን በሚመዝኑበት ጊዜ ከሚያገኙት መረጃ በመነሳት ስለተማሪዎቻቸው የቋንቋ ችሎታ፣ስለቋንቋ ትምህርቱ ሁኔታ ተገቢነት ያለው ውሳኔ ለመስጠት ይችላሉ (Shaaban ፡2001፣17 እና Puhl ፡ 1997፣3)፡፡

የቋንቋ ትምህርት አላማዎች በተፈለገው መጠንና ጊዜ ግባቸውን እንዲመቱና የመማር ማስተማሩ ሂደት በጥራትና ሚዛኑን በጠበቀ ሂደት እንዲጓዝ ከተፈለገ ተከታታይ ምዘናን በየክፍል ደረጃውና በየትምህርት አይነቱ ማከናወን የግድ ይሆናል (ታጠቁ እና ሌሎች ፡1996 ፣4)፡፡

በአሁኑ ጊዜ የሀገራችን አዲሱ የትምህርት ሥልጠና ፖሊሲ ከፍተኛ ትኩረት ከሰጠባቸው ጉዳዩች አንዱና ዋነኛው ተከታታይ ምዘና ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በየክፍሉና በየደረጃው የሚሰጠውን ትምህርትና ሥልጠና በሚገባ ያጠናቀቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በአጠቃላይ በቀለምና በተግባራዊ ትምህርት ተከታታይ ምዘና መኖር እንዳለበት የትምህርት ሥልጠና ፖሊሲው (1986፣10) ያስረዳል፡፡

በተጨማሪም ትምህርት ሚኒስቴር (1999፣16) ከመምህራን ልማት መርሐ-ግብር ዓላማዎች ውስጥ አንዱ የተከታታይ ምዘናና ግምገማን ስራ ለመተርጎም ብቃት ያላቸውን መምህራን ማፍራት እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ለትምህርት ጥራት መሻሻል መምህራን ሊያከናውኗቸው ከሚገቡ ውጤታማ ስራዎች መካከል ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት በቂ እውቅና ክህሎት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ወቅታዊና ተከታታይ ምዘና ማድረግ አንዱ መሆኑን ጨምሮ ገልጿል፡፡

ይህንንም ተከትሎ የመምህራን የሙያ ብቃት ማሻሻያ ከፍተኛ ዲፕሎማ መርሀ-ግብር /HDP/ በሀገራችን ውስጥ ባሉ የመንግስት ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከትኩረት ነጥቦቹም አንዱ ተከታታይ ምዘና ነው፡፡ በዚህም መሰረት መምህራን ተከታታይ ምዘናን እንዲተገብሩት ይደረጋል፡፡

የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያትም የጥናቱ አቅራቢ ስነ-ትምህርት (Pedagogy CTP 601) የተሰኘውን ኮርስ በምትወስድበት ጊዜ "የተከታታይ ምዘና አተገባበር በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ናሙናነት" በሚል ዕርስ አጭር የኮርስ ማሟያ ጥናት በቡድን የመስራት እድል ገጥሟት በነበረበት ወቅት በጥናቱ ውጤትና ከጓደኞቿ ጋር ባደረገችው ውይይት በመስል ተቋማት ላይ መሰል ችግር እንዳለ መስመቷና መገመቷ፣ አጥኚዋ ማየት እስከቻለችው ድረስ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በአማርኛ ትምህርት ክፍል የበሳል ድርሰትና የስነ-ልሳን ትምህርቶችን (Courses) የሚያስተምሩ መምህራን ተከታታይ ምዘናን በአግባቡ እየተገበሩ መሆንና አለመሆናቸውን የሚዳስስ ጥናት አለማግኘቷ እና በአንደኛ ደረጃና በኮሌጅ በሚያስተምሩ አማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከታታይ ምዘና አተገባበር ላይ የተሰሩ ጥናታዊ ጽሁፎችን ባየችበት ጊዜ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ያሉ መምህራንስ ተከታታይ ምዘናን እንዴት ይተገብሩታል? የሚል ጥያቄ ስለተፈጠረባት እና ለጥያቄው መልስ ለማግኘት መሻቷ ነው፡፡

ስለዚህ የጥናቱ አቅራቢ ከላይ በተዘረዘሩት አነሳሽ ምክንያቶች መሰረት በተጠቀሱት ዩኒቨርሲቲዎች በአማርኛ ትምህርት ክፍል የበሳል ድርሰትና የሥነ-ልሳን ትምህርቶችን (Courses) የሚያስተምሩ መምህራንን የተከታታይ ምዘና አተገባበር መፈተሽ አስፈላጊ ነው ብላ ታምናለች፡፡

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደብረብርሃን እና በወሎ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ትምህርት ክፍሎች የበሳል ድርሰትና የስነ-ልሳን ትምህርቶችን (Courses) የሚያስተምሩ መምህራንን የተከታታይ ምዘና አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ ይህ ዓላማ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል፤

ሀ. በደብረብርሃን እና በወሎ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ትምህርት ክፍል የበሳል ድርሰትና የስነ-ልሳን ትምህርቶችን የሚያስተምሩ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ምንነት፣ ባህሪ እና ጠቀሜታ ያላቸውን እውቀት እና አመለካከት መፈተሽ ፡፡

ለ. በተጠቀሱት ዩኒቨርሲቲዎች ከላይ የተገለፁትን ትምህርቶች በአማርኛ ትምህርት ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን የሚጠቀሙባቸውን የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ወይም ስልቶች መመርመር፡፡

ሐ. በተጠቀሱት ዩኒቨርሲቲዎች ከላይ የተገለፁትን ትምህርቶች በአማርኛ ትምህርት ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት የምጋቤ ምላሽ እና የነጥብ /የማርክ/ አሰጣጥ እንዲሁም የውጤት አተረጓጎም ሁኔታን መመርመር፡፡

መ. በተጠቀሱት ዩኒቨርሲቲዎች የተገለፁትን ትምህርቶች የሚያስተምሩ መምህራን የተከታታይ ምዘና ሰነድ አያያዝን መፈተሽ፡፡

ሠ. በተጠቀሱት ዩኒቨርሲቲዎች የተገለፁትን ትምህርቶች የሚያስተምሩ መምህራን ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ለማድረግ የሚገድቧቸውን ሁኔታዎች መለየት፡፡

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

በትምህርት ዙሪያ የሚሠራ ማንኛውም ጥናት ለመማር ማስተማሩ ሂደት ወይም ለትምህርት ጥራት መሻሻል የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፤

ሀ. ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸውን የደብረብርሃንና የወሎ ዩኒቨርሲቲ የበሳል ድርሰትና የሠነ-ልሳን ትምህርቶች መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ሁኔታ ምን እንደሚመስል ስለሚጠቁም መምህራን ያለባቸውን ክፍተት በመሙላት ተከታታይ ምዘናን በተሻለ ሁኔታ እንዲተገብሩት ያነሳሳል፡፡

ለ. መምህራን ተከታታይ ምዘናን በመጠቀም እንዴት አድርገው ተማሪዎቻቸውን መመዘን እና በታላሚው የትምህርት አይነት /Courses/ ብቁ ማድረግ እንደሚችሉ አቅጣጫ ይጠቁማል፡፡

ሐ. ለተከታታይ ምዘና በትክክል መተግበር ሀላፊነቱን ለሚወስዱ አካላት በጉዳዩ ላይ የመነቃቃት ስሜት እንዲፈጠርባቸው እና ክፍተት በሚታይባቸው ቦታዎች ላይ ትኩረት ስጥተው እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

መ. ወደፊት በተመሳሳይ መልኩ ለሚደረጉ ጥናቶች እንደመነሻ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በደብረብርሃን እና በወሎ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ትምህርት ክፍል የበሳል ድርሰትና የስነ-ልሳን ትምህርቶችን መምህራንን የተከታታይ ምዘና አተገባበር መፈተሽ ላይ ነው፡፡

ስለሆነም ጥናቱ በተጠቀሱት ዩኒቨርሲቲዎች እና ትምህርት ክፍሎች የበሳል ድርሰትና የስነ-ልሳን ትምህርቶችን የሚያስተምሩ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ምን አይነት ግንዛቤ እና አመለካከት አላቸው? በተከታታይ ምዘና ሂደት የሚጠቀሟቸው የምዘና ስልቶች የትኞቹ ናቸው? በተከታታይ ምዘና ሂደት የነጥብ /የማርክ/ አሰጣጣቸውና የውጤት አተረጓጎማቸው እንዲሁም የምጋቤ ምላሽ አሰጣጣቸውና የሰነድ አያያዛቸው ምን ይመስላል? እና በተከታታይ ምዘና ሂደት ምን ምን ችግሮች ያጋጥሟቸዋል? የሚሉትን ነጥቦች ይመለከታል፡፡ ነገር ግን እነዚህ መምህራን ምን አይነት የማስተማር ዘዴን ተጠቅመው ያስተምራሉ? የክፍል ውስጥ አመራራቸው ምን ይመስላል? የተከታታይ ምዘና ውጤቶችን እንዴት ሪፖርት ያደርጋሉ? ወዘተ.. የሚሉ ነጥቦችን ጥናቱ አይመለከትም፡፡

ጥናቱ ከላይ በተጠቀሱት ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ያነጣጠረ ቢሆንም የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ከወሎ ዩኒቨርሲቲ ወይም የበሳል ድርሰት መምህራንን ከሥነ-ልሳን መምህራን ጋር የማወዳደር ወይም የማነፃፀር ዓላማ የለውም፡፡ ስለሆነም ንፅፅራዊ ጥናት አይደለም፡፡

## 1.5 የቃላትና የሀረጋት ፍቺ

ምዘና /Assessment/፡ የትምህርት ግብአትና ሂደት መስተጋብራዊ ውጤትን አስመልክቶ ለውሳኔ የሚረዳ አጠቃለይ መረጃ የመሰብሰቢያ ሂደት ነው።

ተለምዷዊ ምዘና፡- በአብዛኛው የፅሁፍ ፈተናዎችን የሚጠቀም፣ፈተናዎቹንም በሴሚስተር አጋማሽና መጨረሻ ላይ ብቻ የሚሰጥ፣ ውጤታዊ የምዘና ስልት ነው።

መደበኛ ፈተና፡- የራሱ የሆነ ጊዜ ተመድቦለት የሚከናወን የምዘና ስልት ነው።

የራስ ምዘና /Self-Assessment/፡-ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው የሚመዘኑበት የምዘና ስልት ነው።

የብጤ ምዘና /Peer-Assessment/፡- ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው ጋር የሚያደርጉት እርስ በርስ የመተራረም ዘዴ ነው።

ኘሮጀክት /Project/፡- ተማሪዎች የተማሩትን ነገር ምን ያህል ተግባር ላይ እንዳዋሉት ለማወቅ በግል ወይም በቡድን እንዲሰሩ የሚሰጣቸው ተግባር ነው።

ሰነደ ትምህርት /Portfolio/፡- ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት የሰሯቸው ትርጉም ያላቸው ተግባራት ስብስብ ነው።

የማሻሻያ እገዛ /Remediation/፡- በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ከሌሎቹ በዘገየ ሁኔታ የሚረዱ ተማሪዎችን መምህሩ በቶሎ እንዲረዱት ለማድረግ የሚያደርገው ድጋፍ ነው።

የማጠናከሪያ እገዛ /Enrichment/፡- በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በፍጥነት የሚረዱ ተማሪዎችን የበለጠ ለማጠናከር የሚሰጥ ማበረታቻ ነው።

የአሰራር ሂደት /Rubric/፡ የተማሪዎች የምዘና ተግባር ብዙ ክፍሎች ሲኖሩትና እያንዳንዳቸውን ማረም በሚያስፈልግበት ጊዜ የሚያገለግል የነጥብ /የማርክ/ መስጫ ዘዴ ነው።

## 1.6 የምህፃረ ቃላት ፍቺ

AED: Academy for educational Development

BESO: Basic Education strategic objective

ICDR: Institute of Curriculum Development and Research

MOE: Ministry of Education

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

### 2.1 የተከታታይ ምዘና ምንነት

የተማሪዎች ምዘና ተማሪዎች ያወቁትን፣የተረዱትንና መስራት የሚችሉትን እውቀት ወይም ችሎታ የምንፈትሽበት ዘዴ ነው፡፡ ይህንንም ለማከናወን ከሚያስችሉ የተለያዩ የምዘና ስልቶች መካከል አንዱ እና ከላይ እንደተገለጸው የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ የትኩረት አቅጣጫ የሆነው ተከታታይ ምዘና ነው፡፡

ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ተከታታይ ምዘና ተከታታይ ድርጊትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህ የምዘና አይነት የክትትል ምዝገባ (Running Records) ፣ ሥርአተ ትምህርት-ተኮር ምዘና (Curriculum based assessment)፣ ሂደታዊ ምዘና (Formative Assessment) ፣ ወዘተ. በሚሉ ስያሚዎች እንደሚጠራ Airasian (1991፣23) እና Joy et al. (2003፣ 4) ይገልጻሉ፡፡ ለተከታታይ ምዘና የተለያዩ ምሁራን ብያኔ አቅርበዋል፡፡

ታጠቁ እና ሌሎች (1996፣8) እንደገለጹት፣ ተከታታይ ምዘና እንደ ሂደታዊ ግምገማ (Formative Evaluation) የሚታይ ሆኖ ትኩረት የሚያደርገው ሥርአት ባለው (ሲስተማቲክ በሆነ) መንገድ ተማሪው በዕውቀት፣ በአስተሳሰብና በክህሎት ያገኘውን ለውጥ በየጊዜው እየተከታተለ የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ BESO II (2003 ፣5) እና Puhl (1997፣3) ተከታታይ ምዘና የመማር ማስተማሩ ሂደት አንድ አካል ሲሆን ተማሪዎች ክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ያገኙትን እውቀት፣ክህሎት፣ልምድ ፣ወዘተ. በአግባቡ ስለመገንዘባቸው ትክክለኛ ውሳኔ ወይም ዳኝነት ለመስጠት የሚያስችሉ መረጃዎችን የማሰባሰብ ሂደት ነው ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

Desalegn and Girma (2009፣283) እና Curzon(1990፣135) በበኩላቸው፣ተከታታይ ምዘና ተማሪውን በክፍል ደረጃው የምንገመግምበት፣ መምህራን የሚከተሏቸው የተለያዩ መለኪያዎቸዎችና የአሠራር ስልቶች ያሉት ሲሆን በዚህም አማካኝነት መምህራን ሥራዎቻቸውን ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር ለማጣጣም፣ የትምህርት አሰጣጣቸው ውጤታማ መሆኑን አለመሆኑን ለመፈተሽ፣ ተማሪዎች ታላሚውን

ግብ መምታትና አለመምታታቸውን ለማወቅ፣የመማር-ማስተማር ሂደቱን እንዲሁም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለማጎልበት የሚያስችል የግምገማ ስልት ነው በማለት ገልፀዋል፡፡

በተጨማሪም ተከታታይ ምዘና በመደበኛ ፈተና አማካኝነት ሊታዩ ወይም ሊመዘኑ የማይችሉ ተፈላጊ ክሂሎችን ፣ በክፍል ውስጥ የሚታዩ መሻሻሎችን፣ ለውጦችን፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን በየጊዜው መገምገም የሚያስችል ነው፡፡ በሌላም በኩል በምንም ዓይነት መንገድ ሊገመገሙ የማይችሉ የተወሰኑ ችሎታዎችን (ጥረት(efforts)፣መንፈሰ ጠንካራነት (persistence) እና አመለካከት (attitude)) ከግምት ውስጥ እንድናስገባ የሚያደርግ የምዘና ስልት ነው (Heaton:1990፣16)፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ብያኔዎች የምንረዳው ተከታታይ ምዘና ሥርአት ባለው መንገድ ተማሪዎች የቀሰሙት ዕውቀት፣ክህሎትና ዝንባሌ ምን ያህል እንደሆነ ለመመዘንና ለማወቅ፣የማስተማርያ ዘዴዎችንና መሣሪያዎችን ለማሻሻል፣የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለመጨመር፣የታቀደውን የትምህርት ግብ ለማሳካት የሚረዳ የምዘና ስልት መሆኑን ነው፡፡

## 2.2 የተከታታይ ምዘና ዓላማ

ተከታታይ ምዘና የመማር-ማስተማሩ ሂደት አካል ሆኖ ሲተገበር ተማሪውን፣ መምህሩን እና ባለድርሻ አካላትን ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ የተለያዩ ዓላማዎችን መሠረት አድርጎ ነው፡፡ Puhl (1997፣3) እንደሚገልጹት፣ የተከታታይ ምዘና ዓላማ የትምህርትን ምዘና ከግምገማ ሚና (Judgemental Role) ወደ ማሻሻያ ሚና (Dev elopment Role) ማሸጋገር ወይም መቀየር ነው፡፡ ይህም ሲባል የተከታታይ ምዘና ዓላማ ተማሪዎችን መገምገም ብቻ ሳይሆን ባስመዘገቡት ውጤት ላይ ተመሥርቶ የተለያዩ ውሳኔዎችን ማስተላለፍ ነው፡፡

Murphy (1996፣35) ደግሞ የተከታታይ ምዘና ዋነኛ አላማ በተከታታይ የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ በመከታተል ተፈላጊ እውቀቶችንና ክሂሎችን መጨበጥ የቻሉትንና ያልቻሉትን በመለየት፣ፈጣንና ውጤታማ ምላሽ በመስጠት ትምህርታችውን ማዳበር ነው ይላሉ፡፡ እንዲሁም Wilkin (1991፣391) የዚህ ምዘና

ዓላማ ተማሪዎች እንዴት መማር እንዳለባቸው ለማቀድ፣ በንቁ ተሳትፎ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ለማስቻል፣ ለተማሪዎች መሻሻል ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት መሆኑን ያስረዳሉ።

ታጠቁ እና ሌሎች (1996፣9) በበኩላቸው፣ የተከታታይ ምዘና አላማ ወቅታዊ (On-Going)፣ የተቀናጀ (Integrated) እና ተግባራዊ (Practical) መረጃ ማሰባሰብ ከመሆኑም በተጨማሪ ስለተማሪው በአንድ ዓይነት መረጃ ላይ ብቻ ተመስርቶ ውሳኔ ለመስጠት ሳይሆን ተማሪው እስከ መጨረሻው ሊማር የሚችልበትን እድል ለማመቻቸትና በመማር ማስተማር ሂደት በእውቀት ፣በአስተሳሰብና በክህሎት ያለውን ለውጥ በትክክል ለማየት ነው በማለት ይገልጻሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ Tamene (2007፣19) እና በድሩ (1994፣86) የተከታታይ ምዘና አላማዎችን እንደሚከተለው ጠቅለል አድርገው ገልጸውታል።

- ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ እየተከታተሉ ስለመሆናቸው ለማወቅና በሂደት ያሳዩትን መሻሻል ለመገንዘብ፣
- የመማር ችግር ያለባቸውን ለመለየትና አስፈላጊውን እርዳታና እርማት ለመስጠት፣
- ስለተማሪዎች አስተማማኝ የሆነ መረጃ አስተያየት ለመስጠት፣
- ለተማሪዎችና ለትምህርቱ ይዘት ምቹ የሆኑ የማስተማሪያ ዘዴዎችንና መሣሪያዎችን ለመምረጥ እና
- በአጠቃላይ በመማር ማስተማሩ ሂደት መሻሻል ስለሚገባቸው ሁኔታዎች ለመወሰንና ሥርአተ ትምህርቱ ወይም መርሀ ትምህርቱ በክፍል ደረጀው መተግበሩን ለማረጋገጥ ነው።

## 2.3 የተከታታይ ምዘና ባሕርያት

ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ውጤት ለማወቅ ብቻ ሳይሆን ከተማሩት ትምህርት ምን እንዳገኙ ለማወቅ ፣እንዲሁም የትምህርት አቀባበላቸውን የበለጠ ለማጎልበትና የተለያዩ እገዛዎችን ለማድረግ የሚረዳ እንደሆነ በዓላማው ተገልጿል። በመሆኑም ተከታታይ ምዘናን ልዩ የሚያደርጉት አራት ባሕርያት እንዳሉት በድሩ (1994፣8) እና ታጠቁ እና ሌሎች (1996፣9) ይገልጻሉ፤

ሀ. ሥርአት ያለው ነው (Systematic)

ተከታታይ ምዘና ስርአት ያለው ነው ሲባል ግልጽ በሆነ መልኩ የተዘጋጀ እቅድ ያለው ሆኖ የተማሪዎች ችሎታ የሚገመገሙባቸውን መሳሪያዎች (instruments) ማለትም የጽሑፍ ፈተናዎች፣የክፍል ምልከታዎች፣የግልና የቡድንስራዎች፣ ቃለ መጠይቆች ወዘተ የሚዘረዝር፣እንዲሁም ግምገማዎቹ የሚደረጉባቸው ጊዜያት ስርአትን ጠብቀው ተከታታይነት ባለው መልኩ የሚቀርብበትነው።

ለ. ሁሉን አቀፍ ነው (Comprehensive)

ይህ የተከታታይ ምዘና ባህሪ የፈተና መልክንና ለመፈተን የምንጠቀምባቸውን መሳሪያዎች አይነት የተለያዩ መሆን እንዳለባቸው የሚጠቁም ነው። ለመገምገሚያ የሚሆኑ መሳሪያዎች ወይም ስልቶች እውቀትን፣ግንዛቤን፣ፍላጎትንና አመለካከትን እንዲሁም የተግባርና የእንቅስቃሴ ክህሎትን የሚያንጸባርቁ ናቸው።

ሐ. በየጊዜው የተሰበሰበ የምዘና ውጤት ነው (Cumulative)

ተከታታይ ምዘና ይህ ባህሪ አለው ሲባል የተማሪዎችን የትምህርት ውጤት መሰረት በማድረግ የውሳኔ ነጥብ ላይ ለመድረስ በተለያዩ ጊዜያት የተሰበሰቡና የተጠራቀሙ ነጥቦች ላይ በመመስረት የተደራጀና አስተማማኝ መረጃ ይሰጣል ማለት ነው።

መ. አቅጣጫ ጠቋሚ ነው (Guidance-Oriented)

ተከታታይ ምዘና ተማሪዎችን በተለያዩ የምዘና ስልቶች አማካኝነት መለየት ስለሚያስችል ተማሪው አልፏል ወይም ወድቋል ከሚል የውሳኔ ሀሳብ ባሻገር ለወደፊት እንዴት ቢማር የበለጠ ውጤታማ ሲሆን እንደሚችል ከወዲሁ ገንቢ አስተያየትና እርምት ይሰጣል።

ከላይ ከተገለፁት በተጨማሪ AED/BESO II (2006፣4) ተከታታይ ምዘና የሚከተሉት ባሕሪያት እንዳሉት ይገልፃል፤

- ስለተማሪዎች የመማር ሁኔታ ወቅታዊ ወይም የማያቋርጥ መረጃ የሚሰጥ፣
- የተለያዩ የምዘና ስልቶችን የሚጠቀም፣
- ወቅቱን የጠበቀ ምጋቤ ምላሽ ለተማሪዎች የሚሰጥ እና
- እንደ ስርአተ ትምህርት ግብ እና አላማ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ነው።

## 2.4 የተከታታይ ምዘና መርሖች

ተከታታይ ምዘና ከሌሎች የምዘና ስልቶች ልዩ የሚያደርጉት ባህሪያት እንዳሉት ሁሉ ጥሩ ተከታታይ ምዘና ሊያሟላቸው የሚገቡ መርሆች አሉ። Shepard (2000፣8)፣ Desalegn (2004፣6) እና ተስፋ (2000፣16-18) NIED (1999)ን መጥቀስ እንደሚገልፁት የሚከተሉት ነጥቦች የተከታታይ ምዘና መርሆች ናቸው፤

- የተከታታይ ምዘና መምህራንን የተለያዩ የምዘና ስልቶችን እንዲጠቀሙ የሚያስችልና ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል።
- ተማሪው አስፈላጊውን ምላሽ እንዲያገኝና የትምህርቱ ሂደት እንዲሻሻል ተከታታይ ምዘና ተማሪ-ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴን የሚያጎለብት መሆን ይኖርበታል።
- የመማር ማስተማር ሂደቱን መሠረት አድርጎ በወቅቱ የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል። ምክንያቱም በትምህርት እቅድ ማብቂያ ላይ የሚካሄድ ምዘና አስፈላጊውን ምጋቤ ምላሽ በመስጠት በኩል የሚኖረው ጠቀሜታ አነስተኛ ነው።
- የምጋቤ ምላሽ ጠቀሜታ ለተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለመምህራንም ጭምር በመሆኑ ተከታታይ ምዘና መምህራን አስፈላጊ ምጋቢ ምላሾችን በወቅቱ እንዲሰጡ የሚያስችል መሆን አለበት።
- የመመዘኛ መስፈርቶችን ለተማሪዎች ማሳወቅ አስፈላጊና ጠቃሚ በመሆኑ ተከታታይ ምዘና ግልፅ መስፈርቶችን የያዘ እና መስፈርቶቹም በተማሪዎች ዘንድ የሚታወቁ መሆን አለባቸው።
- በትምህርቱ አላማዎችና በምዘናው መካከል ያለው ግንኙነት የላላ ከሆነ ምዘናው ለትምህርቱ መሻሻል የሚኖረው ፋይዳ አነስተኛ ይሆናል። አሊያም ላይኖረው ይችላል። ስለዚህ ተከታታይ ምዘና ከትምህርቱ አላማ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል።
- ተከታታይ ምዘና እንደ ተጨማሪ ስራ ሳይሆን የመማር ማስተማሩ ሂደት አካል ሆኖ መተግበር አለበት። እንዲሁም አስተማማኝ፣ዋጋ ያለውና ከአድሎ የፀዳ መሆን ይኖርበታል።

## 2.5 የተከታታይ ምዘና ጠቀሜታ

የጥናነት መገለጫን ያሟላ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን እውቀትና ችሎታ ድክመትና ጥንካሬ፣ፍላጎትና የዕለት ተዕለት መሻሻልን በተከታታይ የሚመዝን እና ስለትምህርቱ ስለመምህራንና ተማሪዎች መረጃ የሚሰጥ በመሆኑ አስፈላጊነቱና ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

### 2.5.1 ተከታታይ ምዘና ለመምህራን የሚሰጠው ጥቅም

መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችንና ቴክኒኮችን በመጠቀም ተከታታይ ምዘናን ቢያካሂዱ በመማር-ማስተማር ሂደቱ ላይ የሚታዩ ችግሮችን ወይም ክፍተቶችን በመለየት ወቅታዊ እርምት በማካሄድ በትምህርት እቅዱ የተቀመጡትን አላማዎች በአስተማማኝ ደረጃ እውን ማድረግ ይችላሉ (Puhl፡1997፣3)፡፡

Chapell and Douglas (1993፣34) ተከታታይ ምዘና ለመምህራን የሚሰጠውን ጥቅም በተመለከተ እንደገለፁት መምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶችን ተጠቅመው ተማሪዎቻቸውን በሚመዝኑበት ጊዜ የሚያስተምሩት የትምህርት ይዘት በተማሪዎች ተረድኦ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ለመቆጣጠር፣ በፈተና እና በክፍል ውስጥ ተግባራት መካከል ያለውን ያለመጣጣም ችግር ለማስተካከል እንዲሁም የመማር ማስተማሩን ሂደት ጥራት ከፍተኛ የተማሪ ቁጥር በሚያስተናግድ ክፍል ውስጥም ቢሆን ለማሻሻል ይረዳል፡፡ ይህም ሙያዊ እርካታቸው እንዲጨምር የማስተማር ድካማቸው እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

በተጨማሪ Desalegn (2004፣7)፣ Heaton (1990፣122) እና Pacheler and Field (2001፣203) ተከታታይ ምዘና ለመምህራን የሚያስገኘውን ጠቀሜታ እንደሚከተለው ዘርዝረዋቸዋል፤

- ለመምህራን ተማሪው አስቀድሞ ያለውን እውቀት፣ በወቅቱ ያገኘውን እውቀት እና ወደፊት ሊኖረው የሚገባውን በትክክል ለይቶ ለማወቅና አስፈላጊውን የማሻሻያና የማስተካከያ እገዛ በማድረግ የተማሪውን የመማር ሁኔታ ለማስተካከል ያግዛል፡፡
- ተማሪዎች የሚማሩትን የትምህርት አይነት (Course) ይዘት በሚገባና በሚጠበቀው መጠን መቅሰማቸውን ለማወቅና ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን ለመለየት ያስችላል፡፡

- መምህራን የማስተማር ብቃታቸውን፣ ዘዴያቸውንና መሣሪያቸውን በተመለከተ ከስርአተትምህርቱ፣ ከተማሪዎች ፍላጎትና ችሎታ አንፃር መረጃ በማግኘት አስፈላጊውን ማስተካከያ በወቅቱ ለማድረግ ይረዳል፡፡
- ተማሪዎች ባላቸው እውቀት፣ ችሎታ፣ ልዩ ልዩ ዝንባሌና ሌሎች ክሂሎች ላይ በመመርኮዝ አስፈላጊውን መረጣ፣ ዝውውር፣ ምደባ ወዘተ. የመሳሰሉትን ለማካሄድ ይጠቅማል፡፡
- ከተለያየ አካባቢ በሚመጡ ተማሪዎች መካከል ሊፈጠር የሚችለውን ተገቢ ያልሆነ የጎላ የውጤት ልዩነትን ለማጥበብ ያስችላል፡፡
- በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ጤናማ የሆነ ግንኙነት ለመፍጠር ያስችላል፡፡
- የተማሪዎች የትምህርት እድገትና መሻሻልን በተመለከተ ውጤታቸውን በደረጃ ለማስቀ መጥ እና ለተማሪዎች፣ለወላጆችና ለሚመለከታቸው የትምህርት አካላት መረጃ ለማቅረብ ይረዳል፡፡

### 2.5.2 ተከታታይ ምዘና ለተማሪዎች የሚሰጠው ጥቅም

ተከታታይ ምዘና የተለያዩ የምዘና ስልቶችን ተጠቅሞ ሂደታዊ በሆነ መንገድ ተማሪዎችን የሚመዝን በመሆኑ ተማሪዎች ብቃታቸውን እንዲያሻሽሉ፣ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የትምህርት ይዘቶች ላይ ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ፣ በትምህርታቸው ውጤታማ ሊያደርጓቸው የሚችሉ አማራጮችን በነፃነት ማግኘት እንዲችሉ እና በትምህርታቸው ላይ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል (Wilkin፡ 1991፣39 እና Puhl፡ 1997፣6)፡፡

ከዚህም በተጨማሪ Desalegn (2004፣7) እና Tamene (2004፣19) ተከታታይ ምዘና ለተማሪዎች የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች እንደሚያስገኝ ይገልፃሉ፤

- ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን እንዲለዩ፣ በራስ የመተማመን መንፈስን እንዲያጎለብቱና ችሎታቸውን አውቀው ወደፊት መቀጠል እንዲችሉ ያደርጋቸዋል፡፡
- የተለያዩ ምጋቤ ምላሾችንና እገዛዎችን ከቢጤዎቻቸውና ከመምህሮቻቸው እንዲያገኙ፣ በጋራ የመስራት ችሎታቸውንና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን እንዲ ያዳብሩ ያግዛቸዋል፡፡

- ተማሪዎች ከመምህሮቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙት ለማጐልበት እና ለችግሮች መፍትሄ የመስጠት ችሎታቸውን ለማዳበር እድል ይሰጣቸዋል፡፡
- መደበኛ የአጠናን ዘዴን እንዲከተሉና በመጨረሻ ሰአት የሚደረግ የሽምደዳ ጥናት ዘዴን እዲያስወግዱ ያግዛቸዋል፡፡
- የሚማሩትን ትምህርት በጥልቀት ማየትና መመርመር እንዲችሉ እና
- በቆይታዎች አንዴ ጊዜ በሚሰጥ ፈተና ምክንያት የሚያጋጥማቸውን የመደናገጥ፣ የመጨነቅና የመረበሽ ስሜታቸውን ለመቀንስ ብሎም ለማጥፋት ይረዳቸዋል፡፡

## 2.6 በተከታታይ ምዘና እና በተለምዷዊው ምዘና መካከል ያሉ ልዩነቶች

ከላይ ከተገለፁት የተከታታይ ምዘና ምንነት፣ አላማ እና ጠቀሜታ በመነሳት ተከታታይ ምዘና ከተለምዷዊው ምዘና በምን እንደሚለይ መገመት አዳጋች አይሆንም፡፡ ሆኖም ግን የበለጠ ግልፅ ለማድረግ Elington and Earl (1997፣2)፣ Puhl (1997፣4) እና Nitko (2004፣24) የጠቀሷቸው የልዩነት ነጥቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

- ተለምዷዊው ምዘና ውጤታዊ የምዘና ስልትን (Summative Evaluation) የሚከተል ሲሆን ፈተናዎቹ የሚሰጡት በሴሚስተር አጋማሽና መጨረሻ ላይ ብቻ ነው፡፡ በአንፃሩ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችንና የመምህሩን ውጤታማነት ለማዳበር ገደብ ሳይበጅለት የመማር ማስተማሩ ሂደት አካል ሆኖ ምንጊዜም የሚተገበር ሂደታዊ የምዘና ስልት ነው፡፡
- ተለምዷዊው ምዘና በአብዛኛው የፅሁፍ ፈተናዎችን የሚጠቀም ሲሆን ተከታታይ ምዘና ግን የፅሁፍ ተግባራት ላይ ብቻ ሳይወሰን የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ዘዴዎችን (ምልከታ፣የቃል ጥያቄ፣የግልና የቡድን ስራዎች ወዘተ…) ይጠቀማል፡፡ ይህም የመማር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለመለየትና ድጋፍ ለመስጠት ያስችላል፡፡
- የተለምዷዊው ምዘና ትኩረት የተማሪዎች የመማር ውጤት ወይም እውቀት ላይ ብቻ በመሆኑ አልፏል ወይም ወድቋል የሚል የውሳኔ ሀሳብ መስጠት ብቻ እንጂ ምጋቤ ምላሽ አያስገኝም፡፡ በአንጻሩ ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በግላቸውና ከጓደኞ ቻቸውጋር በመሆን የሚያካሄዷቸውን ምዘናዎች ስለሚያካትት ለተማሪዎችም፣

ለመምህራንም ጠቃሚ ምጋቤ ምላሽ ያስገኛል፡፡ በመሆኑም በትምህርቱ ሂደት መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዩች ለማሻሻል ይረዳል፡፡

- በአጠቃላይ ተለምዷዊው ምዘና የተማሪዎችን ሁለንተናዊ ገጽታ በትክክል አያሳይም፡፡ ይህ አይነቱ ምዘና የግንዛቤ (Cognitive domains) ብቻ የሚመዝን ሲሆን ሌሎች የአስተሳሰብና የክህሎት(Affective and Psychomotor Domains) እውቀት ዘርፎችን አይጨምርም፡፡ ተከታታይ ምዘና ግን ተማሪዎች በማስታወስ ችሎታ ላይ ብቻ እንዳያተኩሩ ሌሎችም የእውቀት ዘርፎች በማካተት ሁሉን-አቀፍ የሆነ ችሎታ እንዲኖራቸው የሚያደርግ የምዘና ስልት ነው፡፡

## 2.7 መምህራን ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ለማድረግ ሊከተሏቸው የሚገቡ ነጥቦች

በማስተማሩ ስራ የተሰማሩ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ትምህርት የመቀበል ችሎታ በልዩ ልዩ ዘዴዎች መመዘን ከዋና ዋና ተግባሮቻቸው መካካል አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ምቹ እና ውጤታማ የሆነ ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ መምህራን የሚከተሉትን አይቀሬ ቅድመ-ሁኔታዎች ማሟላት እንዳለባቸው ICDR (2004፣15) MOE(1996፣13) እና Bekalu (2007፣32) ያስረዳሉ፤

- *ስለ ተከታታይ ምዘና እና ዘዴዎቹ በቂ እውቀትና ችሎታ፡-* መምህራን ስለ ተከታታይ ምዘና አተገባበር በተለያዩ ስልጠናዎች፣በልምድ ልውውጦችና በተለያዩ አጋዥ ጽሑፎች አማካኝነት ግንዛቤ ካላቸው እውነተኛውን ተከታታይ ምዘና ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላቸዋል፡፡ ነገር ግን በትእዛዝ ብቻ ስሩ የሚባሉ ከሆነ ከተከታታይ ምዘናው አላማ ውጭ የሆነ ተግባር ሊከሰት ይችላል፡፡ ስለዚህ መምህራን ተከታታይ ምዘናን በትክክል ለመተግበር በቅድሚያ እውቀቱና ግንዛቤው ሊኖራቸው ይገባል ማለት ነው፡፡
- *የተከታታይ ምዘና እቅድ ማዘጋጀት ፡-* መምህራን ባገኙት እውቀት ወይም ግንዛቤ መሰረት ምዘናው መቼ፣እንዴትና በምን አይነት ዘዴ እንደሚካሄድ ከወዲሁ በአግባቡ ሊያቅዱ ይገባል፡፡ እቅዱም ከትምህርቱ አላማና ተማሪዎች ከሚመዘኑባቸው ርእሰ ጉዳዩች አንጻር የሚጠበቁትን ለውጦች የሚያሳይ ሆኖ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡
- *የተለያዩ የምዘና ስልቶችን መምረጥ፣ማዘጋጀትና መተግበር፡-* የምዘና ስልቶቹን በሚመርጡበት ጊዜ ስልቶቹ በእቅድ ላይ የተመሰረቱ፣ከትምህርት ግቦችና

አላማዎች ጋር፣ከተማሪዎች ፍላጎትና ችሎታ ጋር የሚጣጠሙ እንዲሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ እንዲሁም በክፍል ውስጥ የሚኖሩ ነባራዊ ሁኔታዎችንና ማህበራዊ ተጽእኖዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ መልኩ ተመርጦ የሚተገበር ምዘና ተማሪዎች የቀሰሙትን ትምህርትና ችሎታ ለማሳየትና ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን ተረድተው ራሳቸውን እንዲያሻሽሉ እድል ይሰጣል፡፡ በድንገት ያለ ዝግጅት ከሆነ ግን ተከታታይ ምዘናው በትክክል እንዳይተገበር እንቅፋት ይሆናል፡፡

- *በተለያዩ የምዘና ስልቶች አማካኝነት የተሰበሰቡትን የተማሪዎች ውጤት በጥንቃቄ መዝግቦ መያዝ*፡ ተማሪዎች በተለያየ መንገድ ተመዝነው ያገኟቸው ነጥቦች በየተሰበሰቡ በት የምዘና አይነት በአግባቡ መዝግቦ ማስቀመጥ ተገቢ ነው ፡፡ ምክንያቱም ተማሪ ዎች በየጊዜው የሚያከናውኗቸውን ተግባራትና ውጤታቸውን በተመለከተ ለሚመለ ከታቸው አካላትና ለተማሪዎች መረጃ ለመስጠት ወሳኝነት አለው፡፡ ይህም ተማሪዎችን ለትምህርት ያነሳሳል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የተማሪዎች ስራ ትኩረት ስለሚያጣ የመማር ፍላጎታቸው ሊቀንስ ይችላል፡፡

በተጨማሪም ተከታታይ ምዘና ጋር በተያያዘ መምህራን በርካታ የሙያ ሀላፊነቶች አሉባቸው፡፡ ከእነዚህም መካከል የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው፤

- መምህራን ተገቢ የምዘና ዘዴዎችን መምረጥ፣
- ተገቢ የጥያቄ አይነቶችን ማዘጋጀትና መጠቀም፣
- የተማሪዎቻቸውን ውጤት በወቅቱ መግለጽና ተገቢው አገልግሎት ላይ ማዋል፣
- በምዘና ሂደት ሊከሰት የሚችል አድሎዎን ማስወገድ፣
- ስለሚሰጡት ፈተና ወይም ተግባር ለተማሪዎቻቸው አስፈላጊውን መረጃ በቅድሚያ መስጠት፣
- የተማሪዎችን ውጤት ሚስጢራዊነት መጠበቅ እና
- ተማሪዎች ለፈተና ዝግጁ ሆነው እንዲቀርቡ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል (በድሩ፡19 94፣17-24)፡፡

## 2.8 በተከታታይ ምዘና ሂደት የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ

ከተከታታይ ምዘና አላማዎች መካከል ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ መስጠት አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም ምጋቤ ምላሽ መስጠትና መቀበል በተከታታይ ምዘና ሂደት ውስጥ ዋነኛና አይቀሬ ተግባራት ናቸው (Brooks:2002፣64)፡፡ ይህን በተመለከተ (Lissitz and Schafer 2000፣70 )ሲገልፁ ምጋቤ ምላሽ የተማሪዎችን መሻሻል ለመደገፍ የሚረዳ ጠቃሚ መሣሪያ ነው፡፡ ስለዚህ መምህራን ተማሪዎች እንዲያውቁ ወይም እንዲሰሩ ከሚጠበቅባቸው ተግባራት በመነሳት ከመስፈርቶቻቸው ጋር ተያያዥነት ያለው ግልፅ የሆነ ምጋቤ ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህም ተማሪዎች ጥንካሬያቸውንና ድክመታቸውን ለይተው መሻሻሎችን ለማድረግ ይነሳሳሉ፡፡

Gipps (1994፣32) እና Harmer (2001፡104)ደግሞ ተከታታይ ምዘናና ምጋቤ ምላሽ የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን በሚያከናውኑበት ጊዜ ምጋቤ ምላሹም አብሮ የሚያያዝ ሲሆን ፈጣን፣ግልፅና ተማሪዎች ችግራቸውን አስተካክለው ለተሻለ ትግበራ እንዲጥሩ የሚያደርግ ነው፡፡ ስለዚህ መምህራን ማስተማራቸው ላይ ብቻ ሳይሆን ትኩረት ማድረግ ያለባቸው የተለያዩ የምዘና ስልቶችን በመጠቀምና የተማሪዎቻቸውን ችግር በመለየት በእያንዳንዱ የትምህርት ሂደት ላይ ወቅታዊ ምጋቤ ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን Brooks (2002፡54) መምህራን አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት በኩል ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ያስረዳል፡፡

መምህራን ወቅታዊ ምላሽ ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡ ከሆነ ተማሪዎች እጅግ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ምክንያቱም ከነችግሮቻቸው ብዙ ርቀት ሳይጓዙ ከወዲሁ ስህተቶቻቸውን ያርማሉ፤ ወደፊትም ብቃታቸውን ወይም ክሂላቸውን ያዳብራሉ (Brooks፡2002)፡፡

ስለዚህ ምጋቤ ምላሽ የመማር ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ በማድረግ በኩል የሚኖረውን ፋይዳ የበለጠ ከፍ ለማድረግ የቋንቋ መምህራን አፋጣኝና ትክክለኛ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ከፍተኛውን ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.9 የተከታታይ ምዘና ስልቶች /Tools or Techniques of Continuous Assessment)

ከተለያዩ የፅሁፍ ፈተናዎች በተጨማሪ ተማሪዎችን በተለያየ መንገድ ለመመዘን የሚያስችሉ ልዩ ልዩ የተከታታይ ምዘና መሣሪያዎች ወይም ስልቶች አሉ። እነዚህንም ስልቶች ከቋንቋ ትምህርት ይዘት፣ አላማ እና ከተማሪዎች እውቀትና ፍላጎት አንፃር እያመቻቹ እና እያስማሙ መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል። በተከታታይ ምዘና ሂደት በአብዛኛው ተማሪዎችን ለመመዘን የሚያገለግሉ የምዘና ስልቶች እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል።

1. የቃል ጥያቄ /Oral Questioning/

ጥያቄዎችን በማዘጋጀት፣ለተጠያቂው በማሳወቅ ወይም ርዕሱን ብቻ በመንገር መላሹ በሚሰጠው መልስ ላይ በመመስረት የተለያዩ ጥያቄዎች የሚጠይቅበት ስልት ነው (ታጠቁ እና ሌሎች :1996፣16)።

ይህ የምዘና ስልት ተማሪዎችን በማስተማርና በመፈተን ሂደት ውስጥ የተለያዩ አላማዎች ይኖሩታል። ይህም ሲባል የተማሪዎችን ዝግጅት ለመገምገምና ተረድኦታቸውን ለመፈተሽ ፣ የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን ለመለየት ወዘተ አላማ ሊያገለግል ይችላል። Richards and Lockhant (1994:10) እንደሚገልፁት የቃል ጥያቄ ለቋንቋ ትምህርት ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች በቃላቸው ከሚናገሯቸው ነጥቦች በመነሳት ታላሚውን ቋንቋ ምን ያህል እንደተገነዘቡት ለማወቅ ያስችላል። ከዚህም በተጨማሪ በክፍል ውስጥ ያለውን የመማር ማስተማር ክንውን ከሁኔታዎች አንፃር ለማስተካከል፣ ተማሪዎች የዕለቱ ትምህርት ላይ እንዲያተኩሩ ለማድረግና መምህሩንና ተማሪዎችን ለማቀራረብ የሚረዳ የምዘና ስልት ነው።

2. ምልከታ (Observation)

ምልከታ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚያከናውኗቸውን ልዩ ልዩ ተግባራት በቀጥታ በመመልከት መረጃ የሚሰበሰብበት የምዘና ዘዴ ነው። ምልከታው ከተማሪው ወይም ከእውነታው ጋር በአካል መገናኘት የሚያስችል ስለሆነ ተአማኒነቱ የላቀ ነው።

እንዲህ መሆኑ ደግሞ ትክክለኛውን ነገር አውቆ ተገቢና ወቅታዊ ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት ይረዳል (Puhl:1997፣5)።

መምህራን የምልከታ ዘዴን ተጠቅመው ተማሪዎቻቸውን መገምገም በሚያስቡበት ጊዜ አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። Harmer (2001፣346) መምህራን የምልከታ ስልት በሚጠቀሙበት ጊዜ መመልከት የሚፈልጉትን ነገር በቅድሚያ ማወቅና ማዘጋጀት፣ተማሪዎች በግልም ሆነ በቡድን የሚሰሯቸው ስራዎች ላይ ማተኩር እና በጥሞና መከታታልና ጠቃሚ ነጥቦችን ማስታወሻ ላይ መፃፍ ይኖርባቸዋል በማለት ያስረዳሉ።

3. ሙከራና ፈተና /Test and Examination)

ሙከራና ፈተና በተከታታይ ምዘና ሂደት የሚዘወተሩና የማይቀሩ የምዘና ስልቶች ናቸው። ይሁንና በሁለቱ መካከል የተወሰነ ልዩነት እንዳለ Norries (2000፣275) ይገልጻሉ። ሙከራ ለተማሪዎች መቼ እንደሚሰጣቸው ሳይነገራቸው ባላቸው ዝግጅት የሚመልሱት ነው። አቀራረቡም በቃል ወይም በጽሁፍ ሊሆን ይችላል። ፈተና ከሆነ ግን መምህሩ ለመፈተን ሲያስብ መቼ እንደሚሆንና የትኛውን የትምህርት ይዘት እንደሚያካትት ይነግራቸዋል። አቀራረቡም በጽሁፍ ሲሆን ምጋቤ ምላሹም የሚሰጠው በጽሁፍ ብቻ ነው።

እንደ Bachman (1990፣2) ገለጻ ፈተና በቋንቋ ትምህርት ሂደት አይቀሬ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ስለተማሪዎች ጠንካራና ደካማ ጎን መረጃ ከመስጠቱም በተጨማሪ የትምህርቱን አቀራረብ ለመገምገምና ለማሻሻል ያግዛል። ከዚህም ባሻገር ተማሪዎች በጊዜው ለሚፈተኗቸው ፈተናዎች ዝግጅት ስለሚያደርጉ የትምህርቱን ይዘት በአግባቡ መረዳትና በጥልቀት መመርመር እንዲችሉ፣በፈተናቸው ውጤት መሠረት ምጋቤ ምላሽ እንዲያገኙ፣ማሻሻል ያለባቸውን እንዲያሻሽሉ ወይም አጠናክረው እንዲቀ ጥሉ ያደርጋቸዋል። Nitko (2004፣3) በበኩላቸው ፈተና መምህራን የተማሪዎቻውን ግን ዛቤ የሚያረጋግጡበት በመሆኑ ተማሪዎቻቸውን ለመለየት፣ የማስተማሪያ ዘዴውን ለማሻሻል፣ በአጠቃላይ የተለያዩ ውሳኔዎችን ለማሳኬድ ግብአት በመሆን እንደሚያገለ ግል ያስረዳሉ።

ነገር ግን ፈተናዎች በየጊዜው የማይሰጡ የሴሚስተሩ ማጠቃለያ ላይ ብቻ የሚሰጡ ከሆነ ተማሪዎች ማሻሻል ስለሚገባቸውን ጉዳዮች፣ መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ማስተካከል ስለሚገባቸው ነገሮች የሚሰጡት መረጃ በጣም ያነስ ይሆናል (Teshome: 2001፣28)። ስለዚህ መምህራን ሙከራንና ፈተናን በየጊዜው በመጠቀም ተማሪዎቻቸውን ሊመዝኑ ይገባል።

4. በተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ / Presentation/

ይህ የምዘና ስልት ተማሪዎች የተለያዩ ማኀህፍትን በማንበብ ወይም ከማህበረሰቡ ጋር መስተጋብር በመፍጠርና የሚፈልጉትን በመጠየቅ የሰሯቸውን የተለያዩ ተግባራት በክፍል ውስጥ ከጓደኞቻቸው ፊት በመውጣት የሚያቀርቡበት ነው። በመሆኑም ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሀሳባቸውን የመግለፅ ችሎታቸውን፣ የሀሳብ አደረጃጀታቸው ንና የቋንቋ አጠቃቀማቸውን ወዘተ... ለመመዘን ያስችላል (Shaaban: 2001፣19)። ይህ ዘዴ ተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀም ብቃታቸው እንዲሻሻል ፍርሃታቸው እንዲቀንስ የሚረዳ ቢሆንም በርካታ ተማሪዎች ባሉበት መማሪያ ክፍል ውስጥ በቀላሉ ለመተግበር አስቸጋሪ እንደሚሆን ጨምረው ይገልፃሉ።

5. የጥንድ እና የቡድን ስራ /Peer and Group Work/

የጥንድ እና የቡድን ስራ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለማስተማርና ለመመዘን በስፋት የሚጠቀሙባቸው ስልቶቻቸው ናቸው። Brown et al.(1997፣77) እንደሚገልጹት የጥንድና የቡድን ስራዎች ተማሪዎች በጋራ የመስራት ፍላጎትና ልምድ እንዲኖራቸው መሰረት ይሆናሉ። በተጨማሪም የንግግር ክሂላቸው እንዲዳብር፣እርስበርስ በመማርና በመተጋገዝ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በራሳቸው መፍታት እንዲችሉ በማድረግ በኩል ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ነገር ግን እነዚህን የምዘና ዘዴዎች በምንጠቀምበት ጊዜ ተማሪዎች ዋናውን ጉዳይ በመተው ወደ ግል ስራቸው ወይም ጨዋታቸው ሊያመዝኑ እና የተወሰኑ ተማሪዎች በሌሎች ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። ስለዚህ መምህራን ተማሪዎቻቸውን መከታተልና ወደሚፈለገው ተግባር ማምጣት ይኖርባቸዋል።

6. የመምህር ተማሪ ውይይት /Teacher-Student Conference/

ይህ ዘዴ ከቃለ መጠይቅ ጋር ተቀራራቢ ሲሆን ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት በተመለከተ ምን አይነት ግንዛቤ እንደያዙ፣ምን አይነት መሻሻል እንዳሳዩ እና ምን አይነት የአሰራር ስልት እንደተከተሉ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ መረጃ የሚሰበሰብበት ነው።

የመምህር ተማሪ ውይይት ለመምህራን የሚያስገኘው ጥቅም ተማሪዎቻቸው ስላላቸው እውቀትና ስላሉበት ደረጃ አእምሯዊ ስእል ከመስጠቱም በተጨማሪ የተማሪዎቹን ፍላጎትና ለውጥ በቅርበት ማወቅ ስለሚያስችል አስፈላጊውን ዝግጅትና እገዛ ለማድረግ መንገድ ይከፍታል። ተማሪዎችም ከመምህሮቻቸው ጋር በሚያደርጓቸው ውይይቶች አማካኝነት የንግግር ክሂላቸው ይዳብራል (Shaaban: 2001፣20)።

7. የራስ ምዘና /Self-Assessment/

የራስ ምዘና ስልት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አይነተኛ ቦታ ያለው፣ ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው የሚመዝኑበት ሂደት ነው (Puhl: 1997፣6)።እንዲሁም የራስ ምዘና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚሰጡ ትምህርቶች መሠረታዊ ወይም ጠቃሚ የሆነ ዘዴ እንደሆነ Desalegn and Girma (2004፣296) ይገልፃሉ።

የራስ ምዘና ለተማሪዎች የሚያስገኘው ጥቅም ከፍተኛ ነው። Desalegn and Girma (2004፣29-293) ፣Puhl (1997፣6) እና Harris (1997፣5) እንደሚገልፁት ተማሪዎች እራሳቸውን በራሳቸው የሚመዝኑበት ሁኔታ ከተመቻቸላቸው ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን መለየት፣ በየጊዜው የሚያሳዩትን ለውጥ መቆጣጠርና የማሻሻያ ወይም የማጠናከሪያ እርምጃዎችን መውሰድ ይችላሉ። በትምህርታቸውም ላይ የባለቤትነት ስሜት ያድርባቸዋል። የማገናዘብ ችሎታቸውና የመማር ተነሳሽነታቸው ይጨምራል።

በተጨማሪም ተማሪዎች በራስ የመተማመን ችሎታቸው ይጐለብታል። ይህ ደግሞ ግልፅነት በተሞላበት መንፈስ ከመምህራኖቻቸው ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠርና ለችግሮቻቸው መፍትሄ መፈለግ እንዲችሉ ያደርጋቸዋል። ለመምህራንም የስራ ጫና ይቀንሳል።

ስለዚህ በዚህ የምዘና ዘዴ ተማሪዎች ትክክለኛ እና ፍትሀዊ ምዘና እንዲያካሂዱ መምህራን ተማሪዎች ራሳቸውን የሚገመግሙበት ነጥቦች ወይም መገምገሚያ ዝርዝሮች በቅድሚያ አዘጋጅተው ሊሰጧቸው ይገባል (Puhl፣1997)።

## 8. የብጤ ምዘና / Peer Assessment/

የብጤ ምዘና እንደ የራስ ምዘና ሁሉ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ያለው ቦታ ከፍተኛ ሲሆን በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው ጋር የሚያደርጉት እርስ በርስ የመገማገም ዘዴ ነው (Puhl፣1997፡7)።

የብጤ ምዘና ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው ጋር የሚያደርጉት የእርስ በርስ የመተራረም ዘዴ ነው (ሰለሞን : 1987፣8)። በተጨማሪም ተማሪዎች ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ሊመዝኑ የሚችሉበትን የመመዘኛ ማረጋገጫ ዝርዝሮች /Check Lists/ መምህሩ ሊያስገነዝባቸው ይገባል፤ ወደ ምዘናውም ከመሄዳቸው በፊት መለማመድ ያስፈል ጋቸዋል በማለት ያስረዳሉ።

የብጤ ምዘና ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ማህበራዊነት እንዲፈጥሩ፣ እርስ በርስ ምጋቤ ምላሽ እንዲለዋወጡ፣ በራሳቸው ለመገምገም የሚያስችሏቸውን መስፈርት እንዲያዘጋጁ፣ ሀሳባቸውን እንዲያንፀባርቁ፣ እንዲነቃቁና ነገሮችን አመዛዝኖ ማየት እንዲችሉ ያደርጋል Puhl (1997፣8)። የብጤ ምዘና እነዚህን ጠቀሜታዎች የሚያስገኝ ቢሆንም ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው ጋር ከሚኖራቸው ቅርበት የተነሳ ትክክለኛ አስተያየት ላይሰጡ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ የተወሰኑ ተማሪዎች የጓደኞቻቸውን አስተያየት አምነው ላይቀበሉ ይችላሉ በማለት Puhl (1997) ጨምረው ገልፀዋል።

## 9. የፕሮጀክት ምዘና /Project Assessment/

ፕሮጀክት ከተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ተማሪዎች በግል ወይም በቡድን በመደራጀት በክፍል ውስጥ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ የተማሩትን ትምህርት ወይም ንድፈ ሀሳብ በተግባር መስራትና ማሳየት መቻላቸውን ለማወቅ የሚካሄድ የምዘና ስልት ነው (MOE 1996፣17)።

በግልም ሆነ በቡድን የሚሰሩ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ትክክለኛው ጊዜ ተመድቦላቸው ተማሪዎች ምን እንደሚሰሩና በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ እንደሚኖርባቸው የሚያሳይ ዕቅድ በጥንቃቄ ተዘጋጅቶላቸው ሊከናወኑ ይገባል (MOE: 1996፣ 20)፡፡በተ ጨማሪም መምህራንም የተማሪዎቻቸውን የግልና የቡድን ፕሮጀክት ስራዎች የሚቆጣ ጠሩበት የመመዘኛ ማረጋገጫ ዝርዝር (Check List) ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህንንም የመመ ዘኛ ዝርዝር ለተማሪዎቻቸው ማሳወቅና በዝግጅት ሂደቱም ውስጥ ማሳተፍ ይኖርባቸዋል (Brown and Knight፡ 1994፣74)፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ በግልም ሆነ በቡድን የሚከናወን የፕሮጀክት ምዘና ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸውና ራሳቸውን ችለው መስራት እንዲችሉ እድል ይሰጣል፡፡ እንዲሁም በስራ ሂደት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በራሳቸው መፍታት እንዲችሉና እርስ በርስ ተባብሮ የመስራት ልምድ እንዲያደብሩ ያግዛል (Brown et al.1997፣78)፡፡

ይሁን እንጂ በፕሮጀክት ስራ ጋር በተያያዘ በተማሪዎች በኩል እርስ በርስ ያለመስማት፣ የጊዜ ማነስ እና ውጤት /ማርክ/ ላይ ብቻ በማተኮር ለመማር ያለመፈለግ ችግር ሊያጋጥም ይችላል፡፡ እንዲሁም በመምህራን በኩል በተማሪዎቻቸው ፕሮጀክት መሠረት በቡድን ስራው የተሳተፉትን ተማሪዎች በሙሉ በእኩል አይን ለመመዘን ይቸገራሉ፡፡ ስራዎቹንም ለተማሪዎች አቅዶ ለመስጠትና አስፈላጊውን ምጋቤ ምላሽ በወቅቱ ለመስጠት ጊዜ ይወስድባቸዋል ሲሉ (Brown et al.፣1997) ገልፀዋል፡፡

## 10. ሰነደ ትምህርት /Portfolio/

Puhl (1997፣8) እንደሚገልጹት፣ ሰነደ ትምህርት ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት ያከናወኗቸው ትርጉም ያላቸው ሥራዎች ስብስብ ሲሆን ተማሪዎች ስላገኙት ዕውቀትና መሻሻል ቁልጭ ያለ ምስል የሚሰጥ የተከታታይ ምዘና ስልት ነው፡፡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ቆይታቸው የሚሰሯቸውን ክንዋኔዎች፣ጥረቶች፣ መሻሻሎች ንና ብቃቶችን የሚያሳይ በመሆኑ ለቋንቋ ትምህርት ምዘና ተመራጭ እንደሆነ (Puhl፣1997) አክለው ይገልፃሉ፡፡

ሰነደ ትምህርት ለተማሪዎች መመዘኛነት መጠቀም የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች እንደሚያስገኝ Desalegn and Girma (2007፣300-30)፣ እና Elington and Earil (1997፣8) ያስረዳሉ።

- የተለያዩ ስራዎች ስብስብ እንደመሆናቸው መጠን ተማሪዎች ምን እንደተረዱና ምን አይነት ክሂሎችን እንዳዳበሩ ለማወቅ ያስችላል።
- ከፈተና በተሻለ ሁኔታ ስለተማሪዎች በቂ መረጃ ይሰጣል።
- ተማሪዎች በየጊዜው ያሳዩትን ለውጥ ለመከታተል እና ለሚመለከታቸውም አካላት አስፈላጊውን መረጃ ለመስጠት ይረዳል።

ሰነደ ትምህርት ለመማር ማስተማሩ ሂደት የሚሰጠው ፋይዳ ከፍተኛ ቢሆንም የራሱ የሆነ ደካማ ጎኖች አሉት። እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

- መምህሩ የሁሉንም ተማሪዎች ስራ አንብቦ ወቅታዊ ምጋቤ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል። ይሁንና ስራው አድካሚ፣ አሰልቺና ጊዜ የሚፈልግ በመሆኑ መምህሩ ምዘናውን በበቂ ሁኔታ ላያከናውንና ፍትሀዊ ውጤት ላይሰጥ ይችላል።
- ተማሪዎች የሚያዘጋጇቸው ሰነደ ትምህርቶች አንድ አይነት ባለመሆናቸው እያንዳንዱን ጉዳይ ለመመዘን የሚያስችል መስፈርት መምህሩ ማዘጋጀት ይኖርበታል። ከዚህ አንፃር ለተለያዩ ጉዳዩች የተለያየ መስፈርት አዘጋጅቶ መመዘን አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል Elington and Earil (1997)።

በአጠቃላይ ሁሉንም የተከታታይ ምዘና ዘዴዎችን መምህራን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ተማሪዎቻቸውን የሚመዝኑበት፣ ተማሪዎችም ራሳቸውንና ጓደኞቻቸውን የሚመዝኑበት የመመዘኛ ማረጋገጫ ዝርዝር /Check list/ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም መመዘኛ መስፈርቱ የሚያስፈልገው እሱን ብቻ መሠረት አድርጎ ተማሪዎች ለሰሩት ስራ ፍትሀዊ ውጤት ለመስጠት ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ የተከታታይ ምዘና ዘዴ ወይም ተማሪዎች በሚሰሯቸው ሥራዎች ዙሪያ ግልፅ አላማ ለማስቀመጥና ተማሪዎች የትኛውን እውቀትና ክህሎት ማዳበር እንዳለባቸው ለማቀድና ለማወቅ ጭምር የሚረዳ በመሆኑ ነው።

## 2.10 ተከታታይ ምዘና እና የቋንቋ ትምህርት

Norris (2000፣19) እንደሚገልጹት የቋንቋ ትምህርት ምዘና በቋንቋ ትምህርት ክፊለ ጊዜያት ላይ አስፈላጊ ተግባራትን ለማከናወን የቋንቋ ፈተናዎችን የመጠቀም ወይም ተግባር ላይ የማዋል ሂደት ነው፡፡ ከተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ውስጥ ፈተናን በተመለከተ Heaton (1990፣11) የክፍል ውስጥ ፈተና ምንጊዜም የማይቀርና የሚተገበር የተከታታይ ምዘና ሂደት አካል ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

Puhl (1997፣4) እንደሚገልፁት የተከታታይ ምዘና ትኩረት የተማሪዎችን ተሳትፎ ወይም ብቃት በሚጠይቁ ተግባራት ላይ ነው፡፡ እነዚህ ተግባራት ደግሞ ተማሪዎች በግል ምን ተማርኩ? ምን ተረዳሁ? የሚለውን ነገር ለመፈተሽ ያስችላቸዋል፡፡ ይህ አይነቱ ሂደት ደግሞ በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ እጅግ ተፈላጊ ነው፡፡ Heaton (1990፣117) በበኩላቸው በመደበኛ ፈተና ዘዴ በትክክል ሊመዘኑ የማይችሉ በርካታ የቋንቋ ክሂሎች አሉ፡፡ የተከታታይ ምዘና እነዚህን ክሂሎች በተሻለ ለማሳየት ወይም ለመፈተሽ ያስችላል በማለት ያስረዳሉ፡፡

በሌላም በኩል በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ አፋቸውን በታላሚው ቋንቋ የፈቱና ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች ይኖራሉ፡፡ በትምህርት፣በኢኮኖሚ ወዘተ ጉዳዮችም የተለያየ ዳራ ይኖራቸዋል፡፡ ስለዚህ ተከታታይ ምዘና በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ በተማሪዎች መካከል የሚፈጠሩ እንደዚህ አይነት ልዩነቶችን ለማቻቻል እና ለማጣጣም የሚያስችል ዘዴ ነው (Puhl፣1997፣15)፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የቋንቋ ትምህርት ዘርፎችን ለማስተማርና ለመመዘን ያገለግላል፡፡

ተከታታይ ምዘና የጽሕፈት ክሂልን ወይም ትምህርትን(Writing Course) ለማስተማርም ሆነ ለመመዘን ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ Heaton (1990፣119) እንደሚያስረዱት ተከታታይ ምዘና የጽህፈት ክሂልን ለመመዘን ከመደበኛውም ሆነ መደበኛ ካልሆነው ፈተና በጣም የተሻለ መሳሪያ ነው፡፡ ምክንያቱም በጽህፈት ተግባር ወቅት ተማሪዎች የጻፉትን ያስተካክሉ ፤ እንደገና ያዋቅራሉ ፤ የተወሰኑ አላስፈላጊ ክፍሎችን ይቀንሳሉ ፤መጨመር ያለባቸውንም ይጨምራሉ፡፡ በአጠቃላይ ሀሳባቸውን በአግባቡ ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ ክሂሎች ወይም ሂደቶች ደግሞ ጥንቃቄ በተሞላበት የክፍል

ውስጥ ክትትል /ምልከታ/ የሚዳብሩ ወይም የሚመዘኑ እንጂ ለመደበኛው ፈተና የሚመቹ ስላልሆኑ ተከታታይ ምዘና ለዚህ ተግባር /Writing task / ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው ።

ከዚህ ጋር በተያያዘ Hughers (1989፣82) የአንድን ቋንቋ ተማሪ የጽሁፍ ችሎታ በክፍል ውስጥ ፈተና ብቻ መለካትና ማወቅ አይቻልም። የጽህፈት ክሂል ቀስ እያለ የሚዳብር በመሆኑ ተማሪዎች በተከታታይ ምዘና ስልት ከአረፍተ ነገር ጀምሮ አንቀጽ ግንባታ ከዚያም ቀስ እያሉ ድርሰት መፃፍ ደረጃ ድረስ በተለያዩ ዘዴዎች ልናለማምዳቸው ይገባል በማለት ያስረዳሉ።

በተጨማሪም Puhl (1997፣4-5) በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ባካሄዱት ጥናት ያገኙትን ውጤት እንዳብራሩት ጥናቱ የትረካ /Narrative/ እና የገለፃ /Discrbtive/ ክሂልን ማደበር ላይ አላማውን መሰረት ያደረገ ጽህፈት ትምህርት /writing course/ በሚወስዱ ተማሪዎች ላይ ያተኩራል። የእነዚህንም ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ የመተረክ እና የመግለጽ ችሎታ ለማደበር ከተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ውስጥ የራስ ምዘና፣ የብጤ ምዘና፣ ሰነደ ትምህርት ፣የመምህሩ ምዘና እና ስራዎቻቸውን እየወጡ ማቅረብ እንዲሁም የሴሚስተር አጋማሽ ፈተና ተግባር ላይ ውለዋል።

በእነዚህም በተጠቀሱት የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች አማካኝነት የተገኘው ውጤት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በታላሚው ቋንቋ በአግባቡ የመተረክና የመግለጽ ክሂላቸው የዳበረና የተሻሻለ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ስለዚህ ከዚህ ተነስተን ይህ ዘዴ ለዚህ የትምህርት ዘርፍ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ መገመት የሚከብድ አይሆንም።

ተከታታይ ምዘና ለስነ-ልሳን ትምህርት ያለውን አስፈላጊነት በተመለከተ Heaton (1990፣68) እንደገለፁት ተከታታይ ምዘና ውስብስብ የሆነውን የስነልሳን ችሎታ ለመለካት የሚያስችል ጥሩ ዘዴ ነው። የስነ-ልሳን ችሎታን የትምህርቱን አላማን ብቻ መሰረት አድርጎ ለመመዘን አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ ለዚህ ችሎታ መለኪያ የሚሆን ግምገማ ስናካሂድ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን መከተል ይኖርብናል። በተጨማሪም Bogale (1994፣26) John stone (1987)'ን በመጥቀስ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን አጠቃላይ የስነ ልሳን ችሎታ ለመመዘን የሚረዳ

ሲሆን የተማሪዎችን ጥረት፣ተነሳሽነት፣አመለካካት እና ሌሎችንም ጨምሮ መጨናነቅ በሌለበት መማሪያ ክፍል ውስጥ ለመመዘን የሚያስችል የምዘና ስልት በማለት ገልጸዋል።

በአጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሱት ገለጻዎች ከቋንቋ ትምህርት ዘርፎች መካከል የስነ-ልሳን በተለይም የጽህፈት ትምህርትን (writing course) በአግባቡ ለማስተማርና ለመመዘን እንዲሁም የትምህርቶችን አላማ ለማሳካት ተከታታይ ምዘና ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ከዚህ አንጻርም ተከታታይ ምዘና ለእነዚህ ትምህርቶች ያለውን ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት እና ትኩረት በመስጠት ተከታታይ ምዘናን የመማር ማስተማሩ ሂደት አካል አድርጎ መተግበር አስፈላጊ ነው።

## 2.11 በተከታታይ ምዘና ሂደት የነጥብ /ማርክ/ መስጫ ዘዴዎች

ተማሪዎች በግል ወይም በቡድን የሚያካሂዱት ምዘና ትክክለኛ እንዲሆን መምህራን መስፈርት አዘጋጅተው ለተማሪዎች መስጠት እንደሚጠበቅባቸው ከላይ ተገልጿል። ለተማሪዎችም ስራዎች ነጥብ /ማርክ/ መስጠት ከመምህራን የሚጠበቅ ተግባር ነው።

መምህራን በተጨባጭ መረጃና እውነታ ላይ ካልተመሰረቱ የነጥብ አሰጣጣቸው በስሜትና ለተማሪዎቻቸው በሚኖራቸው ግላዊ አመለካከት ላይ ብቻ ስለሚመሰረቱ የውጤቱ ተቀባይነት አነስተኛ ሊሆን ይችላል። ታጠቁ እና ሌሎች (1996፣11) መምህራን የነጥብ አሰጣጣቸው ተቀባይነት እንዲኖረው ማስተማር ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ምን ምን እንደሚገመገሙ ካቀዱ ግምገማው ታማኝነት ይኖረዋል። ይህንንም ለማድረግ የእያንዳንዱን የትምህርት ይዘት ወይም ርእስ መሰረታዊ ብቃት ማጤንና የመገምገሚያ ስልቶችን መለየት፣ዝርዝር ብቃቶችን እንዴት መገምገም እንደሚቻል መወሰንና ተማሪው ለእያንዳንዱ መስፈርት ስንት ነጥብ እንደሚሰጠው በቅድሚያ መወሰን እንደሚጠበቅባቸው ይገልጻሉ።

ከ www.equip123.net/.../cA-Practical-Guide-Teachers.Pedf.Similar ድረ-ገጽ የተገኘው መረጃ ደግሞ ለተማሪዎች ምዘና ፍትሀዊ የሆነ ነጥብ ለመስጠት መምህራን የተለያዩ አይነት መልሶችን ለመቀበልና በቅንንት ለማየት ራሳቸውን

በቅድሚያ ማዘጋጀትና ግልጽ ማድረግ እንደሚኖርባቸው፣ እንዲሁም በተከታታይ ምዘና ሂደት አራት የነጥብ መስጫ ዘዴዎች እንዳሉ ይጠቁማል። እነሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

1. የአሰራር ሂደት /Rubric/

ይህ ነጥብ የመስጫ ዘዴ የተማሪዎች ተግባር ብዙ ክፍሎች ሲኖሩትና እያንዳንዳቸውን መመዘን በሚያስፈልግበት ጊዜ የሚያገለግል ነው። ለምሳሌ የተማሪዎች ተግባር በመረጡት ርእሰ ጉዳይ ላይ ከሁለት ገጽ ያልበለጠ ተራኪ ድርሰት መፃፍ ሊሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ መምህሩ የስራውን አጠቃላይ ውጤት ብቻ ሳይሆን ከቃላት አመራረጥ ጀምሮ፣የአረፍተነገር አወቃቀሩን፣የሀሳብ ተያያዥነቱን፣ ፍሰቱን፣ ቀድሞ ከተማሩት ትምህርት ጋር መዛመዱን፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን ነጥቦች ሊያይና ነጥብ ሊሰጥባቸው ይችላል።

መምህራን ይህን ዘዴ በሚጠቀሙበት ጊዜ ከቀረበው ትምህርት ጋር የሚዛመዱ የምዘና ተግባራትን ማዘጋጀት፣በተግባራቱ ውስጥ እንዲታዩ የሚፈለጉትን ዋና ዋና ነጥቦች መለየት፣ለእያንዳንዱ ነጥብ መስፈርት ማዘጋጀት እና ለእያንዳንዱ መስፈርት ነጥብ /ማርክ / መወሰን ይጠበቅባቸዋል።

2. የትንታኔ ዝርዝር /Analytical List/

የትንታኔ ዝርዝር ለተወሰነ የምዘና ተግባር የሚውል ዝርዝር መስፈርት ማለት ነው። መስፈርቱ በተማሪዎች ተግባር ላይ በግልጽ እንዲታዩ የሚጠበቁ የትምህርት ይዘቶችን ያካትታል። ይዘቶቹም እያንዳንዱን መስፈርት ይወክላል።

ይህ ዘዴ ከመጀመሪያው ዘዴ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም ይሄኛው ቀላል እና ምቹ ነው። ምክንያቱም መስፈርቶቹ በቀላሉ ይታወቃሉ። እያንዳንዱ መስፈርት ደግሞ አንድ የትምህርት ይዘት /የትምህርቱ አካል የሆነ አንድ ነጥብ/ ይገልፃል። እንዲሁም የምዘናው ተግባር አሰራር ላይ ሳይሆን ውጤት ላይ ያተኩራል። በዚህ መሰረት ተገቢውን ማርክ መስጠት ነው።

3. ደረጃ መስጠት /Rating Scale/

ደረጃ መስጠት ተማሪዎች በርካታና የተለያዩ መልሶችን እንዲሰጡ ለሚጠበቅባቸው የምዘና ተግባር የሚያገለገል የነጥብ መስጫ ስልት ነው፡፡ የነጥብ መስጫ "ስኬሎቹ" በቁጥር /Numerical/ ወይም በሀተታ /descriptive/ ይገለፃሉ፡፡ የተፈላጊውን ችሎታ ጥራት ወይም ደረጃ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ከመጥፎ እስከ በጣም ጥሩ.... መለኪያ "ስኬል" በመጠቀም ለመመዘን ሁለቱንም መጠቀም ይቻላል፡፡ ነጥብ ሰጪውም አካል ተማሪው በምን ያህል ደረጃ ተፈላጊውን ችሎታ እንደሚያሳይ የሚወክለውን ቁጥር ይመርጣል ወይም ያረጋግጣል፡፡ ትልቁ ቁጥር የችሎታውን ከፍተኛ ደረጃ ሲያመለክት ትንሹ ቁጥር ደግሞ የመጨረሻውን ወይም ዝቅተኛውን ይሆናል፡፡

በጥቅሉ ደረጃ መስጠት ዘዴ በጣም ብዙ ክፍል የሌላቸውን ተግባራት ለመመዘን ይጠቅማል፡፡ በተጨማሪም የአጫጭር ገላፃ እና ትረካ፣ የንባብ ችሎታ፣ የንግግር ችሎታ ወዘተ... ተግባራትን ነጥብ ለመስጠት ያገለግላል፡፡ መምህራን ይህን ስልት ሲጠቀሙ ዘዴውን ለተማሪዎቻቸው ማሳወቅና ማለማመድ አለባቸው፡፡

4. የመቆጣጠሪያ ዝርዝር /Check lists/

በትምህርቱ አላማ መሰረት መመዘን ያለባቸውን ችሎታዎች በዝርዝር በማውጣት ተማሪው ማወቅና አለማወቁን መቻልና አለመቻሉን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስልት ነው፡፡ በዚህ ስልት የሚሰጠው ነጥብ ‹‹አዎ ፣ አይደለም›› ወይም ‹‹አለ ፣የለም›› በሚል ላይ ሊወሰን ይችላል፡፡ ይህ ዘዴ ብዙ ጊዜ የማይወስድ ከትምህርቱ አላማ አንፃር ተማሪዎች የሚጠበቁባቸውን ክሂሎች ማሟላትና አለማሟላታቸውን ለመለየት የሚያስችል ነው፡፡

በጥቅሉ ከላይ ከተዘረዘሩት ነጥቦች ወይም ሀሳቦች የምንገነዘበው መምህራን ግልጽ፣ፍትሀዊ እና ከተማሪዎቻቸው ጋር የሚያግባባ ነጥብ ለመስጠት እንደ ምዘናው ተግባር አይነት እና አላማ የተለያዩ የምዘና ነጥብ መስጫ ዘዴዎችን መጠቀም እና በዋነኝነት ለእያንዳንዱ ምዘና ትክክለኛ መስፈርት አዘጋጅተው መጠቀም እንዳለባቸው ነው፡፡

## 2.12 በተከታታይ ምዘና ሂደት የውጤት አተረጓጐም

የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም የታረመው የተማሪዎች የተግባር ወይም የፈተና ውጤት መረጃ ወይም ትርጉም በሚሰጥ ሁኔታ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ Gronlund (1990፣ 79) እና Gipps (1994፤33) እንደሚገልፁት የውጤት አተረጓጐምን በተመለከተ ሁለት መሰረታዊ ዘዴዎች አሉ፡፡ አንደኛው የተማሪዎችን ውጤት በደረጃ ቅደም ተከተል ሰጥቶ እርስ በርስ በማወዳደር በቡድን ላይ ተመስርቶ የመተርጐም ዘዴ /Norm -referenced/ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የእያንዳንዱን ተማሪ ውጤት ከሌሎች ተማሪዎች ውጤት ጋር ሳይወዳደር በቅድሚያ ከተቀረፁ የውጤት መለኪያ መስፈርቶች ጋር በማነፃፀር የመተረጐም ዘዴ (Criterion-referenced) ናቸው፡፡

በሁለቱ ዘዴዎች መካከል ልዩነቶች እንዳሉ በድሩ (1994፣14) ይገልጻሉ፡፡እርስ በርስ በማወዳደር የመተርጐም ዘዴ /Norm-referenced/ ፈተና ተግባር ጠንካራ ተማሪዎችን ከደካማዎቹ መለየት ስለሆነ መርሀ ትምህርቱን ወይም ስርዐተ ትምህርቱን ሙሉ በሙሉ ላይሸፍንና ከበድ ያሉ ጥያቄዎችንም ሊያካትት ይችላል፡፡ ይህ ዘዴ የራሱ የሆነ ጠንካራ ጎን ቢኖረውም በዚህ ዘዴ የተገለፀን የአንድ ተማሪ ውጤት ከሌሎች ተፈታኞች ውጤት ጋር ተነጻጽሮ ያለበትን ደረጃ ከመጠቆም በስተቀር የተማሪውን የመማር ውጤት በትክክል አያሳይም፡፡ በተጨማሪም ተማሪው በትምህርት አቀባበሉ ላይ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ምን እንደነበሩ ለይቶ አያመለክትም፡፡

በመስፈርት ላይ ተመስርቶ የመተርጐም ዘዴ /Criterion-referenced/ ፈተና ትኩረት የሚያደርገው ስርአተትምህርቱን በሚገባ መሸፈን ላይ ነው፡፡ ፈተናው የግድ ከባድ መሆን አይኖርበትም፡፡ ፈተናውም ሆነ የውጤት መተርጐሚያ ዘዴው ተማሪዎች የአንድን ክፍል ወይም ደረጃ ትምህርት ስለማጠናቀቃቸው ለመመስከር የሚረዳ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ ትክክለኛ መስፈርት ማውጣት አስቸጋሪ ቢሆንም የተማሪዎች ውጤት የሚነጻጸረው ገና ከመነሻው በተቀመጡ ዝርዝር የትምህርት አላማዎችና የማለፊያ ነጥብ ህጎች ወይም መስፈርቶች ጋር በመሆኑ ተማሪው የተፈለገውን እውቀትና ክህሎት መጨበጥ እና ያለመጨበጡን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም የተማሪው ድክመት በየትኛው የትምህርት ይዘት ላይ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡

ስለሆነም መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያካሂዱት ተከታታይ ምዘና ዋና አላማ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረበላቸውን ትምህርት በሚፈለገው መጠን መቅሰማቸውንና አለመቅሰማቸውን፣እንዲሁም የተለያዩ ክሂሎችን፣ ዝንባሌዎችንና አመለካከቶችን እያዳበሩ መሆናቸውን ለመፈተሽ ስለሆነ ክራይቴሪያን-ሪፈረንስድ ዘዴን መጠቀም እንዳለባቸው በድሩ (1994፣15) ይገልጻሉ። በዚህም መምህራን የሚያዘጋጇቸው ፈተናዎች ሁሉንም የትምህርት አላማዎች እንዲያካትቱ ማድረግና ዝቅተኛው የማለፊያ ነጥብ መወሰን ይኖርባቸዋል። ከዝቅተኛው የማለፊያ ነጥብ በታች ለሚያስመዘግቡ ተማሪዎች በየጊዜው የተለያዩ እገዛ ማድረግ ስለሚገባ ይህንን ለማከናወን የሚያስችሉ ስልቶችን መቀየስ እንደሚጠበቅባቸው ጨምረው ገልጸዋል።

ስለዚህ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ውጤት በቁጥር ማስቀመጥ ብቻ ሳይሆን ይሄ ቁጥር ስለተማሪው ምን ምን ነገሮችን ያመለክታል? ምንስ ይጠቁማል? በማለትና ትርጓሜ በመስጠት ለተማሪው መሻሻልና ለመማር ማስተማሩ ሂደት መቃናት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል።

## 2.13 ተከታታይ ምዘና ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ የሚያጋጥሙ ችግሮች

ከላይ ከመግለጽ እንደተሞከረው ተከታታይ ምዘና ለተማሪዎች፣ለመምህራን በአጠቃላይ ለመማር ማስተማር ሂደት የሚኖረው ፋይዳ ላቅ ያለ ነው። ይሁን እንጂ መምህራን ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ የተለያዩ መሰናክሎች ይገጥሟቸዋል።እነዚህም መሰናክሎች በምዘናው በአግባቡ አለመተግበር ወይም ለአላማው አለመሳካት መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ።

መምህራን ተከታታይ ምዘናን የመማር ማስተማሩ ሂደት አካል አድርገው በሚንቀሳቀሱ በት ጊዜ የሚከተሉት ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸው ታጠቁ እና ሌሎች (1996፣7) ይገልጻሉ ። እነዚህም፡-

- በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣
- የልዩ ልዩ መሳሪያዎች አለመኖር ፣
- የመምህሩ የማስተማር ጫና ፣
- የመምህሩ ችሎታ ማነስ፣

- የትምህርቱ አይነት፣
- የትምህርቱ ይዘት ስፋትና ጥበት እና
- አስተዳደራዊ ጉዳዩችና ሌሎችም ናቸው።

በተጨማሪም ስለ ተከታታይ ምዘና እና አተገባበር በቂ የሆነ ስልጠና አለመኖር፣ የተከታታይ ምዘና ዘዴዎችን የማዘጋጀት ችሎታ ወይም ልምድ አለመኖር፣ መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችን ለማዘጋጀትና ተከታታይ ምዘናን ለመተግበር የሚያስችሏቸው የተለያዩ መመሪያዎች (Manuals፣ Guide) በበቂ ሁኔታ አለመኖር፣ መምህራን በስራው ላይ ፍላጎትና ተነሳሽነት አለማሳየት እና የመምህራን በተከታታይ ምዘና ላይ ያላቸው አለመለካካት ለተከታታይ ምዘና አለመተግበር ወይም በትግበራው ወቅት ለችግሮች መፈጠር ምክንያት እንደሆኑ (Desalengn: 2004፣2) ያስረዳሉ።

ከዚህም ባሻገር መምህራን ከግንዛቤ ማነስ የተነሳ ተማሪዎችን በሚመዝኑበት ጊዜ ከተማሪዎች ስህተት ላይ ብቻ ሊያተኩሩ፣ተከታታይ ምዘናውን እንደተከታታይ ፈተና በመቁጠር ሊተገብሩ እና የተማሪዎቻቸውን ውጤት በአግባቡ ላይመዘግቡ ስለሚችሉ የምዘናው አላማ አቅጣጫውን ይስታል። የተማሪዎችም የትምህርት ፍላጎት ይቀንሳል። በሌላም በኩል መምህራን ለተከታታይ ምዘና የሚሆን እቅድ አለማዘጋጀትና የተማሪዎች አመለካከት ወዘተ የመሳሰሉት እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ (Elington and Earl:1997፣7)።

በአጠቃላይ በተከታታይ ምዘና ትግበራ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቋቋም ብሎም ለማስወገድና የተከታታይ ምዘና አተገባበሩን ውጤታማ ለማድረግ የቋንቋ መምህራን ስለ ተከታታይ ምዘና እና ዘዴዎች በቂ የሆነ ስልጠና እና አጋዥ ጽሑፎችን ማግኘት እና ከሌሎች መምህራን ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ አለባቸው። ይህ ካልሆነ ግን ተከታታይ ምዘናን በተፈለገው መንገድ ላይተገብሩት ይችላሉ (Nitko:2004፣47) ።

በሌላም በኩል መምህራን ስልጠናውን አግኝተው ወይም ግንዛቤ ኖሯቸው ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ችግሮች እንቅስቃሴያቸውን ሊገቱ የሚችሉ መሆናቸውን አስቀድመው በመገንዘብ በሂደት እየተፈቱና መፍትሄ እየተገኘላቸው

ጡ የሚችሉ መሆናቸውን በማወቅ ባለመሰላቸትና ተስፋ ባለመቁረጥ መስራት
ቅባቸዋል ሲሉ ታጠቁ እና ሌሎች (1996፤7) ይገልፃሉ።

## የቀደምት ሥራዎች ቅኝት

ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሁለት በአማርኛ እና ሁለት በእንግሊዘኛ ቋንቋ ሩ በድምሩ አራት ጥናቶችን ለመዳሰስ ተሞክሯል።

ጀመሪያው ጥናት በ 1999 ዓ.ም በአልማዝ ሀይሉ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ነው። የጥናቱ ርእስ «አራተኛ ክፍል ያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ» ሲሆን ዋና አላማውም የአንደኛ ደረጃ የመጀመርያ እርከን የአማርኛ ቋንቋ ህራንን ተከታታይ ምዘና አተገባበር መፈተሽ ነው። የጥናቱ ውጤታም ህራንን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ ተከታታይ ን እንደ ተከታታይ ፈተና መስጠት አድርገው በመቆጠር በአግባቡ እየተገበሩት ልሆነ ያስረዳል።

ተኛ ደረጃ የተዳሰሰው ጥናት "የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ አተገባበር ፍተሻ በትግራይ ክልል በሚገኙ ሶስት የመምህራን ትምህርት ች" በሚል እርስ በ2000 ዓ.ም በተስፋ አከለ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ፤የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኮሌጆቹ አሰልጣኝ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ታታይ ምዘና አተገባበርን መመርመር ነው። የተገኘውም ውጤት አሰልጣኝ ርኛ ቋንቋ መምህራን የተለያዩ ስልጠናዎችንና የልምድ ልውውጦችን ያገኙ ሱም የተከታታይ ምዘና እቅድ እንደማያዘጋጁ፤ ከተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ውስጥ ወስኑትን ብቻ እንደሚጠቀሙ፤ የመመዘኛ መስፈርቶችን እንደማያዘጋጁና ፈጣን ጌ ምላሽ እንደማይሰጡ፤ በጥቅሉ ተከታታይ ምዘናን በትክክል እየተገበሩ እንዳል ይገልጻል።

ህ ሁለት ጥናቶች ከእኔ ጋር የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩበት ነጥቦች አሏቸው። ማዝ ሀይሉ ጥናት ከእኔ ጋር የሚያመሳስለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ሳሳይ መሆናቸው ብቻ ነው። ይህም ማለት ምልከታ እና ሰነድ ፍተሻ ዋና

የጽሑፍ መጠየቅ እና ቃለመጠይቅ ደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ልዩነቱ የአልማዝ ጥናት ትኩረት በአንደኛ ደረጃ የመጀመርያ ሳይክል መምህራን ላይ መሆኑና የተከታታይ ምዘና ዘዴዎችን በዝርዝር አለመፈተሹ ነው፡፡

በተጨማሪም የተስፋ አከለ ጥናት አላማ በኮሌጅ ደረጃ ያሉ አሰልጣኝ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን የተከታታይ ምዘና አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡የእኔ ጥናት ግን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በሚያስተምሩ መምህራን ላይ የሚያተኩርና ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን ውስጥ የበሳል ድርሰትና የስነ-ልሳንና ትምህርቶችን የሚያስተምሩ መምህራንን ለይቶ የሚያሳትፍ መሆኑ፣ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ለመምህርነት ሙያ የሚሰለጥኑ አለ መሆናቸው፣ ከተከታታይ ምዘና ገጽታዎች ውስጥ የነጥብ /የማርክ/አሰጣጥና የውጤት አተረጓጎምን ጨምሮ መመርመሩ፣የጽሑፍ መጠይቅ ደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ማገልገሉ እና የቡድን ተኮር ውይይት አለመጠቀሙ ከተስፋ ጥናት የተለየ ያደርገዋል፡፡እንዲሁም ሰነድ ፍተሻ አቢይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ መሆኑ ያመሳስላቸዋል፡፡

ከነዚህ ጥናቶች በተጨማሪ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የቀረበው ሶስተኛው ጥናት እ.አ.አ በ2007 በዘርጋሁን ቻፋሞ የተጠና ነው፡፡ የጥናቱ ርእስ “an investigation into the implementation of continuous assessment by EFL instructors፡ a case of Hosanna College of teacher education” የሚል ሲሆን የጥናቱ አብይ አላማ በተጠቀሰው ኮሌጅ የሚያስተምሩ የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህራንን የተከታታይ ምዘና አጠ ቃቀምን መመርመር ነው፡፡ የጥናቱ ውጤትም የጥናቱ ተተኳሪ ወይም ተሳታፊ መምህ ራን የተከታታይ ምዘና ዘዴዎችን እንደማይጠቀሙባቸው፣ ተከታታይ ምዘናን እን ደ ተከታታይ ፈተና አድርገው በመውሰድ እየተጠቀሙበት እንደሆነና በጥቅሉ ተከታታይ ምዘና በተገቢው መንገድ እየተተገበረ እንዳልሆነ ይገልጻል፡፡

በመጨረሻም የተዳሰሰው ጥናት በታመነ ኦላና እ.አ.አ በ2007 በስርአት ትምህርት ዝግጅት ለሁለተኛ ዲግሪ መሟያነት የቀረበ ነው፡፡ ርእሱም “Factors Affecting the Implementation of Continuous Assessment in Selected Western Oromia Government School Teachers Training College” የሚል ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በተጠቀሰው አካባቢ በመንግስት መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የሚያስተምሩ መምህራን

ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ለማድረግ እንቅፋት የሚሆኑባቸውን ነገሮች መፈተሽ ወይም መለየት ነው። የጥናቱምውጤት የሚያሳየው በተከታታይ ምዘና ዙርያ የመም ህራን በቂ ስልጠና አለማግኘት፣የመምህራንና የተማሪዎች አሉታዊ አመለካከት፣ የመምህ ራን የስራ ጫና እና የተማሪዎች ቁጥር መብዛት ለተከታታይ ምዘና በአግባቡ አለመተግበር እንቅፋቶች መሆናቸውን ነው።

እነዚህ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተሰሩ ሁለት ጥናቶች ስንመለከት የኮሌጅ አሰልጣኝ መምህራን የጥናቶቹ ተሳታፊዎች ወይም ተተኳሪዎች ናቸው። የሁለቱም ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጽሁፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅ ናቸው። ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው አላማቸው የተከታታይ ምዘና አተገባበር መፈተሽ ላይ መሆኑ ነው። ነገር ግን የእኔ ጥናት ተተኳሪዎች በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የሚያስተምሩ መምህራን ሲሆኑ ይህም ሲባል ግን እንደ ታመነ ሁሉንም የትምህርት አይነቶችን የሚያስተምሩ ሳይሆን እንደ ዘርጋሁንም የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህራንን ሳይሆን በአማርኛ ትምህርት ክፍል የስነ-ልሳንና የበሳል ድርሰት ትምህርቶችን የሚያስተምሩ መምህራንን ለይቶ የሚያሳትፍ በመሆኑና ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ምልከታና ሰነድ ፍተሻ መሆናቸው ከእነዚህ ጥናቶች የተለየ ያደርገዋል።

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በደብረብርሃን እና በወሎ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ትምህርት ክፍሎች የበሳል ድርሰትና የስነ-ልሳን ትምህርቶችን የሚያስተምሩ መምህራንን የተከታታይ ምዘና አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ ለጥናቱ የሚሆን መረጃ ለማግኘት አይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴዎች በቅንጅት ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ በምልከታና እና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በአሀዛዊ ስሌት ስለተተነተኑ አሀዛዊ የምርምር ዘዴን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ከቃለ መጠይቅ እና ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ደግሞ በገለፃ ስለተተነተኑ አይነታዊ የምርምር ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

## 3.1 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች

የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ምንጮች በደብረብርሃን እና በወሎ ዩኒቨርሲቲዎችበአማርኛ ትምህርት ክፍሎች  የበሳል ድርሰትና የስነ-ልሳን ትምህርቶችን የሚያስተምሩ መምህ ራን፣ እነዚህን ትምህርቶች የተማሩ ወይም በመማር ላይ ያሉ የሁለተኛ እና የሦስተኛ አመት የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች እና የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ሰነዶች ናቸው፡፡

## 3.2 የናሙና አመራረጥ

### 3.2.1 የዩኒቨርሲቲዎች አመራረጥ

በአሁኑ ሰዓት በሀገራችን በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የደብረብ ርሃን እና የወሎ ዩኒቨርሲቲዎች ለዚህ ጥናት ተመርጠዋል፡፡ እነዚህ ሁለት ዩኒቨርሲቲዎች በወሳኝ ናሙና ስር የሚገኘውን አመቺ የናሙና ዘዴ በመጠቀም የተመረጡ ናቸው፡፡ ይህን ዘዴ መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት ከጊዜ፣ ከገንዘብ እና ከአቅም ውስንነት አንፃር ሁሉንም ዩኒቨርሲቲዎች በጥናቱ ማካተት ስለማይቻል እና አጥኚዋ ዩኒቨርሲቲዎቹ ያሉበትን አካባቢ ከማወቅ አንፃር መረጃ ለመሰብሰብ አመቺ ሆነው በመገኘታቸው ነው፡፡

### 3.2.2 የመምህራን አመራረጥ

በተመረጡት ሁለት ዩኒቨርሲቲዎች በአማርኛ ትምህርት ክፍል ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት የበሳል ድርሰትና የስነ-ልሳን ትምህርቶችን የሚያስተምሩ መምህራን ቁጥር አራት ስለሆነ በወሳኝ ናሙና ስር የሚገኘውን ጠቅላይ የናሙና ዘዴን በመጠቀም ሁሉም መምህራን ተመርጠዋል፡፡ የእነዚህም መምህራንን አጠቃላይ መረጃ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ፡ 1. በሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑትን መምህራን አጠቃላይ መረጃ የሚያሳይ ሠንጠረዥ**

| የዩኒቨርሲ. ቲው ስም | የመምህራን ብዛት | | የትምህርት ደረጃ | | የአገልግሎት ዘመን | | የሳምንት ክፍለ ጊዜ ብዛት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የበሳል ድርሰት መምህራን | የሥነ-ልሳን መምህራን | የመጀመሪያ ድግሪ | ሁለተኛ ድግሪ | ጀማሪ | ሁለት አመት | ዘጠኝ | አስራ ሁለት |
| ደብረብርሃን | ወ - | ወ 1 | - | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| | ሴ 1 | ሴ - | - | | | | | |
| ወሎ | ወ 1 | ወ 1 | - | 2 | - | 2 | - | 2 |
| | ሴ - | ሴ - | - | | | | | |
| ድምር | 2 | 2 | | | | | | |

ሠንጠረዥ 1 እንደሚያሳየው ከደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ሁለት ከወሎ ሁለት በድምሩ አራት መምህራን የጥናቱ ተሳታፊ ናቸው፡፡ ሁሉም በሁለተኛ ዲግሪ የሰለጠኑ ሲሆኑ ከነዚህም መካከል ሦስቱ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ዘዴ፣ የወሎ ዩኒቨርሲቲ የሥነ-ልሳን መምህር ደግሞ በገላጭ እና በንድፈ-ሀሳባዊ ስነ-ልሳን (Descriptive and Theoretical Linguistics)ን አጥንተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሦስቱ መምህራን በያሉበት ዩኒቨርሲቲ ሁለት ሁለት አመት ያገለገሉ ሲሆን የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የበሳል ድርሰት መምህር ግን ለዩኒቨርሲቲው ጀማሪ መምህር ናቸው፡፡ በሳምንት የሚያስተምርቱን የክፍለ ጊዜ ብዛት ስንመለከት ደግሞ የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የበሳል ድርሰት መምህር ብቻ በሳምንት ዘጠኝ ክፍለ ጊዜያት ሲያስተምሩ ቀሪዎቹ መምህራን በሙሉ በሳምንት አስራ ሁለት ክፍለ ጊዜያትን ያስተምራሉ፡፡ እንዲሁም ከጥናቱ ተሳታፊ መምህራን መካከል የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የሥነ-ልሳን እና የወሎ ዩኒቨርሲቲ የበሳል ድርሰት መምህራን ከማስተማር ስራው በተጨማሪ የትምህርት ክፍሉ ሊቀመንበር በመሆን ያገለግላሉ፡፡

በአጠቃላይ የመምህራን ዳራዊ መረጃ የሚያስረዳው በመምህራኑ መካከል በትምህርት ደረጃ፣ በአገልግሎት ዘመን እና በሳምንት በሚያስተምሩት የክፍለ ጊዜ ብዛት በኩል የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ነው፡፡

### 3.2.3 የተማሪዎች አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጡት ተማሪዎች በሁለቱ ዩኒቨርሲቲናዎች በአማርኛ ትምህርት ክፍል የሚሰጡ የበሳል ድርሰትና የሥነ-ልሳን ትምህርቶችን እየወሰዱ ያሉ ወይም የወሰዱ የሁለተኛ እና የሦስተኛ ዓመት ተማሪዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት ጥናቱ የሚያተኩረው የተጠቀሱትን ትምህርቶች በሚያስተምሩ መምህራን ላይ በመሆኑ እና ለተማሪዎች የሚቀርቡትም ጥያቄዎች በዚሁ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ በመሆናቸው ነው፡፡ የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች በጥናቱ ውስጥ አልተካተቱም፡፡ ምክንያቱም በደብረብረሃን ዩኒቨርሲቲ ገና ትምህርቱን በመጀመር ላይ በወሎ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ በመመዝገብ ላይ ስለነበሩ ነው፡፡

ለተማሪዎች መረጣ የነሲብ ዕጣ ናሙና ዘዴ /Simple Random Sampling/ ተግባር ላይ ውሏል፡፡ ይህም ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ከጊዜ እና ከገንዘብ ውስንነት አንፃር ሁሉንም ተማሪዎች ማሳተፍ የማይቻል በመሆኑ እና ጥናቱ ውስጥ እንዲካተቱ ለታሰቡት ተማሪዎች እኩል የመመረጥ እድል እንዲኖራቸው ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡

በመሆኑም በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ አመት ተማሪዎች 140፣ የሦስተኛ አመት ተማሪዎች 61 በድምሩ 201 ተማሪዎች ሲገኙ፣ በወሎ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ አመት ተማሪዎች 86 ፣የሦስተኛ አመት ተማሪዎች 111 በድምሩ 197 ሲገኙ በአጠቃላይ ከሁለቱም ዩኒቨርሲቲዎች 398 ተማሪዎች ተገኝተዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 50 ተማሪዎች በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ መረጃ የሰጡ ተማሪዎችም አጠቃላይ መረጃ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ:2. የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎችን አጠቃላይ መረጃ የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| የዩኒቨርሲቲው ስም | የሁለተኛ አመት ተማሪዎች ብዛት | | | የሶስተኛ አመት ተማሪዎች ብዛት | | | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | |
| ደብረብርሃን | 10 | 6 | 16 | 2 | 5 | 7 | 23 |
| ወሎ | 6 | 4 | 10 | 9 | 6 | 15 | 25 |
| ድምር | 16 | 10 | 26 | 11 | 11 | 22 | 48 |

ከሠንጠረዥ 2 ማየት እንደሚቻለው ከደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ወንድ 12 ፣ሴት 11 በድምሩ 23 ተማሪዎች ለጥናቱ መረጃ የሰጡ ሲሆን ፣ ሁለት የሁለተኛ አመት ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቁን በትክክል ባለመሙላታቸው ከጥናቱ ውጭ ሆነዋል:: ከወሎ ዩኒቨርሲቲ መረጃ የሰጡት ወንድ 15 ፣ሴት 10 በድምሩ 25 ሲሆኑ ከሁለቱም ዩኒቨርሲቲዎች 48 ተማሪዎች መረጃ ሰጥተዋል::

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ለዚህ ጥናት የሚሆን መረጃ ለመሰብሰብ ያገለገሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምልከታ፣ የሰነድ ፍተሻ፣ ቃለ መጠይቅና የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው:: ምልከታ እና ሰነድ ፍተሻ በዋነኝነት ያገለገሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሲሆኑ በእነዚህ አማካኝነት የተገኙ መረጃዎችን ለማጠናከር ደግሞ ቃለ መጠይቅና የጽሁፍ መጠይቅ በደጋፊነት አገልግለዋል::

የቃለ መጠይቁና የጽሁፍ መጠይቁ ጥያቄዎች እና የምልከታና የሰነድ ፍተሻ ማረጋገጫ ዝርዝሮች /Cheek List/ በጥናቱ አማካሪ እና በዘርፉ ባለሙያ ተገምግመው፣ ማስተካከያ ከተደረጉባቸው በኋላ ተግባር ላይ የዋሉ ናቸው::

### 3.3.1 የክፍል ውስጥ ምልከታ

በዚህ ጥናት የክፍል ውስጥ ምልከታን ለማከናወን አስራአንድ ነጥቦችን የያዘ ማረጋገጫ ዝርዝር /Check list/ ተግባራዊ ተደርጓል:: ምልከታው የተካሄደው በሁለቱም ዩኒቨርስቲዎች ከስነ-ልሳን ትምህርቶች ውስጥ በወቅቱ ለሁለተኛ አመት ተማሪዎች ሲሰጥ በተገኘው በአማርኛ አገባብ (Amharic syntax) እና ከበሳል ድርሰት ትምህርቶች ደግሞ ለሦስተኛ አመት ተማሪዎች ሲሰጥ በነበረው በአማርኛ በሳል የፅህፈት ክሂል (Amharic Advanced Writing skill) ትምህርቶች ላይ ነው::

በሌላ አገላለፅ ከሁለቱም ዩኒቨርሲቲዎች ሁለት የስነ-ልሳንና ሁለት የበሳል ድርሰት በድምሩ በጥናቱ የተሳተፉት አራቱም መምህራን በምልከታው ተፈትሸዋል:: በምልከታው አንድ መምህር ሦስት ጊዜ ሲታይ አራቱ መምህራን አስራ ሁለት ጊዜ ታይተዋል:: አንዱ የምልከታ ጊዜ 50 ደቂቃ የፈጀ ሲሆን ሁሉንም የምልከታ ክንውን ለማጠናቀቅ አስር ሰአት ፈጅቷል ::

### 3.3.2 የሠነድ ፍተሻ

ሰነድ ፍተሻ ለጥናቱ የሚሆኑ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ስራ የዋለ የጥናቱ አቢይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው:: በዚህ ዘዴ የተለያዩ የተከታታይ ምዘና እቅዶች ፣የኮርስ ቢጋሮች፣ ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት ያከናወኗቸው የግልና የቡድን ስራዎች ፣ፈተናዎች ፣ስነደትምህርት፣ የተማሪዎች የትምህርት ሁኔታ መከታተያ መዝገብ እና የውጤት ማጠራቀሚያ ቅፆች ተፈትሸዋል:: ከእነዚህ ሰነዶች ፍተሻ የተገኘው መረጃ ከምልከታ፣ ከቃለ መጠይቅና ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን ለማረጋገጥ አግዟል::

### 3.3.3 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ ለዚህ ጥናት ደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሲሆን የቀረበውም ለጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ነው:: የመምህራን ቃለ መጠይቅ በተከታታይ ምዘና ዙሪያ የመምህራንን ግንዛቤ ለማወቅ እና በክፍል ውስጥ ምልከታና በሰነድ ፍተሻ የታዩትን ተግባራት ለማረጋገጥ ወይም ለማጠናከር መረጃ ተሰብስቦበታል::

ለመምህራን የቀረቡት ቃለ መጠይቆች በክለሳ ድርሳን ላይ ስለተከታታይ ምዘና የተነሱትን ዋና ዋና ሀሳቦች መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው:: መጠይቆቹ የመምህራንን ዳራ የሚመለከቱ እና በተከታታይ ምዘና አተገባበር ዙሪያ የሚያጠነጥኑ አስራ አምስት ልቅ ጥያቄዎች ይዘው ተደራጅተዋል:: ለዚህም መቅረፀ ድምፅ ተግባር ላይ ውሏል:: ነገር ግን ድምፃቸው እንዲቀረፅ ፍቃደኛ የሆኑት ሁለቱ መምህራን ብቻ ናቸው:: የሌሎቹን ምላሽ በማስታወሻ ለማያዝ ተሞክሯል::

### 3.3.4 የፅሁፍ መጠይቅ

ይህ የመረጃ መስብሰቢያ ዘዴ ሌላኛው የጥናቱ አጋዥ መሳሪያ ነው:: የፅሑፍ መጠይቁ የቀረበው ለተማሪዎች ሲሆን የተዘጋጀውም ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎችን መሠረት በመድረግ ነው:: ለተማሪዎች የቀረበው መጠይቅ በሦስት

ክፍሎች ተደራጅቷል፡፡ የመጀመሪያው የተማሪዎችን አጠቃላይ መረጃ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው የስምምነት ስኬሎችን በማቅረብ ተማሪዎች የሚስማሙበትን እንዲመርጡ የሚያደርግና አስራ አምስት ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህ የስምምነት ስኬሎች በጣም እስማማለሁ 5 ፣ እስማማለሁ 4፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል 3፣ አልስ ማማም 2 እና በጣም አልስማማም 1 በሚሉ ቁጥሮች ተወክለዋል፡፡ ሦስተኛው አስር የተከታታይ ምዘና ስልቶች ቀርበው ተማሪዎች እንደመምህሮቻቸው አጠቃቀም ቅደም ተከተል እንዲያስዙ የሚያደርግ እንዲሁም ሁለት ዝግና ሁለት ልቅ ጥያቄዎች የቀረቡበት ነው፡፡

ለተማሪዎች ገለፃ ለመስጠትና በአግባቡ መረጃ ለመሰብሰብ ሲባል በተተኳሪ መምህራን ትምህርት ክፍለ ጊዜያት ማብቂያ ላይ አጥኚዋ በተገኘችበት የተመረጡ ተማሪዎች መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ በሁለቱም ዩኒቨርሲቲዎች ከተሰራጩ 50 የፅሁፍ መጠይቆች ውስጥ 48ቱ በትክክል ተሞልተው ሲመለሱ ከደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲዎች ሁለት መጠይቆች በትክክል ስላልተሞሉ ከጥናቱ ውጪ ተደርገዋል፡፡

## 3.4 የመረጃ አሰባሰብ ቅደም ተከተል

ከላይ እንደተገለጸው ለዚህ ጥናት ያገለገሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምልከታ፣የሰነድ ፍተሻ፣ ቃለ መጠይቅና የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ ትክክለኛና አስተማ ማኝ መረጃ ለመሰብሰብ ሲባል ምልከታው በመጀመሪያ ተካሂዷል፡፡ ከዚያም በምልከታው የተገኙትን መረጃዎች ለማጠናከር ወይም ለማመሳከር ለመምህራን ቃለ መጠይቅ ተደርጓል፡፡ ከመምህራን በመቀጠል ተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቁን ሞልተዋል፡፡ በመጨረሻም የተለያዩ ሰነዶች ከመምህራንና ከአማርኛ ከትምህርት ክፍል በመውሰድ የተለያዩ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን ስልት

በዚህ ጥናት የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተን አይነታዊና ገላጭ ስታቲክስ የመረጃ አተናተን ስልት ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ ለተማሪዎች ከቀረቡ የፅሁፍ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች ገላጭ ስታቲክስ የመረጃ አተናተን ዘዴን በመጠቀም የተተነተኑ ሲ ሆን ከመምህራን ቃለ መጠይቅ፣ ለተማሪዎች ከቀረቡ ልቅ ጥያቄዎች፣ ከምልከታና ከሰነ ድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ደግሞ አይነታዊ የመረጃ አተናተን ዘዴን በመጠቀም ለመተ ንተን ተሞክሯል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተና

በዚህ ምዕራፍ የበሳል ድርሰትና የስነ-ልሳን መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ምንነት፣ ባህሪ እና ጠቀሜታ ያላቸውን ግንዛቤ፣ ስለሚጠቀሙባቸው የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች፣ ስለምጋቤ ምላሽ አሰጣጣቸው ሁኔታ፣ ስለ ነጥብ አሰጣጣቸው እና ውጤት አተረጓጐማቸው እንዲሁም የተከታታይ ምዘና ሰነድ አያያዛቸውን በተመለከተ ከምልከታ፣ ከሰነድ ፍተሻ፣ ከቃለ መጠይቅ እና ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው እንደሚከተለው ቀርበዋል::

### 4.1 መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ያላቸውን ግንዛቤ በሚመለከት ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

#### 4.1.1 ስለ ተከታታይ ምዘና ምንነት የመምህራን ግንዛቤ

በጥናቱ አላማ መሰረት ተተኳሪ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ምንነት ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ወይም ለመፈተሽ ቃለ መጠይቅ ተካሂዷል:: በዚህ መሠረት በቃለ መጠይቁ መጀመሪያ "በእርስዎ አመለካከት ተከታታይ ምዘና ማለት ምን ማለት ነው?" የሚል ጥያቄ ቀርቧል:: ለዚህም ጥያቄ አራቱም መምህራን (100%) ተከታታይ ምዘና በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ትምህርቱን መረዳታቸውንና አለመረዳታቸውን ለማወቅ፣ በማስተማሩ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ወይም ለማሻሻል እና የተለያዩ ድጋፎችን ለመስጠት የሚያስችል የምዘና ዘዴ እንደሆነ ገልፀዋል:: አክለውም ተከታታይ ምዘና በተለያዩ ዘዴዎች ማለትም ከክፍል ውስጥ የቃል ጥያቄ ጀምሮ፣ በምልከታ፣ በግልና የቡድን ስራ፣ በተለያዩ ሙከራዎችና ፈተናዎች፣ወዘተ. የሚደገፍ፣ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ሊተገበር የሚችል እና የመማር-ማስተማሩ ሂደት አካል እንደሆነ ገልፀዋል::

ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለው ሁሉም ተጠኚዎች ስለተከታታይ ምዘና ምንነት ያላቸው ግንዛቤ ተመሳሳይ እና ምዕራፍ ሁለት ላይ ስለተከታታይ ምዘና ምንነት ከተጠቀሰው የምሁራን ብያኔ አንፃር ጥሩ መሆኑን ነው:: በማስከተል የቀረበላቸው

ጥያቄ «በተከታታይ ምዘና አተገባበር ዙሪያ ያገኙት ስልጠና አለ? ካለ ስልጠናውን እንዴት ሊያገኙ ቻሉ?» የሚል ነው፡፡

ለቀረበው ጥያቄም ሁሉም (100%) የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ተከታታይ ምዘናን በሚመለከት ስልጠና ማግኘታቸውን ገልፀዋል፡፡ ስልጠናውን ያገኙበት መንገድ ደግሞ ሦስቱ መምህራን በከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም (HDP) አማካኝነት፣ አንደኛዋ የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ጀማሪ መምህር ከማስተማር በፊት በሚሰጠው የአምስት ቀን ስልጠና አማካኝነት በተከታታይ ምዘና አተገባበር እና በሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎች ዙሪያ ስልጠና ማግኘታቸውን አስረድተዋል፡፡

ከጥያቄው ምላሽ የምንረዳው ተጠኚ መምህራን በሙሉ በከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም እና ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት በሚሰጠው የአምስት ቀን ስልጠና አማካኝነት ስለ ተከታታይ ምዘና ምንነትና አተገባበር ስልጠና ማግኘታቸውን እና ይህም ስልጠና ተጠኚዎቹ ስለ ተከታታይ ምዘና ምንነት ተመሳሳይና ጥሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማስቻሉን ነው፡፡

### 4.1.2 ስለተከታታይ ምዘና አስፈላጊነት እና ጠቀሜታ የመምህራን ግንዛቤ

ጥያቄ ቁጥር (3) ላይ "እርስዎ ለሚያስተምሩት ትምህርት /course/ ተከታታይ ምዘና የሚያገለግል ወይም አስፈላጊ ይመስለዎታል?" የሚል ጥያቄ ለተተኳሪ መምህራን ቀርቧል፡፡ ለዚህም ጥያቄ አራቱም መምህራን (100%) 'አዎ በትክክል አስፈላጊ ይመስለኛል' በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የቀረበላቸው ጥያቄ «ከመሰለዎት በሚያስተምሩት ትምህርት ላይ ይተገብሩታል?» የሚል ሲሆን ለጥያቄውም ሦስቱ መምህራን (75%) በሚያስተምሩት ትምህርት ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ እንደሚያደርጉ አስረድተዋል፡፡ አንደኛው ብቻ ተከታታይ ምዘናን የምተገብረው በመጠኑ ወይም በተወሰነ ደረጃ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ ለዚህም ምክንያታቸውን ሲያስረዱ ከማስተማር በተጨማሪ ሌሎች የስራ ጫናዎች ስላሉብኝ ከጊዜ አንፃር ትምህርቱን መጨረስ ላይ ትኩረት አደርጋለሁ ብለዋል፡፡ ስለዚህ ይህ ምላሽ ሁሉም ተጠኚ መምህራን ተከታታይ ምዘና ለሚያስተምሩት ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን እንደሚያምኑ ወይም እንደሚያውቁ ያስረዳል፡፡

በተጨማሪም የተከታታይ ምዘናን ጠቀሜታ በሚመለከት ለመምህራን የቀረበው ጥያቄ ተራ ቁጥር (8) "ተከታታይ ምዘና ከተለምዷዊው ፈተና (ከማጠቃለያ ፈተና) በተሻለ ሁኔታ ለርሰዎም ሆነ ለተማሪዎች የሚያስገኘው ጠቀሜታ አለ? ካለ ይዘርዝሩ?" የሚል ነው፡፡ ለዚህም ጥያቄ ሁሉም ተጠኚዎች 'አዎ ተከታታይ ምዘና ከተለምዶዊው ምዘና በተሻለ መልኩ የተለያዩ ጠቀሜታዎች ያስገኛል' በማለት መልሰ ዋል፡፡የጠቀሷቸውም ጠቀሜታዎችም የሚከተሉት ናቸው፡-

- በተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በየጊዜው የሚገመገሙና የሚታዩ በመሆኑ ተማሪ ዎች በራስ በመተማመን መንፈስ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ፣ እንዲጠይቁ፣ ፍርሀትን እንዲያስወግዱ እና የማፍለቅ ችሎታቸው እንዲዳብር ያግዛል፡፡
- የማስተማር እና የግምገማ ዘዴን ለማስተካከል፣ ለተማሪዎች አፋጣኝ የሆነ ምላሽ ለመስጠት እጅግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡
- ከተማሪዎች አዳዲስ ነገር ለማግኘት ይረዳል፡፡
- ተማሪዎች ብዙ እንዲያነቡ እርስ በርስ እንዲግባቡ፣ ልምድ እንዲለዋወጡ እና ዘና ብለው እንዲማሩ ያደርጋል፡፡
- ተማሪዎች የትምህርቱን አላማ በግልፅ እንዲረዱ ያስችላል፡፡ ለመምህሩም የትምህርቱን ይዘት ለመሸፈንና አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት ያስችላል፡፡

ይህ ምላሽ ምእራፍ ሁለት 2.5 ላይ ከተጠቀሱት የተከታታይ ምዘና ጠቀሜታዎች ጋር የሚጣጣም ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን በሙሉ የተከታታይ ምዘና ጠቀሜታን በተመለከተ ጥሩ ግንዛቤ እንዳላቸው ያስረዳል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ ጥያቄ ቁጥር (13) ላይ "በማስተምረው ትምህርት ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረጌ ተማሪዎች የታለሙ ክሂሎችን ማዳበር ችለዋል ብለው ያስባሉ? ያብራሩ?" የሚል ጥያቄ ተጠይቀው የደብረብርሃን ተጠኚዎች (50 %) ትምህርቱን ባንጨርሰውም ባለንበት ሁኔታ ተማሪዎች የታለሙ ክሂሎችን እያዳበሩ ነው በማለት ሲገልፁ፣የወሎ ዩኒቨርሲቲ መምህራን (50 %) ደግሞ ሙሉ በሙሉ ተማሪዎች የታለሙ ክሂሎችን ማዳበር ችለዋል ለማለት ባያስደፍርም የተወሰነ ለውጥ ግን አለ በማለት አስረድተዋል፡፡ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘውን ውጤት ለማረጋገጥ ለተማሪዎች ይህን የተመለከተ ጥያቄ ቀርቧል፡፡ የተገኘውም ምላሽ እንደሚከተለው ነው፡፡

ሠንጠረዥ፡3. የተከታታይ ምዘና ጥቅምን በተመለከተ ከፅሁፍ መጠይቅ የተማሪዎችን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ጥያቄ | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | ለመወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | |
| | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % |
| 13. መምህራን በተለያየ ጊዜ በሚሰጡን የተለ ያዩ የምዘና ተግባራት ምክንያት ትምህርቱን በአግባቡ መረዳት ችለናል:: | 18 | 48 | 16 | 33.33 | 8 | 16.6 | 3 | 6.25 | 3 | 6.25 |

ም ሠንጠረዥ 3መ ላይ እንደተገለፀው ለጥያቄ ቁጥር (13) 48% ተማሪዎች "በጣም እስማማለሁ" የሚለውን አማራጭ መልስ ሲመርጡ፣ 33.33% የሚሆኑት "እስማማለሁ" ሲሉ፣ 16.6% ተማሪዎች ደግሞ "ለመወሰን ያስቸግረኛል" የሚለውን አማራጭ መልስ መርጠዋል:: የቀሩት 6.25% "አልስማማም" እና 6.25% "በጣም አልስማማም" በማለት መልሰዋል:: ይህ ውጤት ሙሉ በሙሉ ባይሆንም አብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች መምህሮቻቸው በሚሰጧቸው የተለያዩ የምዘና ተግባራት አማካኝነት ትምህርቱን በመረዳት ረገድ ጠቀሜታ ማግኘታቸውን እና ተተኳሪ መምህራን የተከታታይ ምዘናን ጠቀሜታ መረዳታቸውን ያሳያል:: ይህም የተማሪዎች ምላሽ ውጤት ከመምህራን ምላሽ ጋር የሚጣጣም ሆኖ ተገኝቷል::

## 4.2 የተከታታይ ምዘና እቅድ እና የኮርስ ቢጋር ዝግጅትን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.2.1 ስለመምህራን ተከታታይ ምዘና እቅድ እና የኮርስ ቢጋር ዝግጅት ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ

የተከታታይ ምዘና እቅድ አዘገጃጀትን በሚመለከት የተጠኚ መምህራንን ሰነዶች ለማየት ወይም ለመፈተሸ ተሞክሯል:: ነገር ግን አንድም የተከታታይ ምዘና እቅድ ማግኘት አልተቻለም:: በዚህም መሰረት ሁሉም መምህራን (100%) የተከታታይ ምዘና እቅድ አዘጋጅተው እንደማይጠቀሙ ማረጋገጥ ተችሏል::

በተጨማሪም በተተኳሪ መምህራን ኮርስ ቢጋር ዝግጅት ላይ ፍተሻ ለማድረግ በቅድሚያ የሁሉንም መምህራን ኮርስ ቢጋር በቀላሉ ከመምህራኑ ማግኘት ተችሏል:: በተደረገውም ፍተሻ ሁሉም መምህራን የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን እና ምዘናዎቹ ከምን ያህል ፐርሰንት እንደሚያዙ በኮርስ ቢጋራቸው ላይ አስፍረዋል:: ነገር ግን የእያንዳንዱ የምዘና ተግባር አላማ እና ከአንድ የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህር በስተቀር ምዘናዎቹ የሚሰጡበት ጊዜ አልተገለፀም :: (አባሪ ስምንት እና ዘጠኝን ይመልከቱ)::

## 4.2.2 ስለተከታታይ ምዘና እቅድ እና የኮርስ ቢጋር ዝግጅት የመምህራን ምላሽ

ጥያቄ ቁጥር (4) ላይ "የተከታታይ ምዘና እቅድ እና የኮርስ ቢጋር አዘጋጅተው ይጠቀማሉ?" ተብሎ በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረት ሁሉም መምህራን (100%) የተከታታይ ምዘና እቅድና ኮርስ ቢጋር አዘጋጅተው እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል:: ከዚህ ጋር በተያያዘም "እነዚህን ነገሮች አዘጋጅተው የሚጠቀሙ ከሆነ በእቅድዎና በኮርስ ቢጋርዎ ውስጥ የምዘና ተግባራትን አላማ፣ ዘዴ እና ጊዜ በግልፅ ይዘረዝራሉ?" የሚል ጥያቄ ተጠይቀው (75%) የሚሆኑት መምህራን በእቅዳቸውና በኮርስ ቢጋራቸው የምዘና ተግባራትን አላማ፣ዘዴና ምዘናዎቹ የሚሰጡበትን ጊዜ በግልፅ ዘርዝረው እንደሚያካትቱ አስረድተዋል:: አንደኛው መምህር (25%) ብቻ የኮርስ ቢጋሩን ባዘጋጅም የተጠቀሱትን ጉዳዮች በሙሉ አላካትትም በማለት ገልፀዋል::

የዚህ ምላሽ ውጤት ተተኳሪ መምህራን የተከታታይ ምዘና እቅድ አዘጋጅተው እንደሚጠቀሙ ቢገልፅም ከላይ በ(4.2.1) ሰነድ ፍተሻ ውጤት እንደተገለፀው ሁሉም መምህራን ይህ ሰነድ እንደሌላቸው ወይም አዘጋጅተው እንደማይጠቀሙ ማረጋገጥ ተችሏል::

ይህን በሚመለከት ምእራፍ ሁለት 2.7 ላይ በተጠቀሰው የምሁራን ሃሳብ መሰረት ተከታታይ ምዘናን በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ መሟላት ከሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች መካከል የተከታታይ ምዘና እቅድ ማዘጋጀት አንዱና ዋነኛው ነው:: መምህራን ባላቸው ግንዛቤ ወይም እውቀት መሰረት ምዘናው መቼ፣ እንዴትና በምን አይነት ዘዴ እንደሚካሄድ በዝርዝር ከወዲሁ ሊያውቁ ይገባል:: ነገር ግን

ተጠኚ መምህራን የተከታታይ ምዘና እቅድ አዘጋጅተው እንደሚጠቀሙ ቢገልፁም በሰነድ ፍተሻ የተገኘ ማረጋገጫ ባለመኖሩ የተጠኚ መምህራን ምላሽ ውጤት ከንድፈ ሀሳቡ ጋር የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም፡፡

### 4.2.3 ስለመምህራን የኮርስ ቢጋር ዝግጅት ከፅሁፍ መጠይቅ የተማሪዎች ምላሽ

የኮርስ ቢጋር ዝግጅትን በሚመለከት ከጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የተገኘውን ምላሽ ወይም ውጤት ለማረጋገጥ ለተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ቀርቧል፡፡ ከእዚህም የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

**ሠንጠረዥ ፡4. ስለመምህራን የኮርስ ቢጋር ዝግጅት የተማሪዎችን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| ጥያቄ | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | ለመወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | |
| | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1. መምህራን የሚሰጡን የኮርስ ቢጋር የተከታታይ ምዘና ተግባራትን አላማ፣ ዘዴና ጊዜን ያካተተ ነው፡፡ | 30 | 62.5 | 13 | 27.08 | 4 | 8.33 | 1 | 2.08 | - | - |

ሰንጠረዥ4 እንደሚያሳየው በጥያቄ ቁጥር አንድ ለቀረበው ሀሳብ አብዛኛው (62.5%) ተማሪዎች "በጣም እስማማለሁ"፣ 27.08% ተማሪዎች "እስማማለሁ" በማለት ሲመልሱ፣ 8.33% የሚሆኑት ደግሞ "ለመወሰን ያስቸግረኛል" እና አንድ 2.08% ተማሪ "አልስማማም" በማለት መልሰዋል፡፡

ይህ ውጤት የሚያመለክተው የበሳል ድርሰት እና የስነ-ልሳን መምህራን የሚያዘጋጇቸው የኮርስ ቢጋሮች የተከታታይ ምዘና ተግባራትን አላማ፣ ዘዴንና ምዘናዎቹ የሚሰጡበትን ጊዜ ያካተቱ መሆናቸውን ነው፡፡ በተጨማሪም ተጠኚ መምህራን በቃለ መጠይቅ ከሰጡት ምላሽ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ጥቂት ተማሪዎች ለመወሰን የተቸገሩት የኮርስ ቢጋሮቹ የምዘና ዘዴዎቹን ብቻ የያዙ ወይም የሚሰጡበትን ዓላማና ጊዜ የማይገልፁ ሆነው ሊሆን ይችላል፡፡ በሰነድ

ፍተሻውም የተገኘው ውጤት ከተማሪዎችና ከመምህራን ምላሽ ጋር የሚጣረስ ነው፡፡ ይህም ሲባል መምህራን በሚያዘጋጁቸው ኮርስ ቢጋሮች ውስጥ የተለያዩ የምዘና ዘዴዎች ቢጠቀሱም እያንዳንዱ ምዘና የሚሰጥበት አላማ እና ጊዜ በግልፅ አልተቀመጠም፡፡ ይህ ደግሞ ተከታተይ ምዘናን በአግባቡ ለመተግበር ግልፅ የሆነ እቅድ ማቀድና ለተማሪዎችም ማሳወቅ ይገባል ከሚለው የምሁራን ሀሳብ ጋር አብሮ የማይሄድ ነው፡፡

## 4.3 የተከታታይ ምዘና ስልቶችን አጠቃቀም በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.3.1 ስለመምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶች አጠቃቀም ከክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኙ መረጃዎች

የተከታታይ ምዘና ስልቶች በክፍል ውስጥ ያላቸውን ተተግባሪነት ለመፈተሽ በአራቱም መምህራን ላይ ሦስት ሦስት ጊዜ ምልከታ ተካሂዷል፡፡ በምልከታ የተገኙት ውጤቶች የተተነተኑት በምልከታ የታዩትን ክንውኖች በመቁጠርና አማካያቸውን በማስላት ነው፡፡ ውጤቱም የእያንዳንዱን ተጠኚ መምህር ውጤት በግልፅ በሚያሳይ መልኩ (ሀ እና መ) ፊደል የስነ-ልሳን መምህራንን (ለ እና ሠ) ደግሞ የበሳል ድርሰት መምህራንን ወክለው በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

## ሠንጠረዥ፡5. ስለ መምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶች አጠቃቀም ከምልከታ የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የዩኒቨርሲቲው ስም | የመምህራን ብዛት | የመምህራን ኮድ | የቃል ጥያቄ | | ሙከራና ፈተና | | በተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ | | የግል ስራ | | የቡድን ስራ | | የመምህር ተማሪ ውይይት | | የራስ ምዘና | | የቢጤ ምዘና | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | |
| | | | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % |
| 1 | ደብረብርሃን | 2 | ሀ | 3 | 100 | - | - | 2 | 66.66 | 3 | 100 | - | - | - | - | - | - | - | |
| | | | ለ | 3 | 100 | - | - | 1 | 33.33 | 2 | 66.66 | 3 | 100 | - | - | - | - | - | |
| 2 | ወሎ | 2 | መ | 2 | 66.66 | - | - | 1 | 33.33 | 3 | 100 | 1 | 33.33 | - | - | - | - | 1 | 33.33 |
| | | | ሠ | - | - | 1 | 33.33 | - | - | 2 | 66.66 | 2 | 66.66 | - | - | - | - | 1 | 33.33 |
| | | | ድምር | 8 | 66.6 | 1 | 8.33 | 4 | 33.33 | 10 | 83.33 | 6 | 50 | - | - | - | - | 2 | 16.66 |
| | | | አማካይ | 2 | | 0.25 | | 1 | | 2.5 | | 1.5 | | - | | - | | 0.5 | |

ሠንጠረዥ 5 እንደሚያሳየው ስምንት የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች በምልከታው ማረጋገጫ ዝርዝር ውስጥ ተካተው የክፍል ውስጥ ተተግባሪነታቸው ተፈትሿል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የቃል ጥያቄን የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተጠኚ መምህራን በምልከታ ጊዜያት ሁሉ ተግባራዊ ያደረጉ ሲሆን፣ የወሎ ዩኒቨርሲቲ የሥነ-ልሳን መምህር 66.66% ሲተገብሩ የበሳል ድርሰት መምህር ጭራሹንም ሲተገብሩት አልታዩም፡፡ ሙከራና ፈተናን የወሎ ዩኒቨርሲቲ የበሳል ድርሰት መምህር አንድ ጊዜ ብቻ አከናውነዋል፡፡ ሌላው በተማሪዎች ፊት እየወጡ የማቅረብ ስልት ነው፡፡ ይህ ስልት ከወሎ ዩኒቨርሲቲ የበሳል ድርሰት መምህር በስተቀር ሦስቱ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን ተጠቅመውበታል፡፡ የአጠቃቀም ደረጃቸውን ስንመለከት የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የሥነ-ልሳን መምህር 66.6 % ያከናወነ ሲሆን ፣ቀሪዎቹ አንድ አንድ ጊዜ ብቻ 33.33 % አከናውነዋል፡፡

የግል ሥራ በአብዛኛው በሁሉም መምህራን ዘንድ የተከናወነ የምዘና ስልት ነው፡፡ የሥነ-ልሳን መምህራን ሙሉ በሙሉ 100%፣የበሳል ድርሰት መምህራን ደግሞ ሁለት ሁለት ጊዜ ማለት 66.66% ተግባራዊ አድርገዋል፡፡ የቡድን ስራ ስልትን ስናይ ደግሞ ከደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የስነ-ልሳን መምህር ውጭ ሁሉም ተግባራዊ ለማድረግ ሞክረዋል፡፡ የደብረብርሃን የበሳል ድርሰት መምህር በሁሉም የምልከታ ጊዜያት ውስጥ ተግባራዊ ሲያደርጉ፣የወሎ የስነ-ልሳንና የበሳል ድርሰት መምህራን በቅደም ተከተል 33.33% እና 66.66% አከናውነዋል፡፡

ሌላውና የመጨረሻው የቢጤ ምዘና ስልት ሲሆን የተተገበረውም በወሎ ዩኒቨርሲቲ በሁለት ተጠኚ መምህራን ብቻ ነው፡፡ የተጠቀሙበትም 33.33% ብቻ ነው፡፡ የመምህር ተማሪ ውይይት እና የራስ ምዘና በሁሉም መምህራን ዘንድ ያልተከናወኑ የምዘና ስልቶች ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ መምህራን የተጠቀሙባቸውን የምዘና አይነቶች ብዛት ስንመለከት የወሎ ዩኒቨርሲቲ የስነ-ልሳን መምህር የቃል ጥያቄ፣ በተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ፣ የግል ስራ፣ የቡድን ስራ እና የቢጤ ምዘና በድምሩ አምስት የምዘና ዘዴዎችን ተጠቅመዋል፡፡ የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተጠኚ መምህራን የቃል ጥያቄ፣ በተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ፣ የግል ስራ እና የድርሰት መምህር የቡድን ስራን

ጨምረው በመጠቀም በድምሩ ሦስትና አራት ዘዴዎችን ተግባር ላይ አውለዋል። የወሎ ዩኒቨርሲቲ የበሳል ድርሰት መምህር ደግሞ ከሌሎቹ በተለየ ከ10% የሚያዝ ፈተናን ጨምረው የግል ስራ፣ የቡድን ስራ እና የቢጤ ምዘናን ተጠቅመዋል። በአጠቃላይ መምህራን በክፍል ውስጥ የተጠቀሙባቸው የተከታታይ ምዘና ስልቶች ብዛት ከፍተኛው አምስት ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ ሦስት ነው።

ከሁሉም መምህራን የተገኘውን ውጤት በምናይበት ጊዜ በአብዛኛው 83.33% ያከናወኑት ወይም የተጠቀሙት የግል ስራ ስልትን ነው። በመቀጠል የቃል ጥያቄ 66.66%፣ የቡድን ስራ 50%፣ በተማሪዎች ፊት እየወቱጡ ማቅረብ 33.33%፣ የብጤ ምዘና 16.66% እና ሙከራና ፈተና 8.33% ተከናውነዋል።አማካያቸውም እንደ ቅደም ተከተላቸው 2.5፣2፣ 1.5 ፣1፣ 0.5 እና 0.25 ነው።

ስለዚህ ከምልከታው ውጤት የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ከምዘና ዘዴዎች ውስጥ የግል ስራን፣ የቃል ጥያቄን፣ የቡድን ስራን እና በተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብን በአብዛኛው፣ የቢጤ ምዘና እና ሙከራና ፈተናን አልፎ አልፎ መጠቀማቸውን ቀሪዎቹን ዘዴዎች ደግሞ ጭራሹን አለመጠቀማቸው ለማወቅ ተችሏል።

በሌላም በኩል በክፍል ውስጥ ምልከታ ወቅት የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን በሙሉ ለተማሪዎች ገለፃ እና ማስታወሻ በመስጠት አብዛኛውን ሰአት ሲሸፍኑ ተስተውለዋል። ይህ ማለት ደግሞ ተማሪ - ተኮር የማስተማር ዘዴን እየተከተሉ ወይም ተግባራዊ እያደረጉ አይደለም። ነገር ግን ተከታታይ ምዘና ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴን መከተል እንዳለበት በክለሳ ድርሳን 2.4 ላይ ተገልጿል።

### 4.3.2 ስለመምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶች አጠቃቀም ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች

የመምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶች አጠቃቀም አስመልክቶ ከምልከታ የተገኙትን መረጃዎች ለማመሳከር ሲባል መምህራን ያዘጋጇቸው ኮርስ ቢጋሮች እና የውጤት ማጠራቀሚያ ቅጾች ላይ ፍተሻ ተካሂዷል። የተገኘውም ውጤት እንደሚከተለው ተተንትኗል።

በኮርስ ቢጋሮች ላይ በተደረገው ፍተሻ የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተጠኚ መምህራን ኮርስ ቢጋሮች በተመሳሳይ መልኩ የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ስልቶችን ይዘው ወይም አካተው ተገኝተዋል። እነዚህም በየምዕራፎቹ ማጠናቀቂያ የሚሰጡ ድንገቴ ፈተናዎች፣ በግል ተሰርቶ የሚቀርብ ወረቀት፣ የቡድን ስራ ከተናጠላዊ ተሳትፎ ጋር፣ አጋማሽ ፈተና እና የማጠቃለያ ፈተና ሲሆኑ የስነ-ልሳን መምህር የብጤ ምዘናን ጨምረው አካተዋል። (አባሪ ስምንትን ይመልከቱ)።

የወሎ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ኮርስ ቢጋሮች ላይ የምዘና ዘዴዎች በግልፅ ተዘርዝረው የተቀመጡ ባይሆኑም የቡድን ስራ በሁለቱም መምህራን ኮርስ ቢጋሮች ላይ የተጠቀሰ ስልት ነው። ከዚህ በተጨማሪ የስነ-ልሳን መምህር ለተማሪዎች የሚሰጥ ሥራ (አሳይመንት)፣ እንዲሁም የበሳል ድርሰት መምህር የማስተማሪያ ዘዴዎች እንጂ የምዘና ዘዴ በማይመስልና ግልፅ ባልሆነ መልኩ የተለያዩ አንቀፆችን እንዲፅፉ በማድረግ፣ የተዛቡ አንቀፆችን አቃንተው እንዲፅፉ በማድረግ ወዘተ.የሚሉ ነጥቦችን የምዘና ስልቶች በሚል ንዑስ ርዕስ ስር አስፍረዋል። (አባሪ ዘጠኝን ይመልከቱ)።

በአጠቃላይ ከኮርስ ቢጋሮች የተገኙት መረጃዎች የሚያሳዩት ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የግል ስራ፣ የቡድን ስራ እና ፈተና ስልቶችን እንደሚጠቀሙ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በምልከታ እንደታየው በኮርስ ቢጋሮች ላይ የማይገልጿቸው ነገር ግን በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ የምዘና ስልቶች እንዳሉ ያሳያል።

ከኮርስ ቢጋሮች በተጨማሪ የመምህራን የውጤት ማጠራቀሚያ ቅፆች ታይተዋል። በዚህም መሰረት የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህራን የውጤት ማጠራቀሚያ ቅጾች በኮርስ ቢጋሮቻቸው ላይ በተጠቀሱት የምዘና ስልቶች መሰርት የተሸነሸነ ናቸው። ይህም ማለት የተማሪዎች ውጤቶች እንደምዘናው አይነት ተመዝግበዋል።የ ምዘናዎቹም አይነት ተመሳሳይና ከፍ ብሎ የተጠቀሱት ናቸው። ከመቶው ስልሳ ፐርሰንቱ በተለያዩ የተከታታይ ምዘና ስልቶች የሚሸፈን ሲሆን አርባ ፐርሰንቱ በማጠ ቃለያ ፈተና ይሸፈናል።የወሎ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ውጤት ማጠራቀሚያ ቅፆች ላይ ደግሞ የምዘና ስልቶችን ማግኘት አልተቻለም። ምክንያቱም ቅፆቹ ውጤቶቹን ብቻ እንጂ ውጤቶቹ በየትኞቹ የመመዘኛ ዘዴዎች የተገኙ እንደሆኑ የሚገልፁ አይደሉም።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ከጥናቱ ተተኳሪ ዩኒቨርሲቲዎች የተገኙ የተከታታይ ምዘና መተዳደሪያ ደንቦች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የደብረብረሃን ዩኒቨርሲቲ መምህራን ሊጠቀሙባቸው የሚገቡ የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች እና የሚይዙት ነጥብ ተወስነው የተቀመጡ ናቸው፡፡ እነዚህም በክፍለ ጊዜ መገኘትና በንቃት መሳተፍ 5%፣ በየምዕራፉ የሚሰጡ ድንገቴ ፈተናዎች 10% በግል ተሰርቶ የሚቀርብ ወረቀት 10% ፣የቡድን ስራ ከተናጠላዊ ተሳትፎ ጋር 10%፣ አጋማሽ ፈተና 20% እና የማጠቃለያ ፈተና 40% ናቸው፡፡ (አባሪ አስራ ሁለትን ይመልከቱ)፡፡

የመምህራኑም ኮርስ ቢጋሮች ይህንኑ መሰረት አድርገው የተዘጋጁ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ከእነዚህ ስልቶች በተጨማሪ ሌሎችንም መጠቀም የሚቻል ቢሆንም የተጠቀሱትን ስልቶች ያጓደለ ወይም ከዚህ አካሄድ ውጭ የተዘጋጀን የውጤት ማጠራቀሚያ ቅፅ በትምህርት ክፍሉም ሆነ በፋኩልቲ ዘንድ ተቀባይነት እንደማይኖረው ከመምህራኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሌላው የጥናቱ ተተኳሪ የሆነው የወሎ ዩኒቨርሲቲ የተከታታይ ምዘና መተዳደሪያ ደንብ ደግሞ መምህራን ምን አይነት የምዘና ዘዴዎችን መጠቀም እንዳለባቸው ወይም እነዚህ የምዘና ዘዴዎች አገልግሎት ላይ መዋል አለባቸው የሚል ነገር የለውም፡፡ ነገር ግን ተከታታይ ምዘና ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት ያዛል፡፡ ከዚህም የምንረዳው ለመምህራን በኮርስ ቢጋራቸው ላይ ተከታታይ ምዘና ስልቶችን በግልፅ አለማስቀመጥና በውጤት ማጠራቀሚያ ቅፆቹ ላይ የምናዘውን አይነት አብሮ አለማስፈር ምክንያት የዩኒቨርስቲው ተከታታይ ምዘና መተዳደሪያ ደንብ እና የበላይ አካላት ቁጥጥር መላላት መሆኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ ከውጤት ማጠራቀሚያ ቅፆች የተገኘው መረጃ የወሎ ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህራን ቅጾች የሚጠቀሙባቸውን የምዘና ስልቶች የትኞቹ እንደሆኑ ለመለየት የሚያስችሉ ባይሆኑም ከደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህራን የውጤት ማጠ ራቀሚያ ቅጾች የተገኘው ውጤት ከኮርስ ቢጋሮቻቸው ከተገኘው ውጤት ጋር የሚጣጣም መሆኑን ያስረዳል፡፡

### 4.3.3 የተከታታይ ምዘና ስልቶች አጠቃቀምን በተመለከተ የመምህራን ምላሽ

የስነ-ልሳንና የበሳል ድርሰት ትምህርቶችን የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶች አጠቃቀም አስመልክቶ ከምልከታ እና ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ከላይ ተተንትነዋል። ይህን የተመለከተ ጥያቄም መምህራን ተጠይቀዋል። የሰጡትም ምላሽ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል።

በቃለመጠይቅ ተራ ቁጥር (5) "ከተከታታይ ምዘና ስልቶች ወይም ዘዴዎች መካከል የትኞቹን ይጠቅማሉ? እንደ አጠቃቀምዎ ደረጃ በቅደም ተከተል ይግለፁ?" የሚል ጥያቄ ለተጠኚ መምህራን ቀርቧል። ለቀረበውም ጥያቄ እንደ ትምህርቱ ይዘት እና እንደ ምዘናው አላማ የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል። ከእነዚህም መካከል የክፍል ውስጥ ሙከራዎችና ፈተናዎች፣ የግልና የቡድን ስራዎች በሁሉም መምህራን (100%) የተጠቀሱ ናቸው። የክፍል ውስጥ ስራ፣ የቤት ስራ እና በተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብን ደግሞ ሶስቱ መምህራን (75%) ጠቅሰዋቸዋል። የቃል ጥያቄን በአብዛኛው በክፍል ውስጥ የተማሪዎችን ግንዛቤ ለማወቅ እጠቀምበታለሁ ያሉት ደግሞ የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የስነ-ልሳን መምህር ሲሆኑ የወሎ ዩኒቨርሲቲ የበሳል ድርሰት መምህር ደግሞ የብጤ ምዘናን እና ሰነደ ትምህርትን ጨምረው ጠቅሰዋል።

በዚህ ውጤት መሰረት የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙባቸው የምዘና ዘዴዎች ሙከራና ፈተና፣ የግልና የቡድን ስራዎች፣ የቃል ጥያቄ ፣የክፍል ውስጥ ስራዎች እና በተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ ናቸው።

### 4.3.4 ስለመምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶች አጠቃቀም የተማሪዎች ምላሽ

የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የበሳል ድርሰትና የስነ-ልሳን መምህሮቻቸው ተማሪዎችን ለመመዘን የተለያዩ ዘዴዎችን ስለመጠቀማቸው እና የትኞቹን ዘዴዎች አዘውትረው እንደሚጠቀሙ ተጠይቀው ምላሽ ሰጥተዋል። ውጤቱም የሚከተለው ነው።

ሠንጠረዥ፡ 6. ስለመምህራን የምዘና ስልቶች መጠቀም ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ዝርዝር ጥያቄ | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | ለመወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | በጣም አልስ ማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | |
| | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % |
| 2. መምህራን የተለያዩ የምዘና ተግባራትን (የግልና ቡድን ስራ ፈተና ፖርትፎሊዮ ወዘተ.....) ይሰጡናል:: | 27 | 56.25 | 18 | 37.5 | 2 | 4.16 | 1 | 2.08 | - | - |
| 11. መምህራን ከ5% ወይም ከ10% የሚያዙ ፈተናዎችን መስጠት ያዘወትራሉ:: | 15 | 31.25 | 19 | 39.58 | 8 | 16.66 | 5 | 10.41 | 1 | 2.08 |

ሠንጠረዥ6 እንደሚያመለክተው ጥያቄ ቁጥር 2 ላይ ለቀረበው ጥያቄ 56.25% የሚሆኑ ተማሪዎች "በጣም እስማማለሁ"፣ 37.5% የሚሆኑት ደግሞ "እስማማለሁ" የሚሉ አማራጭ መልሶችን መርጠው መልሰዋል:: በጣም ጥቂቶቹ ደግሞ ለመወሰን መቸገራቸውንና አለመስማማታቸውን ገልፀዋል:: ይህም ውጤት መምህራን የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ዘዴዎችን እንደሚጠቀሙ ያመለክታል:: በተጨማሪም መምህራን የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን እንጠቀማለን ብለው ከሰጡት ምላሽ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ያሳያል::

በዚሁ ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር (11) ለቀረበው ጥያቄ 70.83% የሚሆኑ ተማሪዎች "በጣም እስማማለሁ" እና "እስማማለሁ" በማለት መልሰዋል:: ይህም የሚያሳየው የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ከ5% እና ከ10% የሚያዙ ፈተናዎችን መስጠት እንደሚያዘወትሩ ነው:: መምህራን በአብዛኛው የምንጠቀምባቸው ብለው ከጠቀሷቸው የምዘና ዘዴዎች ውስጥ ደግሞ ፈተና አንዱ ነው:: ስለዚህ የተማሪዎች ምላሽ ከመምህራን ምላሽ ጋር ተጣጥሟል:: (የሁለቱ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በተናጠል የተሰጡትን ምላሽ በተመለከተ (አባሪ ስድስትን ይመልከቱ))::

ከዚህ በተጨማሪ መምህራን ከተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ውስጥ በአብዛኛው የትኞቹን እንደሚጠቀሙ ለማወቅና ከምልከታ፣ ከሰነድ ፍተሻ እና ከመምህራን ምላሽ ከተገኙ መረጃዎች ጋር ለማመሳከር ለተማሪዎች አስር የተከታታይ ምዘና ስልቶችን በማቅረብ

እንደ መምህሮቻቸው አጠቃቀም ደረጃ ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት የተገኘው ውጤት በሚከተለው ሰንጠረዥ የተገለፀ ሲሆን ወደ ጎን ከ1-10 የተቀመጡት ቁጥሮች የደረጃ ቅደም ተከተሉን ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ የመጀመሪያውን ዘዴ የተወሰኑ ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃ የተወሰኑ በሁለተኛ ደረጃ እያለ ይቀጥላል፡፡

ሠንጠረዥ፡7. የመምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶች የአጠቃቀም ደረጃን በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የተከታታይ ምዘና ስልቶች | የደረጃ ቅደም ተከተል | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | አማካይ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | | 2 | | 3 | | 4 | | 5 | | 6 | | 7 | | 8 | | 9 | | 10 | | |
| | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | |
| 1 | የቃል ጥያቄ | 11 | 22.91 | 9 | 18.75 | 6 | 12.5 | 6 | 12.5 | 4 | 8.33 | 5 | 10.41 | 3 | 6.25 | 3 | 6.25 | - | - | 1 | 2.08 | 7.33 |
| 2 | ምልከታ | 3 | 6.25 | 4 | 8.33 | 2 | 4.16 | 5 | 10.41 | 4 | 8.33 | 8 | 16.66 | 6 | 12.5 | 5 | 10.41 | 7 | 14.58 | 4 | 8.33 | 4.96 |
| 3 | ሙከራና ፈተና | 11 | 22.91 | 12 | 25 | 7 | 14.58 | 4 | 8.33 | 3 | 6.25 | 2 | 4.16 | - | - | 4 | 8.33 | 2 | 4.16 | 3 | 6.25 | 7.27 |
| 4 | በተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ | 7 | 14.58 | 7 | 14.58 | 8 | 16.66 | 6 | 12.5 | 4 | 8.33 | 1 | 2.08 | 6 | 12.5 | 6 | 12.5 | 2 | 4.16 | 1 | 2.08 | 6.56 |
| 5 | የጥንድና የቡድን ስራ | 16 | 33.33 | 11 | 22.91 | 6 | 12.5 | 5 | 10.41 | 5 | 10.41 | 2 | 4.16 | 1 | 2.08 | 2 | 4.16 | - | - | - | - | 8.17 |
| 6 | የመምህር ተማሪ ውይይት | 1 | 2.08 | 2 | 4.16 | 3 | 6.25 | 5 | 10.41 | 2 | 4.16 | 1 | 2.08 | 6 | 12.5 | 12 | 25 | 10 | 20.83 | 6 | 12.5 | 3.96 |
| 7 | የራስ ምዘና | - | | 1 | 2.08 | 4 | 8.33 | 5 | 10.41 | 6 | 12.5 | 6 | 12.5 | 7 | 14.58 | 8 | 16.66 | 6 | 12.5 | 5 | 10.41 | 4.40 |
| 8 | የብጤ ምዘና | - | | 1 | 2.08 | 2 | 4.16 | 3 | 6.25 | 5 | 10.41 | 6 | 12.5 | 13 | 27.08 | 10 | 20.83 | 7 | 14.58 | 1 | 2.08 | 4.23 |
| 9 | የፕሮጀክት ምዘና | - | | - | - | - | - | - | - | 2 | 4.16 | 3 | 6.25 | 8 | 16.66 | 11 | 22.91 | 17 | 35.41 | 7 | 14.58 | 2.77 |
| 10 | ፖርትፎሊዮ | - | | - | | 1 | 2.08 | 1 | 2.08 | - | | 1 | 2.08 | 3 | 6.25 | 2 | 4.16 | 8 | 16.66 | 32 | 66.66 | 1.79 |

በሠንጠረዥ 7 እንደተገለፀው የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የተሰጧቸውን አስር የተከታታይ ምዘና ስልቶች እንደመምህሮቻቸው አጠቃቀም የተለያየ ደረጃ ሰጥተዋቸዋል። በዚህም መሰረት የጥንድና የቡድን ስራ፣ የቃል ጥያቄ፣ ሙከራና ፈተና እና በተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ ከአንድ እስከ አራት ያለውን ደረጃ የያዙ ሲሆን አማካይ ውጤታቸውም በቅደም ተከተል 8.17፣ 7.33፣ 7.27 እና 6.56 ነው። ስለዚህ እነዚህ ስልቶች መምህራን በአብዛኛው የሚጠቀሙባቸው መሆናቸውን ማወቅ ይቻላል። በተጨማሪም በምልከታ እና በመምህራን ምላሽ በአብዛኛው የሚተገበሩ ተብለው ከተለዩ የምዘና ስልቶች ጋር አንድ ወይም ተመሳሳይ መሆናቸው ተረጋግጧል።

ከአምስት እስከ አስር ያለውን ደረጃ የያዙት ደግሞ ምልከታ፣ የራስ ምዘና፣ የቢጤ ምዘና፣ የመምህር ተማሪ ውይይት፣ የፕሮጀክት ምዘና እና ፖርትፎሊዮ ናቸው። አማካያቸውም በቅደም ተከተላቸው መሰረት 4.96 ፣4.40 ፣4.23፣ 3.96 ፣2.77 እና 1.79 ነው።ከዚህ ውጤት በመነሳት መምህራን ምልከታን፣የራስ ምዘናን እና የቢጤ ምዘና አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ፣ ሌሎቹን ስልቶች ግን እንደማይጠቀሙባቸው ማረጋገጥ ይቻላል። ነገር ግን ምልከታ፣ የራስ ምዘና፣ የመምህር-ተማሪ ውይይት እና የፕሮጀክት ምዘና ከአምስት ጀምሮ ያለውን ደረጃ የያዙ ቢሆኑም ከምልከታ ከሰነድ ፍተሻ እና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ በተገኘው መረጃ ያልታዩና ያልተጠቀሱ ስልቶች ናቸው። በተጨማሪም መምህራን ፖርትፎሊዮን አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙት ቢገልፁም በምልከታ እና በሰነድ ፍተሻ ውጤት ያልተገኘ በተማሪዎችም ምላሽ የመጨረሻውን ደረጃ የያዘ ስልት ነው። ስለዚህ መምህራን እነዚህን ስልቶች በጭራሽ እንደማይጠቀሙባቸው ማወቅ ይቻላል። ይሁን እንጂ ምዕራፍ ሁለት 2.9 ላይ በተገለፀው የPuhl (1997) ሀሳብ መሠረት የራስ ምዘና እና ፖርትፎሊዮ ለቋንቋ ትምህርት በተለይ ደግሞ ለጽህፈት ትምህርት (Writing Course) በጣም ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ስልቶች ናቸው።

በአጠቃላይ የመምህራን የተከታታይ ምዘና ስልቶችን አጠቃቀም በተመለከተ ከምልከታ፣ ከሰነድ ፍተሻ፣ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ እና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ከተገኙ መረጃዎች ማረጋገጥ የሚቻለው መምህራን በአብዛኛው የቃል ጥያቄ፣ የግል እና የቡድን ስራ፣ ሙከራና ፈተና እና በተማሪዎች ፊት እየወጡ

ማቅረብ ስልቶችን መጠቀም እንደሚያዘወትሩ፣ የብጤ ምዘናን አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ እና ሌሎቹን ስልቶች ምንም እንደማይተገብሯቸው ነው::

ከዚህ ጋር ተያይዞ መምህራን የተለያዩ የምዘና ስልቶችን ለተማሪዎቻቸው በሚሰጡበት ጊዜ ማብራሪያ መስጠታቸውን አስመልክቶ ከምልከታ፣ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ እና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቦ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል::

ከምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ሁሉም መምህራን (100%) በክፍል ውስጥ የተለያዩ የግልና የቡድን ስራዎችን ተማሪዎች እንዲሰሩ በሚያደርጉበት ጊዜ ሥራውን እንዴት መስራት እንደላባቸው ለተማሪዎች ማብራሪያ ይሰጣሉ:: ይሁን እንጂ ሦስቱ መምህራን አንድ አንድ ጊዜ ለተማሪዎቻቸው የሰጡት የክፍል ስራ አሰራር ማብራሪያ ግልፅነት የጎደለው ነው:: ምክንያቱም ተማሪዎች የተሰጡትን ስራ እንዴት መስራት እንዳለባቸው በግልፅ ባለመረዳታቸው ምክንያት ስለአሰራሩ ከብጤዎቻቸው ጋር ሲነጋገሩ በኋላም መምህሮቻቸውን ደግመው ሲጠይቁ ተስተውለዋል:: በአጠቃላይ ከምልከታው መረጃ መምህራን ለተማሪዎች ለሚሰጧቸው የምዘና ተግባራት አብዛኛውን ጊዜ ግልፅ የሆነ ማብራሪያ እንደሚሰጡ፣ አልፎ አልፎ ግን ግልፅ ያለማድረግ ችግር እንዳለ ለማወቅ ተችሏል::

ይህን በተመለከተ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ለቀረበላቸው ጥያቄ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሚሰሩ የምዘና ተግባራት በሙሉ ግልፅ ማብራሪያ እንደሚሰጡ ገልፃዋል:: ይህም ምላሽ በምልከታ የተገኘውን ውጤት የሚደግፍ ነው:: ከምልከታ እና ከመምህራን ምላሽ የተገኘውን መረጃ ለማጠናከር ለተማሪዎችም ጥያቄ ቀርቧል:: የሚከተለውም ውጤት ተገኝቷል::

ሠንጠረዥ፡8. የመምህራን ለምዘና ተግባራት ማብራሪያ መስጠትን በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ጥያቄ | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | ለመወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | |
| | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 3. ለግልም ሆነ ለቡድን ስራዎቻችን ግልፅ የሆነ ማብራሪያ ከመምህሮቻችን እናገኛለን:: | 21 | 43.75 | 19 | 39.58 | 3 | 6.25 | 5 | 10.41 | - | - |

ከሠንጠረዥ8 ማየት እንደሚቻለው ተማሪዎች ተራ ቁጥር (3) ላይ ለቀረበላቸው ጥያቄ 43.75% ተማሪዎች "በጣም እስማማለሁ"፣ 39.58% የሚሆኑ ተማሪዎች "እስማማለሁ" የሚሉ አማራጮችን በመምረጥ መልሰዋል:: ቀሪዎቹ 6.25% እና 10.41% ተማሪዎች በቅደም ተከተል "ለመወሰን ያስቸግረኛል" እና "አልስማማም" በማለት መልስ ሰጥተዋል::ይህ ውጤት የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ለተማሪዎቻቸው የምዘና ተግባራት በሚሰጡበት ጊዜ በቅድሚያ ግልፅ ማብራሪያ መስጠታቸውን ያሳያል::

በአጠቃላይ የመምህራን ለምዘና ተግባራት ግልፅ ማብራሪያ መስጠትን በተመለከተ ከምልከታ፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ የሚጣጣም ሆኖ ተገኝቷል::

## 4.4 በተከታታይ ምዘና ተግባራት ላይ ተማሪዎችን ማሳተፍ በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በምዘናው ተግባር ላይ ማሳተፋቸውንና አለማሳተፋቸውን ለመመርመር በምልከታ፣ በመምህራን ቃለ መጠይቅ እና በተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ አማካኝነት መረጃ ተሰብስቧል:: የተገኘውም መረጃ እንደሚከተለው ተተንትኗል::

በምልከታው ሂደት ወቅት መምህራን ካከናወኗቸው የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች መካከል ተማሪዎች በምዘናው ተግባር እንዲሳተፉ እድል የሚሰጠው የቢጤ ምዘና ብቻ ነው:: ይህም ከጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ውስጥ በሁለቱ አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ተከናውኗል:: ከዚህ ባለፈ ተማሪዎችን የሚያሳትፍ የምዘና ተግባር በምልከታው ወቅት አልታየም:: ይህ ውጤት ደግሞ መምህራን ተማሪዎች የራሳቸውን ወይም የጓደኞቻቸውን ስራ እንዲገመግሙ በማድረግ፣ ተማሪዎች በምዘናው ተግባር ላይ እንዲሳተፉ እንደማያደርጉ ይገልፃል::

ለመምህራን በቀረበው ቃለ መጠይቅ ተራ ቁጥር (6) "ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው እንዲመዝኑ ወይም እንዲገመግሙ እንዲሁም እርስ በርሳቸው እንዲገማገሙ ያደርጋሉ? ካደረጉ መቼ እና እንዴት ያስኬዱታል?" ተብለው ተጠይቀዋል:: ለዚህም ጥያቄ አንድ (25%) መምህር ብቻ ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው እንዲገመግሙ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል::: የክፍል ውስጥ ስራዎቻቸውን

እንዲለዋወጡ በማድረግ እርስ በርስ እንዲገማገሙ እናደርጋለን ያሉት ደግሞ ሁለቱ የበሳል ድርሰት መምህራን ናቸው:: አንድ ስነ-ልሳን መምህር ግን ሁለቱንም እንደማያደርጉ ተናግረዋል::

ከመምህራን ምላሽ የምንገነዘበው መምህራን ተማሪዎቻቸው የራሳቸውንና የጓደኞቻ ቸውን ስራ እንዲገመግሙ በማድረግ የራሳቸውን ስህተት ራሳቸው እንዲያወጡና ከብጤዎቻቸው ጋር እንዲተራረሙ የማድረግ ልምዳቸው በጣም አነስተኛ መሆኑን ነው:: ይህም ውጤት በምልከታ የተገኘውን መረጃ የሚያጠናክር ነው::

ከምልከታና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ በተጨማሪ ለተማሪዎችም ጥያቄ ቀርቦ የሚከተለው ምላሽ ተገኝቷል::

ሠንጠረዥ፡9. መምህራን በምዘና ተግባራት ላይ ተማሪዎችን ማሳተፍ በተመለከተ የተማሪዎችን ምላሽ የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ጥያቄ | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | ለመወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | |
| | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % | በቁ ጥር | % |
| 8. የመመዘኛ መስፈርቶችን በመስጠት የራሳችንን ስራ በራሳችን እንድንገመግም ያደርጉናል:: | 9 | 18.75 | 7 | 14.58 | 12 | 25 | 11 | 22.91 | 9 | 18.75 |
| 9. ከጓደኞቻችን ጋር ስራዎቻችንን በመለዋወጥ እርስ በርስ እንድንገማገም እና አስተያየት እንድንለዋወጥ ያደርጋሉ:: | 13 | 27.08 | 11 | 22.91 | 9 | 18.75 | 10 | 20.83 | 5 | 10.41 |

ይህ ሠንጠረዥ እንደሚያሳየው ተራ ቁጥር (8) ላይ ለቀረበው ጥያቄ 18.75% ተማሪዎች "በጣም እስማማለሁ"፣ 14.58% "እስማማለሁ" የሚሉ አማራጭ መልሶችን ሲመልሱ፣ 22.91% እና 18.75% ተማሪዎች ደግሞ "አልስማማም" እና "በፍፁም አልስማማም" በማለት መልሰዋል:: ቀሪዎቹ ተማሪዎች ለመወሰን ያስቸግረናል ብለዋል:: ይህም ምላሽ ከጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ አለመስማማታቸውንና ለመወሰን መቸገራቸውን የገለፁበት በመሆኑ ተተኳሪ መምህራን የመመዘኛ መስፈርቶችን አዘጋጅቶ በመስጠት ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ

በራሳቸው እንዲመዝኑ እንደማያደርጉ ያሳያል። ይህም ውጤት ከምልከታ እና ከመምህራን ምላሽ ከተገኘው ውጤት ጋር የሚስማማ ነው።

ይህን በተመለከተ ምዕራፍ ሁለት 2.9 ተራ ቁጥር 7 ላይ እንደተገለፀው ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው የሚመዝኑበት ሂደት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አይነተኛ ቦታ አለው። ተማሪዎችም እራሳቸውን የሚመዝኑበት ሁኔታ ከተመቻቸላቸው ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን መለየት፣ ለውጣቸውን መቆጣጠርና የተለያዩ እርምጃዎችን መውሰድ ይችላሉ። እንዲሁም ለመምህራን የስራ ጫና ይቀንሳል። ነገር ግን የተተኳሪ መምህራን ተግባር ከንድፈ ሀሳቡ በተቃራኒ ነው ።

ከሠንጠረዥ 9 ሳንወጣ ተራ ቁጥር (9) ላይ መምህራን ተማሪዎች እርስ በርስ እንዲገማገሙና አስተያየት እንዲለዋወጡ ማድረጋቸውን ለማወቅ የሚያስችል ጥያቄ ቀርቧል። በዚህም መሰረት 27.08% ተማሪዎች "በጣም እስማማለሁ" ፣22.91% ተማሪዎች ደግሞ "እስማማለሁ" ብለው መልሰዋል። 31.24% የሚሆኑት አለመስማማ ታቸውን ቀሪዎቹ ደግሞ ለመወሰን መቸገራቸውን ገልጸዋል። ስለዚህ ከዚህ ውጤት የምንረዳው መምህራን ተማሪዎቻቸውን ከብጤዎቻቸው ጋር እንዲገማገሙ፣ አስተያየት እንዲለዋወጡ ማድረጋቸውን ነው።ነገር ግን ከምልከታ እና ከመመምህራን ምላሽ የተገኘው ውጤት በዚህ ጉዳይ ላይ የመምህራን ልምድ አነስተኛ መሆኑን የሚያመላክት ነው። ስለዚህ ተተኳሪ መምህራን ተማሪዎች በእርስ በርስ ግምገማ እንዲሳተፉ የሚያደርጉት በጣም አልፎ አልፎ ወይም በጣም በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን ማወቅ ይቻላል።

ይሁን እንጂ እርስ በርስ የመተራረም ተግባር በቋንቋ ትምህርት በተለይ በፅሁፈት ወይም በድርሰት ትምህርት ከፍተኛ ቦታ ያለው ሲሆን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ማህበራዊነትን እንዲፈጥሩ፣ አስተያየት እንዲለዋወጡ፣ ሀሳባቸውን እንዲያንፀባርቁና አመዛዝኖ ማየት እንዲችሉ እንደሚያደርግ በክለሳ ድርሳን 2.9 ተራ ቁጥር 8 ላይ የምሁራን ሀሳብ ተጠቅሷል።

በአጠቃላይ ከምልከታ፣ ከቃለ መጠይቅ እና ከፅሁፍ መጠይቅ የመምህራን በተከታታይ ምዘና ተግባራት ላይ ተማሪዎችን ማሳተፍ ላይ ያተኩሩ ምላሾች ተገኝተዋል። በዚህም ተተኳሪ መምህራን ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው

እንዲገመግሙ አለማድረጋቸው ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች እርስ በርስ እንዲገማገሙ የሚያደርጉት አልፎ አልፎ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በሌላም በኩል ከፍ ብሎ (4.3) ላይ የተገለፀውን ውጤት የሚያጠናክር ነው፡፡ ምክንያቱም ተተኳሪ መምህራን ከተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ውስጥ የራስ ምዘና ዘዴን እንደማይጠቀሙበት እና የብጤ ምዘናንም በጥቂቱ የሚተገብሩት መሆኑን ያሳያል፡፡

## 4.5 በተከታታይ ምዘና ሂደት የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.5.1 ስለመምህራን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ከክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኙ መረጃዎች

የተተኳሪ መምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታ በክፍል ውስጥ ምልከታ ተፈትሿል፡፡ በዚህ ጊዜ በመምህራን ትዕዛዝ መሰረት ተማሪዎች የተለያዩ የምዘና ተግባራትን አከናውነዋል፡፡ በዚህም መሰረት በእያንዳንዱ የምዘና ተግባራት ላይ መምህራን የሰጧቸውን ምጋቤ ምላሾች በመቁጠር ከዚያም የሁሉንም በመደመር አማካይ ውጤት ለማግኘት ተሞክሯል፡፡ ውጤቱም በሚከተለው ሠንጠረዥ የተቀመጠ ሲሆን የሁሉንም መምህራን የምልከታ ውጤት በግልፅ ለማሳየት ሲባል የእያንዳንዳቸው ክንዋኔ ድግግሞሽ በተናጠል ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ፡ 10. የመምህራን ምጋቤ ምላሽ መስጠትን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘውን መረጃ የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| የዩኒቨርሲቲው ስም | የመምህራን ብዛት | የመምህራን ኮድ | የክንዋኔ ብዛት | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቁጥር | % |
| ደብረብርሃን | 2 | ሀ | 3 | 100 |
| | | ለ | 3 | 100 |
| ወሎ | 2 | መ | 2 | 66.66 |
| | | ሠ | 2 | 66.66 |
| | | | 10 | 83.33 |
| ድምር | 4 | አማካይ | 2.5 | |

ሠንጠረዥ 10 እንደሚያመለክተው የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተጠኚ መምህራን ምልከታ በተካሄደባቸው ጊዜያት ሁሉ ለተማሪዎቻቸው ምጋቤ ምላሽ የሰጡ ሲሆን፣ የወሎ ዩኒቨርሲቲ ተጠኚ መምህራን ደግሞ ሁለት ሁለት ጊዜ ሰጥተዋል፡፡ በአጠቃላይ

የሁለቱንም ዩኒቨርሲቲዎች መምህራን ምጋቤ ምላሽ የመስጠት ክንዋኔን ስንመለከት 83.33% እና 2.5 አማካይ ውጤት ተገኝቷል:: ይህ ውጤት የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት በአብዛኛው ለተማሪዎች ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡ መሆናቸውን ያሳያል::

ከምልከታው ሳንወጣ ተተኳሪ መምህራን ምጋቤ ምላሽ መቼ እንደሚሰጡ ወይም የሚሰጡበትን መንገድ ለማየት ተሞክሯል:: በዚህም መሰረት ከወሎ ዩኒቨርሲቲ የበሳል ድርሰት መምህር በስተቀር ሁሉም ተጠኚ መምህራን ያለፈውን ትምህርት ለመከለስ እና በማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ትምህርቱን መረዳታቸውንና አለመረዳታቸውን ለማወቅ በሚያቀርቧቸው የቃል ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች ለሚሰጧቸው መልሶች ምጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል:: በተጨማሪም የሁለቱም ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ የስነ-ልሳን መምህራን ሀረጎችንና ዓረፍተ ነገሮችን በመስጠት ተማሪዎች በግል በእፀ-መዋቅር እንዲሰሩ በማድረግ፣ በተ ማሪዎች መሃል በመዘዋወር እና የተወሰኑ ተማሪችን ቦርድ ላይ አውጥተው በማሰራት፣ የተማሪዎች የስራ ውጤት ወይም አሰራር ላይ ምጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል::

እንዲሁም የወሎ ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ የበሳል ድርሰት መምህር ተማሪዎች በግልና በቡድን ሆነው የተለያዩ የአንቀፅ ማስፋፊያ ዘዴዎችን ተጠቅመው አንቀፅ እንዲፅፉና ከተሰጣቸው አንቀፅ ላይ አንቀፁ የተስፋፋበትን መንገድ ከማስረጃ ጋር እንዲያቀርቡ በማድረግ፣ የደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ የበሳል ድርሰት መምህር ደግሞ ተራኪ ድርሰት በቡድን በቡድን ሆነው እንዲፅፉና የተወሰኑ ተማሪዎች ወጥተው እንዲያቀርቡ በማድረግ፣ በየቡድኑ በመዘዋወርና በመጨረሻም ተማሪዎች ለሚያቀርቡት መልስ ምጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል::

አሁንም ከምልከታው ሳንወጣ የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ምጋቤ ምላሽ ትኩረት ምን ላይ እንደሆነ ታይቷል:: በዚህም ሁሉም መምህራን (100%) ምጋቤ ምላሽ በሚሰጡበት ወቅት ተማሪዎች ለሚሰጡት መልስ ወይም ለሚያቀርቡት ስራ ትክክለኛውን መልስ እና ስህተትን መንገር ላይ ትኩረት አድርገዋል:: (በተለይ በስነ-ልሳን መምህራን ላይ በተደረገው ምልከታ):: ከደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ የስነ-ልሳን መምህር እና ከወሎ ዩኒቨርሲቲ የድርሰት መምህር፣ ምልከታ በተከናወነባቸው

ጊዜያት ውስጥ አንድ አንድ ጊዜ ብቻ የተማሪዎችን ጠንካራና ጎን የሚገልፅ ምጋቤ ምላሽ ሰጥተዋል::

### 4.5.2 ስለመምህራን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች

የጥናቱ ተተኳሪ መምህራንን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታ በሚመለከት ከምልከታ የተገኙ መረጃዎችን ለማረጋገጥ የተማሪዎች ፈተናዎች፣ የግልና የቡድን ስራዎች ላይ የተሰጡ ወይም የተፃፉ ምጋቤ ምላሾች ላይ ፍተሻ ተካሂዷል::

በዚህም መሰረት በፈታናዎች እና በግልና በቡድን ስራዎች ላይ ምጋቤ ምላሽ ሰጥተው የተገኙት ሁለቱ ተጠኚ መምህራን ብቻ ናቸው:: እነዚህም የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የስነ-ልሳን መምህር እና የወሎ ዩኒቨርሲቲ የበሳል ድርሰት መምህራን ሲሆኑ፣ የወሎ ዩኒቨርሲቲ ተጠኚ የስነ-ልሳን መምህር በአብዛኛው ለተማሪዎች የምሰጣቸው ፈተናዎች የምርጫ ጥያቄዎች ስለሆኑ በአብዛኛው ውጤታቸውን /ማርካቸውን/ ብቻ እንጂ የማስቀምጠው ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ አልሰጠሁባቸውም በማለት ለማሳየት ፍቃደኛ ባለመሆናቸው፣ እንዲሁም የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የበሳል ድርሰት መምህር በእጃቸው ያለውን የተማሪዎች ወረቀት በጊዜው ባለማረማቸው፣ በድጋሚም ታርሞ ከሆነ በማለት ለማግኘት በተደረገው ጥረት በግላቸው ችግር ምክንያት ማግኘት ባለመቻሉ ምክንያት ምጋቤ ምላሽ የሰጡበትን የፈተና ወይም የግልና የቡድን ወረቀት ማግኘት አልተቻለም::

ምጋቤ ምላሽ የሰጡት ሁለት መምህራን (50%) በተማሪዎች የግልና የቡድን ስራዎች ላይ የፃፏቸውን ምጋቤ ምላሾች ስንዳስስ ሁለቱም መምህራን ተማሪዎችን የሚያነሳሱ፣ ስህተትን የሚያሳውቁ ወይም ማሻሻል ያላባቸውን ነገሮች የሚጠቁሙ ምጋቤ ምላሾች በጥያቄና በሀተታ መልክ በፅሁፍ ተገልፀው ተገኝተዋል:: ከእነዚህም መካከል "ጥሩ ነው"፣ "በጣም ጥሩ ነው"፣ "የአረፍተ ነገር አወቃቀር?"፣ "የቃላት ድግግሞሽ?" ወዘተ የሚሉ አስተያየቶች ናቸው:: የተማሪዎችን ጠንካራ ጎን የሚገልጽ አስተያየት የተሰጠባቸው ወረቀቶችን ግን ማግኘት አልተቻለም:: እንዲሁም ምንም አይነት አስተያየት ሳይሰጥባቸው ውጤቱን ብቻ የሚገልፁ የተወሰኑ የፈተና ወረቀቶች ተገኝተዋል::

ከዚህ የሰነድ ፍተሻ ውጤት የምንረዳው ከጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ውስጥ ሁለቱ ብቻ በተማሪዎች ፈተናዎችና የቡድን ስራዎች ላይ ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ እንዲሰጡ፣ ምጋቤ ምላሹም ጥሩ ላልሰሩ ተማሪዎች ድክመታቸውን ወይም ስህተታቸውን መንገር ላይ፣ ጥሩ ለሰሩ ተማሪዎች ደግሞ የማበረታቻ ቃላትን መጠቀም ላይ ብቻ እንደሚያተኩር ነው::በተጨማሪም ከምልከታ ከተገኘው ውጤት ጋር እንደሚመሳሰል ነው::

### 4.5.3 ስለምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ የመምህራን ምላሽ

የተተኳሪ መምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታ አስመልክቶ ከምልከታ እና ከሰነድ ፍተሻ የተገኘውን መረጃ ለማጠናከር በቃለ መጠይቅ የቀረበው ጥያቄ ተራ ቁጥር (9) "ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ /Feedback/ ይሰጣሉ? የሚሰጡ ከሆነ መቼ እና ምን ላይ በማተኮር ይሰጣሉ?" የሚል ነው:: በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረት ሁሉም መምህራን (100%) በተከታታይ ምዘና ሂደት ለተማሪዎቻቸው ምጋቤ ምላሽ እንደሚሰጡ፣ ምጋቤ ምላሹንም የሚሰጡት በክፍል ውስጥ የትምህርት ሂደት በሚከናወኑ ቃል ጥያቄዎች፣ ተማሪዎች ስራዎቻቸውን በሚያቀርቡበት ጊዜ እና የፈተና ወረቀቶችን አርመው በሚመልሱበት ጊዜ እንደሆነ ገልፃዋል:: በተጨማሪም ምጋቤ ምላሽ ሲሰጡ ለተማሪዎች ስህተታቸውን ወይም ጉድለታቸውን መንገር ላይ እንደሚያተኩሩ አስረድተዋል:: ይህ የቃል ጥያቄ ምላሽ ውጤት በምልከታ እና በሰነድ ፍተሻ ከተገኘው ውጤት ጋር የሚመሳሰል ሆኖ ተገኝቷል::

ከዚህ ጋር በተያያዘ Puhl (1997) ምዕራፍ ሁለት 2.8 ላይ እንደገለፁት የምጋቤ ምላሽ ዋነኛ ትኩረት ተማሪዎች በሂደት የሚያሳዩትን ጠንካራና ደካማ ጎን መለየትና ድጋፍ መስጠት ነው:: ከዚህ አንፃር ሁሉም ተጠኚዎች በተለያየ መንገድ ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ መስጠታቸው ከምሁራኑ ሀሳብ ጋር የሚጣጣም ቢሆንም የምጋቤ ምላሽ አሰጣጣቸው ሁኔታ በተማሪዎች ድክመት ላይ ብቻ ያነጣጠረ መሆኑ ከንድፈ ሀሳቡ ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል::

### 4.5.4 ስለመምህራን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ የተማሪዎች ምላሽ

የመምህራንን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታ በሚመለከት ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ መረጃ ለመሰብሰብ ተሞክሯል:: እንደሚከተለውም ተተንትኗል::

ሠንጠረዥ፡11 ስለመምህራን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ የተማሪዎችን ምላሽ የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ጥያቄ | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | ለመወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | |
| | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 7. ክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለምናቀርባቸው ስራዎች አስፈላጊውን ምጋቤ ምላሽ /feed back/ ይሰጡናል:: | 15 | 31.25 | 20 | 41.6 | 4 | 8.33 | 7 | 14.58 | 2 | 4.16 |
| 10. ምጋቤ ምላሽ በሚሰጡን ጊዜ ትክክለኛውን መልስ በመንገር ላይ እንጂ ጠንካራ ጎናችን እና ማሻሻል ያለብን ነገሮች ላይ አያተኩሩም:: | 14 | 29.16 | 15 | 31.25 | 5 | 10.41 | 11 | 22.91 | 3 | 6.25 |
| 12. ፈጣንና ወቅቱን የጠበቀ ምጋቤ ምላሽ አይሰጡንም:: | 7 | 14.58 | 7 | 14.58 | 9 | 18.75 | 17 | 35.41 | 8 | 16.66 |

ሠንጠረዥ11 እንደሚያሳየው ጥያቄ ቁጥር (7) ላይ ለቀረበው ሐሳብ 31.25% እና 41.6% ተማሪዎች በቅደም ተከተል "በጣም እስማማለሁ" እና "እስማማለሁ" የሚሉ አማራጭ መልሶችን መልሰዋል:: ስለዚህ አብዛኛው የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የበሳል ድርሰትና የስነ-ልሳን መምህሮቻቸው አስፈላጊውን ምጋቤ ምላሽ እንደሚሰጧቸው ገልፀዋል:: ይህ ውጤት ደግሞ ከምልከታና ከሰነድ ፍተሻ ከተገኘው ውጤት እንዲሁም መምህራን ከሰጡት ምላሽ ጋር የሚጣጣም ነው:: በተመሳሳይ መልኩ ጥያቄ ቁጥር (10) ላይ ለቀረበው ሐሳብ 29.16% እና 31.25% የሚሆኑት ተማሪዎች "በጣም እስማማለሁ" እና "እስማማለሁ" የሚሉ አማራጮችን በመምረጥ መምህራን ምጋቤ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ትክክለኛ መልስ በመንገር ላይ እንጂ

ጠንካራ ጎናቸው ላይ እና ማሻሻል ያለባቸው ነገሮች ላይ ትኩረት እንደማያደርጉ ገልፀዋል:: ይህም የተማሪዎች ምላሽ ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ከተገኙ ውጤቶች ጋር የሚጣጣም ሆኖ ተገኝቷል::

ከሠንጠረዥ 10 ሳንወጣ ተራ ቁጥር (12) ላይ ለቀረበው ጥያቄ 52.07% የሚሆኑ ተማሪዎች ያለመስማማት አማራጮችን መርጠዋል:: ይህም የሚያሳየው በአብዛኛው ለማለት ባያስደፍርም ተጠኚ መምህራንን ፈጣንና ወቅቱን የጠበቀ ምጋቤ ምላሽ ለተማሪዎች እንደሚሰጡ ነው:: ይህ ውጤት ደግሞ በክላስ ድርሳን ከተገለፀው የምሁራን ሀሳብ ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ተጠኚ መምህራን ምጋቤ ምላሽ በወቅቱ በመስጠት በኩል የተሻለ ትኩረት እንዳላቸው ያስረዳል::

በአጠቃላይ የመምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታን ለመፈተሽ ከምልከታ፣ከሰነድ ፍተሻ፣ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ እና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ ውጤቶች በአብዛኛው መጣጣም ታይቶባቸዋል:: በዚህም መሠረት ተተኳሪ መምህራን ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ እንደሚሰጡ፣ ምጋቤ ምላሹንም በተለያዩ የተከታታይ ምዘና ተግባራት ላይ እንደሚያከናውኑ፣ ምጋቤ ምላሽ ሲሰጡ ስህተትን ወይም ትክክለኛውን መልስ መናገር ላይ እንደሚያተኩሩ እና መምህራን ወቅቱን የጠበቀ ምጋቤ ምላሽ እንደሚሰጡ ለማወቅ ተችሏል::

## 4.6 በተከታታይ ምዘና ሂደት የመመዘኛ መስፈርት ዝግጅት እና የነጥብ /የማርክ/ አሰጣጥን በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.6.1 ስለመመዘኛ መስፈርት ዝግጅት እና ስለነጥብ አሰጣጥ የመምህራን ምላሽ

መምህራን ለተማሪዎቻቸው ነጥብ የሚሰጡበትን መንገድ ከመጠየቃቸው በፊት የትምህርቱን አላማ መሰረት የሚያደርጉ የመመዘኛ መስፈርቶችን ማዘጋጀት በተመለከተ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል:: ይህም ተራ ቁጥር (7) ሲሆን "የትምህርቱን አላማ መሰረት ያደረጉ የመመዘኛ መስፈርቶች ያዘጋጃሉ? ካዘጋጁ መስፈርቶቹን ለተማሪዎች ያሳውቃሉ? በዝግጅት በኩልስ ተማሪዎችን ያሳትፋሉ?" የሚል ሲሆን አራቱም መምህራን(100%) ለተማሪዎች የምዘና ተግባራት የትምህርቱን አላማ መሰረት ያደረጉ የመመዘኛ መስፈርቶችን አዘጋጅተው እንደሚጠቀሙ አስረድተዋል::

የመመዘኛ መስፈርቶቹን ለተማሪዎች በማሳወቅ በኩል የሁለቱም ዩኒቨርሲቲ የበሳል ድርስት ተጠኚ መምህራን የምዘና ተግባርቱን ከመስጠታቸው በፊት የመመዘኛ መስፈርቶቹን ለተማሪዎቻቸው እንደሚያሳውቁ ሲገልፁ የስነ-ልሳን መምህራን ደግሞ ከእርማት በኋላ በተማሪዎች በኩል የሚነሳ ቅሬታ ካለ መልስ መስጠት እንጂ በቅድሚያ እንደማያሳውቁ ገልፀዋል::የመመዘኛ መስፈርቶች ዝግጅት ላይ ተማሪዎችን የማሳተፍ ጉዳይን በሚመለከት ደግሞ ሁሉም መምህራን የመመዘኛ መስፈርታቸውን የሚያዘጋጁት በግላቸው እንጂ ተማሪዎችን ጣልቃ እንደማያስገቡ ገልፀዋል::

ይህም ምላሽ የሚያሳየው የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን በሙሉ የተማሪዎችን ስራዎች መገምገም የሚያስችሉና የትምህርቱን አላማ መሰረት ያደረጉ የመመዘኛ መስፈርቶችን ቢጠቀሙምሁሉም መምህራን የመመዘኛመስፈርቶች በማዘጋጀት ሂደት ተማሪዎቻቸውን እንደማያሳትፉ ነው::በተጨማሪም መስፈርቶቹን ለተማሪዎች የሚያሳውቁት ሀምሳ በመቶ የሚሆኑት መምህራን ብቻ መሆናቸውን ያሳያል::

ከዚህ ጋር በተያያዘ ምዕራፍ 2.4 ላይ የተጠቀሰው የምሁራን ገለፃ እንደሚያስረዳው ተከታታይ ምዘና ግልፅ የመመዘኛ መስፈርቶች የያዘ እና መስፈርቶቹም በተማሪዎች ዘንድ የሚታወቁ መሆን አለባቸው:: ስለዚህ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ከመመዘናቸው በፊትም ሆነ በሚመዝኑበት ጊዜ የመመዘኛ መስፈርቶችን አስቀድመው ማሳወቅ አለባቸው:: ስለዚህ ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የመመዘኛ መስፈርቶችን እንደሚያዘጋጁ የሰጡት ምላሽ ከምሁራኑ ሀሳብ ጋር የሚጣጣም ቢሆንም መስፈርቶችን ለተማሪዎች በማሳወቅ ረገድ የሰጡት ምላሽ ግን የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል::

በጥያቄ ተራ ቁጥር (10) ደግሞ "ለተማሪዎች የምዘና ተግባራት ነጥብ /ማርክ/ ለመስጠት የሚጠቀሙበት ዘዴ አለዎት? ካለዎት ምን አይነት ዘዴዎችን ይጠቀማሉ?" የሚል ጥያቄ ተጠይቀዋል:: ለዚህም ሁሉም መምህራን (100%) ይህ ነው የሚባል የነጥብ መስጫ ዘዴ ባንጠቀምም እንደ ምዘናዎቹ አይነት እና አላማ የተለያዩ የመመዘኛ መስፈርቶችን አዘጋጅተን እንጠቀማለን:: በእነዚህም መሰረት ለእያንዳንዱ ተማሪ ስራ ነጥብ /ማርክ/ እንሰጣለን በማለት መልሰዋል:: ስለዚህ በክለሳ ድርሳን 2.11 ላይ በተከታታይ ምዘና ሂደት የተለያዩ የነጥብ መስጫ ዘዴዎች እንዳሉ በምሁራን ተገልጿል:: መምህራንም የምንጠቀመው ዘዴ ይህን ነው ብለው በስያሜ ደረጃ ባይጠቅሱም የተለያዩ መስፈርቶችን እንደሚጠቀሙ ለማወቅ ተችሏል::ይህ

ደግሞ የተማሪዎችን ስራ በእኩል አይን አይቶ ትክክለኛ ነጥብ በመስጠት በኩል የራሱ የሆነ አዎንታዊ ጎን ይኖረዋል::

### 4.6.2 ስለመምህራን የመመዘኛ መስፈርት ዝግጅት እና የነጥብ አሰጣጥ የተማሪዎች ምላሽ

ሠንጠረዥ፡12. ስለመምህራን የመመዘኛ መስፈርት ዝግጅት እና የነጥብ አሰጣጥን በተመለከተ የተማሪዎችን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ዝርዝር ጥያቄ | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | ለመወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | |
| | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 4. መምህራን ስራዎቻችንን የሚያርሙት የመመዘኛ መስፈርቶችን አዘጋጅተው በመጠቀም ነው:: | 4 | 8.33 | 6 | 12.5 | 22 | 45.83 | 6 | 12.5 | 10 | 20.83 |
| 5. የመመዘኛ መስፈርቶቹንም ያሳውቁናል:: | 5 | 10.41 | 7 | 14.58 | 13 | 27.08 | 15 | 31.25 | 8 | 16.66 |
| 14. በግል ወይም በቡድን ለምንሰራቸው ስራዎች የሚመጥን ትክክለኛነጥብ/ማርክ/ ይሰጡናል :: | 11 | 22.91 | 13 | 27.08 | 11 | 22.91 | 11 | 22.91 | 2 | 4.16 |

ሰንጠረዥ 12 የሚያመለክተው ከሁለቱም ዩኒቨርሲቲ በጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎችን ምላሽ ነው:: በተናጠል የተሰጡትን ምላሽ ስንመለከት ለሦስቱም ጥያቄዎች የቀረቡትን አምስት አማራጮች የመረጡ ተማሪዎች ቁጥር እጅግ ተቀራራቢ ነው:: (አባሪ ስድስትን ይመልከቱ):: በዚሁ ሰንጠረዥ አጠቃላይ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎችን ምላሽ ስንመለከት በተራ ቁጥር (4) ለቀረበው ጥያቄ አብዛኛዎቹ 45.83% ተምሪዎች "ለመወሰን ያስቸግረኛል" በማለት ሲመልሱ ከዚህ ቀጥሎ ከፍተኛ ውን ቁጥር የሚይዙት 20.83% ተማሪዎች ደግሞ "በጣም አልስማማም" በማለት መልሰዋል::

ይህም ውጤት ተማሪዎች ስራዎቻቸው የሚታረሙት መምህሮቻቸው በሚያዘጋጇቸው የመመዘኛ መስፈርቶች መሰረት ይሆን አይሆን የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ያስረዳል::

በዚሁ ሰንጠረዥ ለጥያቄ ተራ ቁጥር (5) ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው 31.25% የሚሆኑ ተማሪዎች “አልስማማም” ሲሉ መልስ ሰጥተዋል:: 27.08% ሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ “ለመወሰን ያስቸግረኛል” የሚለውን አማራጭ በመምረጥ መልሰዋል:: ስለዚህ ይህ ውጤተ ተተኳሪ መምህራን የተማሪዎችን ስራዎች በምን መስፈርት እንደሚ መዝኑ በቅድሚያ ለተማሪዎች እንደማያሳውቁ ያስረዳል:: ከላይ ከጥያቄ ቁጥር (4) የተገኘውም ውጤት ይህንኑ የሚያጠናክር ነው:: ምክንያቱም ተማሪዎች የሚሰሩት ስራ በምን እንደሚመዘን አለማወቃቸው መምህራን የመመዘኛ መስፈርቶችን ለተማሪ ዎች እንደሚያሳውቁ አድርገው ከሰጡት ምላሽ ጋር የሚስማማ ሆኖ አልተገኘም::

ስለዚህ ከላይ እንደተገለፀው የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን የመመዘኛ መስፈርት አዘጋጅተው እንደሚጠቀሙ ቢገልፁም ለተማሪዎቻቸው አለማሳወቃቸው በትክክል መስፈርት አዘጋጅተው የመጠቀማቸውን ነገር አጠራጣሪ ያደርገዋል::

ከዚሁ ሰንጠረዥ ሳንወጣ በተራ ቁጥር (14) ለቀረበው ጥያቄ 22.91% እና 27.08% የሚሆኑ ተማሪዎች በቅደም ተከተል “በጣም እስማማለሁ” እና “እስማማለሁ” በማለት ምላሽ ሰጥተዋል:: 27.07% የሚሆኑት ደግሞ አለመስማማታቸውን ገልፀዋል:: ይህም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የእያንዳንዱ ተማሪ ስራ የሚወጥን እና ተማሪዎችን የሚያስማማ ትክክለኛ ነጥብ እንደሚሰጡ ያሳያል:: ከዚህም በተጨማሪ እንደ ተጠኚ መምህር ምላሽ የተማሪዎችን ስራዎች ለማረም ወይም ነጥብ ለመስጠት የተለያየ ዘዴዎችን ባይጠቀሙም በሚያዘጋጁት የመመዘኛ መስፈርት መሰረት ለተማሪዎች ትክክለኛ ነጥብ መስጠት መቻላቸውን ያስረዳል::

መምህራን ትክክለኛ ነጥብ መስጠታቸው ተማሪዎቻቸውን በትክክል ለመለየት ያስችላቸዋል:: ይህ ደግሞ ዝቅተኛ ውጤት ላመጡ ተማሪዎች የማሻሻያ ድጋፍ እና ጥሩ ውጤት ላመጡ ተማሪዎች ደግሞ የማጠናከሪያ እገዛ ለማድረግ ይረዳል::

## 4.7 በተከታታይ ምዘና ሂደት ስለውጤት አተረጓጎም የመምህራን ምላሽ

ለጥናቱ ተተኳሪ መምህራን በጥያቄ ተራ ቁጥር (11) “በተከታታይ ምዘና ሂደት የሚገኘውን መረጃ ወይም የተማሪዎችን ውጤት ይተረጉማሉ? የሚተረጉሙ ከሆነ የትኛውን ዘዴ ይጠቀማሉ?” የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሁሉም (100%) መምህራን የተማሪዎቻቸውን ውጤት እንደሚተረጉሙ ገልፀዋል:: ለዚህም የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህራን በመስፈርት ላይ ተመስርቶ የመተርጎም ዘዴ

(Criterion-referenced) እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ፣ የወሎ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ደግሞ እርስ በርስ በማወዳደር የመተርጎም ዘዴን (Norm-referenced) እንደሚጠቀሙ አስረድተዋል::

ይህንንም የመምህራን ምላሽ ለማረጋገጥ የጥናቱ ተተኳሪ ዩኒቨርሲቲዎች ያዘጋጇቸው የተከታታይ ምዘና መተዳደሪያ ደንቦች ተፈትሸዋል:: በዚህም መሰረት ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የተከታታይ ምዘና መተዳደሪያ ደንብ የውጤት አተረጓጎምን አስመልክቶ መምህራን (ክራይቴሪያን-ሪፈረንስድ) ዘዴን መጠቀም እንደሚኖርባቸው በግልፅ ያስረዳል:: (አባሪ አስራ ሁለትን ይመልከቱ):: የወሎ ዩኒቨርሲቲ የተከታታይ ምዘና ደንብ ደግሞ ይህን ጉዳይ በሚመለከት በዝርዝር ያስቀመጠው ነገር ባይኖርም ከመምህራን ምላሽ (ኖርም- ሪፈረንስድ) ዘዴን እንደሚጠቀሙ ለማወቅ ተችሏል::

ስለዚህ የመምህራንም ምላሽ ሆነ የሰነድ ፍተሻው ውጤት የሚያመለክተው የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ዩኒቨርሲቲዎቻቸው ባዘጋጁት የተከታታይ ምዘና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተማሪዎችን ውጤት መተርጎማቸውን፣ ከውጤት መተርጎሚያ ዘዴዎችም ሁለቱ መምህራን (ክራይቴሪያን- ሪፈንስድ)፣ሁለቱ መምህራን ደግሞ (ኖርም-ሪፈንስድ) ዘዴን መጠቀማቸውን ነው:: ይህ ማለት ደግሞ የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ውጤት የሚነፃፀረው ገና ከመነሻው በተቀመጡ ዝርዝር የትምህርት አላማዎችና የማለፊያ ነጥብ ህጎች ወይም መስፈርቶች ጋር ሲሆን የወሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ውጤት ደግሞ የሚነፃፀረው ከሌሎች ተፈታኞች ወይም ተማሪዎች ውጤት ጋር ነው::

በምዕራፍ ሁለት 2.13 ላይ በተገለፀው የምሁራን ሐሳብ መሰረት መምህራን የሚያካሄዱት ተከታታይ ምዘና ዋና አላማ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረበላቸውን ትምህርት በሚፈለገው መጠን መቅሰማቸውንና አለመቅሰማቸውን እንዲሁም የተለያዩ ክሂሎችን፣ ዝንባሌዎችን ወዘተ እያዳበሩ መሆናቸውን መፈተሸ ስለሆነ ክራይቴሪያን ሪፈንስንድ የውጤት መተርጎሚያ ዘዴን መጠቀም አለባቸው:: ከዚህ አንፃር መምህራን የሰጡትን ምላሽ እና ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው ውጤት ከንድፈ ሀሳቡ ጋር በከፊል የሚስማማ መሆኑ ተረጋግጧል::

## 4.8 በተከታታይ ምዘና ሂደት ከተማሪዎች የሚገኙ መረጃዎችን ወይም ውጤቶችን መሰረት በማድረግ የሚደረጉ ድጋፎችን በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.8.1 የተማሪዎች ውጤቶችን መሰረት ያደረጉ ድጋፎችን በተመለከተ የመምህራን ምላሽ

ለመምህራን በቀረበው ቃለ መጠይቅ ከጥያቄ ተራ ቁጥር (12) ጋር ተያይዞ "ከተከታታይ ምዘና የሚገኘውን መረጃ ወይም ውጤት ለምን ለምን አገልግሎት ያውሉታል?" የሚል ጥያቄ ተጠይቀው ሦስቱ መምህራን (75%) ለተለያዩ አገልግሎቶች እንደሚጠቀሙበት ገልፀዋል:: እነዚህም:-

- ለተማሪዎችም ሆነ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ለማድረግ፣
- ተማሪዎችን ለመለየት፣ በዚህም መሰረት ዝቅተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ተማሪዎች ተጨማሪ የማሻሻያ ትምህርት ለመስጠት ፣
- ጥሩ ውጤት ላመጡ ተማሪዎች የማበረታቻ ሽልማቶችን ለመስጠት እና
- የራሳችንን የማስተማር ዘዴ ለማሻሻል የሚሉ ናቸው::

አንደኛው የወሎ ዩኒቨርሲቲ የስነ-ልሳን መምህር የተማሪዎችን ውጤት የሚጠቀሙበት የተማሪዎችን ውጤት (Grade) ሰርቶ ለሚመለከታቸው አካላት ለማቅረብ ወይም ሪፖርት ለማድረግ ብቻ እንጂ ለሌላ ለምንም አገልግሎት እንደማያውሉት ገልፀዋል:: ለዚህም ምክንያታቸው ካለብኝ የጊዜ እጥረት የተነሳ የተለያዩ እገዛዎችን ማድረግ ስለማልችል የሚል ነው::

በተጨማሪ የደብረብርሃን ተተኳሪ መምህራን እንደገለፁት በዩኒቨርሲቲው የተከታታይ ምዘና አሰራር መሰረት ትምህርት በተጀመረ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ተማሪዎች ተለይተው ደከም ላሉ ተማሪዎች ድጋፍ ይደረግላቸዋል:: እንዲሁም ከማጠቃለያ ፈተና በፊት በተከታታይ ምዘና ከ60% ያጠራቀሙት ውጤት ታይቶ ዝቅተኛ ውጤት ላመጡ ተማሪዎች የማጠቃላያ ፈተና ላይ ከመቀመጣቸው በፊት የማጠናከሪያ ትምህርት ይሰጣቸዋል:: አጠቃላይ ከመቶ ያገኙት ውጤት ከ50% በታች ከሆነ ደግሞ የማጠናከሪያ ትምህርት ወስደው በድጋሚ ይፈተናሉ:: እነሱም ይህንኑ አሰራር ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል::

ይህ የመምህራን ምላሽ ውጤት ተጠኚ መምህራን የተከታታይ ምዘና ውጤቶችን መሰረት አድርገው ተማሪዎቻቸውን በመለየት የማሻሻያ እና የማጠናከሪያ እገዛዎችን ማድረጋቸውን ያሳያል::

### 4.8.2 መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚያደርጉትን ድጋፍ በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ

የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት የምናሰባስባቸው የተማሪዎች ውጤቶች በሚያሳዩን ምስል መሰረት ለተማሪዎቻችን የተለያዩ እገዛዎችን እናደርጋለን ብለው የሰጡትን ምላሽ ለማረጋገጥ ይህን የተመለከተ ጥያቄ ተማሪዎችም ተጠይቀዋል:: የሰጡትም ምላሽ እንደሚከተለው ተተንትኗል::

ሠንጠረዥ:13. መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚያደርጉትን ድጋፍ በተመለከተ ተማሪ ዎች የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| ዝርዝር ጥያቄ | በጣም እስማማለሁ | | እስማማለሁ | | ለመወሰን ያስቸግረኛል | | አልስማማም | | በጣም አልስማማም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | | ብዛት | |
| | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 6. ጠንካራና ደካማ ጎናችንን በመለየት የማበረታቻ ወይም የማሻሻያ ድጋፎችን ይሰጡናል :: | 13 | 27.08 | 14 | 29.16 | 10 | 20.83 | 8 | 16.66 | 3 | 6.25 |
| 15. በተከታታይ ምዘና ሂደት የምናስመዘግ- በውን ውጤት መዝግቦ መያዝ እንጂ ከውጤታችን በመነሳት የሚደረግልን እገዛ የለም:: | 8 | 16.66 | 8 | 16.66 | 8 | 16.66 | 15 | 31.25 | 9 | 18.75 |

ሠንጠረዥ 13 እንደሚያሳየው ተራ ቁጥር (6) ላይ ለቀረበው ጥያቄ 27.08% የሚሆኑ ተማሪዎች "በጣም እስማማለሁ"፣29.16% ተማሪዎች "እስማማለሁ" ሲሉ፣ 16.66% እና 6.25% የሚሆኑ ደግሞ ተማሪዎች በቅደም ተከተል "አልስማማም" እና "በጣም አልስማማም" በማለት መልሰዋል:: ቀሪዎቹ 20.83% ተማሪዎች ለመወሰን መቸገራቸውን ገልፀዋል:: በዚህ ውጤት መምህራን የተለያዩ ድጋፎችን ለተማሪዎች አለመስጠታቸውን የተወሰኑ ተማሪዎች መግለፃቸው በዚህ ረገድ መጠነኛ ድክመት መኖሩን የሚጠቁም ቢሆንም መምህራን ተማሪዎችን በመለየት የማጠናከሪያ ድጋፎችን እንደሚሰጡ ማወቅ ይቻላል::

ከዚህ በተጨማሪ ለጥያቄ ተራ ቁጥር (15) አብዛኛዎቹ 31.25% እና 18.75% የሚሆኑት ተማሪዎች በተከታታይ ምዘና ሂደት ከሚያስመዘግቧቸው ውጤቶች በመነሳት የሚደረግላቸው እገዛ እንዳለ ምላሽ ሰጥተዋል:: የቀሩት 33.32% የሚሆኑት የጥናቱ ተሳታፊዎች ደግሞ እገዛ እንደሌለ በሰጡት መልስ ገልፀዋል:: ይህም ከላይ ከጥያቄ ቁጥር (6) የተገኘውን ውጤት የሚያጠናክር ወይም የሚደግፍ ነው::

ይህንኑ ጉዳይ በሚመለከት ከሁለቱ ዩኒቨርስቲዎች በጥናቱ የተሳተፉ ተማሪዎች በተናጠል የሰጡትን ምላሽ ስንመለከት ከደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተሳታፊዎች ከፍተኛ ውን ቁጥር የሚይዙት ተማሪዎች በውጤታቸው መሰረት ከመምህሮቻቸው የተለያዩ እገዛዎችን እንደሚያገኙ ሲገልፁ ከወሎ ዩኒቨርሲቲ ተሳታፊዎች ደግሞ በውጤታቸው መሰረት የሚደረግላቸው እገዛ እንዳለ የገለፁት ጥቂቶቹ ናቸው:: (አባሪ ስድስትን ይመልከቱ):: በጥቅሉ ሁሉም የሰጡት ምላሽ ሲታይ መጠኑ ወይም ደረጃው የሚለያይ ቢሆንም ተጠኚ መምህራን ለተማሪዎች የተለያዩ ድጋፎችን እንደሚሰጡ ማረጋገጥ ተችሏል::

በአጠቃላይ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ መምህራን ከሰጡት ምላሽ ጋር ተመሳሳይ መሆኑ ተረጋግጧል:: ይህም በምዕራፍ ሁለት 2.2 ላይ ተማሪዎችን መገምገም ብቻ ሳይሆን ባስመዘገቡት ውጤት ላይ ተመስርቶ የተለያዩ ውሳኔዎችን ማስተላለፍ፣ የተማሪዎችን ችግር መለየትና አስፈላጊውን ድጋፍና እርማት መስጠት ነው ተብሎ ከተገለፀው የምሁራን ሀሳብ ጋር የሚጣጣም ነው::

## 4.9 ስለተከታታይ ምዘና ሰነዶች አያያዝ እና አጠቃቀም የመምህራን ምላሽ እና ከሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ከተከታታይ ምዘና ሰነዶች መካከል የተከታታይ ምዘና እቅድ፣ የኮርስ ቢጋር ፣የተማሪዎች ፈተናዎች፣ የግልና የቡድን ስራዎች ከሚዛመዷቸው ነጥቦች ጋር ከፍ ብሎ ተተንትነዋል:: በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ደግሞ የተማሪዎች የትምህርት ሁኔታ መከታተያ መዝገብ፣ ሰነደ ትምህርት (Portfolio) እና የውጤት ማጠራቀሚያ ቅፆች (Mark lists) ሰነዶች ታይተዋል::

ለጥናቱ ተሳታፊ መምህራን በቃለ መጠይቅ ተራ ቁጥር (12) "የተማሪዎችን የትምህርት ሁኔታ መከታተያ መዝገብ አዘጋጅተው ይጠቀማሉ?" የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሁሉም መምህራን (100%) የተማሪዎቻቸውን የትምህርት አቀባበል

ሁኔታ እና መሻሻል እየተከታተሉ ለመያዝ የሚያስችል መዝገብ አዘጋጅተው እንደማይጠቀሙ ገልፀዋል። በሰነድ ፍተሻውም የዚህ አይነት መዝገብ በሁሉም መምህራን ዘንድ እንደሌለ፣ በክፍል ውስጥ ምልከታም መምህራን ከተማሪዎች የሚገኙ መረጃዎችን ወይም የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ እንደማይመዘግቡ ተረጋግጧል።

ከዚህ አንፃር በምእራፍ ሁለት 2.10 ላይ ተከታታይ ምዘና በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ በተማሪዎች መካከል በትምህርት፣ በኢኮኖሚ እና በባህል ዳራ መለያየት ምክንያት የሚፈጥር የውጤት ልዩነትን ለማጥበብ የሚያስችል መሆኑን ተገልጿል። ለዚህ ደግሞ በቅድሚያ የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ እየተከታተሉ መመዝገብ ያስፈልጋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ለመምህራን የቀረበው ጥያቄ "የተማሪዎችን የቀከታታይ ምዘና ውጤት እንደምናዘው አይነት መዝግበው ይይዛሉ?" የሚል ነው። ለቀረበውም ጥያቄ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን በሙሉ የተማሪዎቻቸውን ውጤቶች እንደምዘናዎቹ አይነት መዝግበው እንደሚይዙ እና ከላይ እንደተገለፀው ውጤቱን ለተለያዩ አገልግሎቶች እንደሚጠቀሙበት አስረድተዋል። ይህንን የመምህራን ምላሽ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በውጤት ማጠራቀሚያ ቅፆች ላይ ፍተሻ ተካሂዷል። በዚህም መሰረት ሁሉም መምህራንን የተማሪዎቻቸውን ውጤት መዝግበው እንደሚይዙ ማረጋገጥ ተችሏል። ነገር ግን ውጤቶቹ የተገኙበትን የምዘና አይነት የሚገልፁት የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተጠኚ መምህራን ቅፆች ብቻ ናቸው። ይህ የሰነድ ፍተሻ ውጤት መምህራን ከሰጡት ምላሽ ጋር የሚጣረስ ነው።

በምዕራፍ ሁለት 2.7 ላይ Elington and Earl (1997) እንዳስረዱት መምህራን በተለያዩ የምዘና ስልቶች አማካኝነት የተሰበሰቡትን የተማሪዎች ውጤቶች በጥንቃቄ መዝግቦ መያዝ ይኖርባቸዋል። ውጤቶቹም እንደ ምዘናው አይነት በአግባቡ ተመዝግበው ሊቀመጡ ይገባል። ምክንያቱም የተማሪዎችን ውጤት በተመለከተ ለተማሪዎችና ለሚመለከታቸው አካላት መረጃ ለመስጠት ወሳኝነት አለው። ይህ ካልሆነ የተማሪዎች ስራ ትኩረት ስለሚያጣ የመማር ፍላጎታቸው ሊቀንስ ይችላል።

ከዚህ አንፃር የተገኘውን ውጤት ስንመለከት ተጠኚ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ውጤቶች በአግባቡ መዝግበው መያዛቸው ከንድፈ ሀሳቡ ጋር የሚጣጣም ሲሆን

ከውጤቶቹ ጋር የምዘናዎቹን አይነት አያይዘው አለማስቀመጣቸውን ግን የሚጣረስ መሆኑ ታውቋል::

ሌላው መምህራን ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት ያከናወኗቸው ተግባራት ተያይዘው የሚቀርቡበትን ወይም የሚቀመጡበትን ሰነደ ትምህርት ተማሪዎች እንዲያዘጋጁ ያደርጉ እንደሆነ ተጠይቀዋል:: ለዚህም ከወሎ ዩኒቨርሲቲ የድርሰት መምህር፣ ከደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ የስነ-ልሳን መምህር ተማሪዎችን እንደሚያዙ ወይም እንደሚያስሩ ገልፀዋል:: ሌሎቹ መምህራን (50%) — ግን ይህን ስልት እንደማይተገብሩት ተናግረዋል:: ስለዚህ ምክንያታቸው አሁንም በድጋሚ የጊዜ ጉዳይ መሆኑን ገልፀዋል::

በሰነድ ፍተሻው እንደታየው የተማሪዎችን ሰነደ ትምህርት የሚመለከት መረጃ በሁሉም መምህራን በኩል አልተገኘም :: ተማሪዎች እንዳላዘጋጁ ማረጋገጥ ተችሏል:: ይህ ደግሞ ከመምህራን ምላሽ ውጤት ጋር ይጣረሳል::

ከዚህ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ምዕራፍ ሁለት 2.9 ተራ ቁጥር 10 ላይ Puhl (1997) እንደገለፀውት ሰነደ ትምህርት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ቆይታቸው የሚሰሯቸውን ክንዋኔዎች፣ ጥረቶች፣ መሻሻሎችንና ብቃቶችን የሚያሳይ በመሆኑ ለቋንቋ ትምህርት ምዘና ተመራጭ ነው:: ምክንያቱም ተማሪዎች ምን እንደተረዱና ምን አይነት ክሂሎችን እንዳዳበሩ ለማወቅና በየጊዜው ያሳዩትን ለውጥ ለመከታተል ይረዳል፤ከፈተና በተሻለ ሁኔታ ስለተማሪዎች በቂ መረጃ ይሰጣል:: ይሁን እንጂ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን እንደ ቋንቋ መምህርነታቸው ሰነድ ትምህርትን እንደማይጠቀሙ ለማወቅ ተችሏል::

በአጠቃላይ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ እና ከሰነድ ፍተሻው በተገኙ መረጃዎች መሰረት የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት የተማሪዎችን የትምህርት ሁኔታ ለመከታተል የሚያስችል መዝገብ አዘጋጅተው እንደማይጠቀሙ፣ የተማሪዎችን ውጤት ሲመዘግቡ የምዘናውን አይነት እማይገልፁ እና ሰነደ ትምህርትን እንደማይጠቀሙና በሰነድ ደረጃም እንደሌላቸው ተረጋግጧል::

## 4.10 ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.10.1 ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ስለሚያጋጥሙ ችግሮች የመምህራን ምላሽ

በመምህራን ቃለ መጠይቅ "ተከታታይ ምዘናን ለመተግበር ወይም በሚተገብሩበት ጊዜ የሚያጋጥመዎት ችግሮች አሉ? ካሉ ቢገልፁልኝ?" የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸዋል:: በዚህም መሰረት ሁሉም መምህራን (100%) የሚያጋጥሟቸው ችግሮች እንዳሉ ገልፀዋል:: የዘረዘሯቸው ችግሮችም የሚከተሉት ናቸው::

**1. የመምህራን የስራ ጫና**

ምዕራፍ ሦስት ላይ እንደተገለፀው ተተኳሪ መምህራን በሳምንት ከ9-12 ክፍለ ጊዜያት ያስተምራሉ:: ከዚህም በተጨማሪ በተለይ የወሎ ዩኒቨርስቲ የስነ-ልሳን መምህር እንደገለፁት የተለያዩ የስራ ሃላፊነቶችን ይወጣሉ:: የመደበኛ፣ የክረምት እና የማታ ተማሪዎችን የመመረቂያ ፅሁፎች ያርማሉ፤ ያማክራሉ:: ከዚህ አንፃር ተከታታይ ምዘናን በትክክል መተግበር እንዳልቻሉ አስረድተዋል::

**2. የተማሪዎች ቁጥር መብዛት**

በምልከታ ወቅት እንደታየው በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ትምህርት ክፍል 61 የሦስተኛ አመት ተማሪዎች፣ በወሎ ዩኒቨርሲቲ 86 የሁለተኛ አመት ተማሪዎች በአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ እንዲማሩ ተደርጓል:: እንዲሁም የወሎ ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህራን እንደገለፁት የአንድ ምድብ (section) ተማሪዎች ሁል ጊዜ ወይም ሁሉንም የትምህርት አይነቶች በአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ እንዲማሩ ይደረጋል:: በዚህ ጊዜ የማስተማሪያ አዳራሽ (Lecture Hall) ለተመደቡና ከፍተኛ ቁጥር ላላቸው ተማሪዎች የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ተግባራትን መስጠት፣ እያንዳንዱን ተማሪ እየተዘዋወሩ መከታተል እና ምጋቤ ምላሽ መስጠት እንደማይችሉ ገልፀዋል::

**3. የቁሳቁስ (የማቴሪያል) እጥረት**

መምህራን እንደገለፁት በየጊዜው የተለያዩ የምዘና ተግባራትን ተማሪዎች እንዲሰሩና እንዲለማመዱ ለማድረግ የወረቀት እጥረት ያጋጥማቸዋል:: በተጨማሪም በቤተ መፃህፍት ውስጥ በቂ ማጣቀሻ መፃህፍት ባለመኖራቸው ምክንያት ለተማሪዎች የሚሰጧቸው የምዘና ተግባራት የተወሰኑ ናቸው::

4. የጊዜ እጥረት

የጊዜ እጥረት ከላይ እንደተገለፀው በስራ ጫና ምክንያት ሊከሰት የሚችል ችግር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የጥናቱ ተተኳሪ ዩኒቨርሲቲዎች አዳዲስ እና ግንባታቸውን ያልጨረሱ በመሆናቸው ተማሪዎችን የሚቀበሉት ከመደበኛው የትምህርት መጀመሪያ ጊዜ ትንሽ ዘግይተው ነው፡ በዚህ ምክንያት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ትምህርቱን ለመሸፈን ሲባል ብሎክ ቲቼንግ (Block Teaching) የማስተማር ስልትን ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም መምህራን በተሰጠው አጭር ጊዜ ውስጥ የትምህርቱን ይዘቶች መሸፈን ላይ እንደሚያተኩሩ በዚህም ምክንያት ተከታታይ ምዘናን በአግባቡ መተግበር እንዳልቻሉ ያስረዳሉ፡፡

5. የተማሪዎች አመለካከት

ተማሪዎች በአብዛኛው ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ብቻ አጥንተው መፈተንን ይመርጣሉ፡፡ የተለያዩ የግል የቡድን ስራዎችን ወዘተ የምዘና ተግባራትን በተደጋጋሚ እንዲሰሩ በሚደረጉበት ጊዜ መስራት ያለመፈለግና የመሰላቸት ባህሪ እንደሚያሳዩ መምህራን ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ምላሽ መምህራን ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ለማድረግም ሆነ በሚያደርጉበት ጊዜ የስራና የተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ የማቴሪያልና የጊዜ እጥረት፣ የተማሪዎች አመለካከት እና የስልጠና አሰጣጥ ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸው ያስረዳል፡፡

በመጨረሻም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን በስነ-ልሳንና በበሳል ድርሰት ትምህርቶች ተከታታይ ምዘና በትክክል እንዲተገበር ምን መደረግ እንዳለበት ተጠይቀዋል፡፡ ለዚህም ጥያቄ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ ወይም ተመጣጣኝ ቢሆን፣ የመምህራን የስራ ጫና ቢቀንስ፣ ለመምህራን ወቅታዊ ሆነ ስልጠና ቢያገኙ፣ በቂ የማቴሪያል አቅርቦት ቢኖር፣ መምህራን ሳይሰላቹ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ቢችሉ፣ የመምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር እና ያሉባቸው ችግሮች በሚመለከታቸው አካላት ቢታይና ክትትል ቢደረግበት እንዲሁም በመምህራን በኩል የማሳመን ፣ በተማሪዎች ዘንድ ደግሞ ስለ ጉዳዩ ግንዘቤ የመፍጠር ስራ ቢሰራ የተሻለ ነው በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

### 4.10.2 መምህራን ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ስለ ሚስተዋሉ ችግሮች የተማሪዎች ምላሽ

የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በቀረበላቸው የፅሁፍ መጠይቅ በበሳል ድርሰትና በስነ-ልሳን ትምህርቶች ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ያስተዋሏቸው ወይም ያጋጠሟቸው ችግሮች ካሉ እንዲጠቅሱ በተጠየቁት መሰረት የተለያዩ ችግሮች እንዳሉ ገልፀዋል። አብዛኛዎቹ ተማሪዎችም በተደጋጋሚ የጠቀሷቸው ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- በቤተ መፃህፍት ውስጥ ያሉ መፃህፍት ቁጥር አነስተኛ መሆንና የቤተ መፃህፍቱ ሰራተኞች ተማሪውን እኩል አለማስተናገድ፣
- መምህራን የሚሰጡትን የምዘና ተግባራት የተማሪውን የእውቀት ደረጃ እና የማጣቀሻ መፃህፍትን ከግምት ውስጥ ያላስገባ መሆን ፣
- መምህራን በሚይዟቸው ኮርሶችና የስራ ጫናዎች ብዛት ምክንያት በመዳከምና በመሰላቸት የትምህርቱን መሰረታዊ እውቀት አለማግኘት ፣
- የራሳችንን ስራ በራሳችን እንዲሁም ከጓደኞቻችን ጋር እንድንገማገም አለማድረግ፣
- የፈጠራ ስራዎቻችንን የምናቀርብበት እድል አለማግኘት ፣
- ድንገቴ ፈተናዎችን መፈተን ፣
- በአብዛኛው የምንሰጠው የምዘና ተግባር የቡድን ስራ መሆን እና ስራው በተወሰኑ ተማሪዎች ላይ የተወሰነ በመሆኑ የእያንዳንዱ ተማሪ ችሎታ ወይም አስተዋፅኦ የሚለካ አለመሆን ፣

ይህ የተማሪዎች ምላሽ በመምህራን በኩል የተጠቀሱ ችግሮች ተማሪዎችም ያስተዋሏቸው መሆኑን ያመለክታል። ከዚህ በተጨማሪ ከላይ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መምህራን ከሰጧቸው ምላሾች ጋር የሚቃረኑ ሀሳቦች መኖራቸውን እና በተጠኚ መምህራን ተከታታይ ምዘና አተገባበር ዙሪያ የተለያዩ ችግሮች እንዳሉ ያስረዳል።

ከዚህም በተጨማሪ ለተማሪዎች በቀረበው የምርጫ ጥያቄ ተራ ቁጥር (1) ላይ ተከታታይ ምዘና በአብዛኛው በየትኞቹ ትምህርቶች ላይ እንደሚተገበር የተጠየቁ ሲሆን ለዚህም 20.83% ተማሪዎች በስነ-ልሳን ትምህርቶች፣52.08% ተማሪዎች በበሳል ድርሰት ትምህርቶችና እና 27.08% ተማሪዎች ደግሞ በሁለቱም ትምህርቶች የሚሉ አማራጭ መልሶችን በመምረጥ መልሰዋል። ይህም ተከታታይ ምዘናን የሁለቱም ትምህርቶች መምህራን የሚተገብሩት ቢሆኑም በአተገባበር ደረጃ በስነ-ልሳን መምህራን በኩል ድክመት መኖሩን ያመለክታል። በተለይ በወሎ ዩኒቨርሲቲ የስነ-ልሳን ትምህርቶችን በሚያስተምሩ መምህራን የተከታታይ የምዘና ትግበራ ላይ ችግሩ

የጎላ መሆኑን ያሳያል። ምክንያቱም በስነ-ልሳን ትምህርቶች ላይ እንደሚተገበር የገለፁት የወሎ ዩኒቨርሲቲ ተሳታፊ ተማሪዎች ቁጥር አምስት ብቻ ነው።

በምርጫ ጥያቄ ተራ ቁጥር (2) ደግሞ ተማሪዎች ከላይ ለሰጡት ምላሽ ምክንያታቸውን ተጠይቀው በበሳል ድርሰት ትምህርቶች ላይ እንደሚተገበር ከገለፁት ውስጥ 37.5% ተማሪዎች ኮርሶቹ በባህሪያቸው ተከታታይ ምዘናን ለመተግበር ስለሚያስችሉ ብለው ሲመልሱ፣ 8.33% ተማሪዎች ደግሞ የኮርሶቹ መምህራን ተከታታይ ምዘናን በተለያየ መንገድ ለመተግበር ስለሚጥሩ ነው ሲሉ፣6.25% ተማሪዎች ሁለቱም የሚለውን አማራጭ መልስ መርጠዋል። ከዚህ በተጨማሪ ሌላ ካለ በሚል በቀረበው ክፍት ቦታ የበሳል ድርሰት ትምህርት ደጋግሞ በመለማመድ የሚዳብር በመሆኑ በተከታታይ የተለያዩ ስራዎችን መስራት ስለሚያስፈልግ ወዘተ የሚሉ በትምህርቱ ባህሪ ምክንያት ተከታታይ ምዘናው የሚተገበር መሆኑን የሚገልፁ ምላሾችን ሰጥተዋል።

በሌላም በኩል በስነ ልሳን ትምህርቶች ላይ ይተገበራል ያሉ ተማሪዎች ምክንያታቸው ኮርሶቹ በባህሪያቸው ተከታታይ ምዘናን ለመተግበር ስለሚያስችሉ መሆኑን ገልፀዋል። እንዲሁም ሌላ ካለ በሚለው ክፍት ቦታ የሥነ ልሳን ትምህርት ትንሽ ከበድ ስለሚል ተከታታይ ምዘና ስለሚያስፈልገው የሚሉ ምላሾችን ሰጥተዋል።

በሁለቱም ትምህርቶች ላይ ይተገበራል ያሉ የተወሰኑ ተማሪዎች ደግሞ ሁለቱንም ምክንያቶች የመረጡ ሲሆን በተጨማሪም ሁለቱም ትምህርቶች የዕለት ተዕለት ተግባርንና ልምምድን የሚጠይቁ ፣የሁለቱም ኮርሶች መምህራን ለተማሪዎች እውቀትና ውጤት የሚጨነቁ በመሆናቸው ነው በማለት መልሰዋል።

በአጠቃላይ ከዚህ የተማሪዎች ምላሽ ውጤት ተተኳሪ መምህራን ተከታታይ ምዘናን እንደሚተገብሩ ነገር ግን በስነ -ልሳን በተለይም በወሎ ዩኒቨርሲቲ የስነ-ልሳን መምህራን በኩል ያተገባበር ችግር እንዳለ ለማወቅ ተችሏል።

በመጨረሻም ተማሪዎች በበሳል ድርሰትና በስነ-ልሳን መምህራን ተከታታይ ምዘና አተገባበር ዙሪያ አስተያየት እንዲሰጡ ተጠይቀው የተለያዩ ይበል የሚያሰኙና በዚህ መንገድ ቢሻሻሉ ጥሩ ነው የሚሉ አስተያየቶችን ሰጥተዋል። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፤

- መምህራን በትምህርቱ (በኮርሱ) ላይ የጠለቀ እውቀት እንዲኖረንና የሙያው ባለቤት እንድንሆን የሚስችሉ ጥረቶችን እያደረጉ ነው ። ምዘናዎቹም የድርሰት አጻጻፋችን እንዲዳብር እና ለትምህርቱ ትኩረት እንዲሰጥ አድርገውናል። ስለዚህ በዚሁ ቢቀጥሉ ጥሩ ነው።
- ነገር ግን የሚሰጡትን የግልና የቡድን ስራዎች እንዲሁም ፈተናዎች የመፃህፍት እጥረቱንና የተማሪውን ግንዛቤ ታሳቢ ያደረገ ቢሆን ፣
- ምዘናዎቹ ሁሉንም የትምህርት ይዘቶች የሚዳስሱ ቢሆኑ ፣
- የተለያዩ ምዘናዎች በተደጋጋሚ ቢሰጡ እና ምዘናው እንዴት እንደሚሰራ፣ ፈተናው ምን ምን ይዘቶችን እንዳካተተ ፣መቼ እንደሚሰጥና በምን መስፈርት እንደሚታረም ቀድመው ቢያሳውቁን ፣
- ዝቅተኛ ውጤት ላላቸው ተማሪዎች የተጠናከረ የማሻሻያ ትምህርት ቢሰጥ፣

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦች

በምዕራፍ አንድ እንደተጠቆመው የዚህ ጥናት ዋነኛ አላማ በደብረብርሃን እና በወሎ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ትምህርት ክፍሎች የበሳል ድርሰትና የስነ-ልሳን ትምህርቶችን የሚያስተምሩ መምህራንን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ሁኔታን መፈተሽ ነው፡፡ በተጨማሪም በዚህ አብይ አላማ ስር ንዑሳን አላማዎች ተዘርዝረዋል፡፡

እነዚህን አላማዎች ከግብ ለማድረስ ከተተኳሪ መምህራን በምልከታ እና በቃለመጠይቅ፣ ከተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቅ እንዲሁም ከተከታታይ ምዘና ሰነዶች በሰነድ ፍተሻ አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበውና ተደራጅተው መጠናዊ እና አይነታዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ በትንተናው የተገኙ ውጤቶችም እንደሚከተለው ጠቅለል ብለው ቀርበዋል፤

### 5.1 ማጠቃለያ

1. ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ስለተከታታይ ምዘና ስልጠና ያገኙ እንደሆኑ እና ስለተከታታይ ምዘና ምንነት፣ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ጥሩ ግንዛቤ እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡
2. ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የተከታታይ ምዘና እቅድ አዘጋጅተው እንደማይጠቀሙ ተረጋግጧል፡፡

   የኮርስ ቢጋሮችን በተመለከተም ሁሉም መምህራን አዘጋጅተው እንደሚጠቀሙ እና የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ዘዴዎችን እንደሚያካትቱ፣ ሆኖም ግን በኮርስ ቢጋሮቹ ላይ የምዘናዎቹን አይነትና ምዘናዎቹ ከስንት ፐርሰንት እንደሚያዙ ከመግለፅ ውጭ ምዘናዎቹ የሚሰጡበት አላማ እና ጊዜ ከግምት ውስጥ እንዳልገቡ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡
3. ተተኳሪ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በተለያዩ የተከታታይ ምዘና ስልቶች አማካኝነት እንደሚመዝኑ፣ ከእነዚህም መካከል የቃል ጥያቄ፣ የግል እና የቡድን ስራ፣ ሙከራና ፈተና እና በተማሪዎች ፊት እየወጡ ማቅረብ ስልቶችን በአብዛኛው እንደሚጠቀሙ፣ ነገር ግን የራስ ምዘና፣ ምልከታ፣ የመምህር ተማሪ ውይይት፣የፐሮጀክት ምዘና እና ስነደ ትምህርት ስልቶችን ከናካቴው እንዳላከናወኑ ተረጋግጧል፡፡

4. በተከታታይ ምዘና ሂደት ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ረገድ ጥናቱ ያተኮረባቸው መምህራን በተለያዩ የምዘና ተግባራት ላይ ወቅቱን የጠበቀ ቃላዊ እና ፅሁፋዊ ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡ ቢሆኑም ስህተትን ወይም ትክክለኛውን መልስ የሚጠቁሙ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት ላይ እንደሚያተኩሩበጥናቱ ተረጋግጧል፡፡
5. የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የተለያዩ የነጥብ /ማርክ/ መስጫ ዘዴዎችን ለይተው ባይጠቀሙም እንደምዘናው አይነትና አላማ የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም የተማሪዎችን ስራ እንደሚያርሙ ወይም ነጥብ እንደሚሰጡ፣ ይሁን እንጂ የመመዘኛ መስፈርቶቹን ለተማሪዎች ቀድመው እንደማያሳውቁ እና መስፈርቶ ቹን በማዘጋጀት ሂደት ተማሪዎችን እንደማያሳትፉ በጥናቱ ተደርሶበታል፡፡
6. የተከታታይ ምዘና አላማ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረበላቸውን ትምህርት በሚፈለገው መጠን መቅሰማቸውን፣ የተለያዩ ክሂሎችንና ዝንባሌዎችን ማዳበራቸውን መፈተሽ በመሆኑ የተማሪዎች ውጤት በመስፈርት ላይ ተመስርቶ (Criterion-referenced) ዘዴ መተርጐም ያለበት ቢሆንም የወሎ ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህራን ብቻ ይህን ዘዴ እንደማይጠቀሙ ተረጋግጧል፡፡
7. የተተኳሪ መምህራን የተከታታይ ምዘና ሰነዶች አጠቃቀምን አስመልክቶ የተማሪዎች የትምህርት ሁኔታ መከታተያ እና ሰነደ ትምህርት በመምህራን ዘንድ ተግባራዊ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ መዛግብት እንደሌሉ፣ የተማሪዎችን ውጤት በውጤት ማጠራቀሚያ ቅፆች ላይ መዝግበው እንደሚይዙ፣ ነገር ግን የወሎ ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህራን ቅፆች ውጤቶቹ ከተገኙበት የምዘና አይነቶች ጋር ተያይዘው የተቀመጡ እንዳልሆኑ የሰነድ ፍተሻው ውጤት አረጋግጧል፡፡
8. ጥናቱ ያተኮረባቸው መምህራን ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ ለማድረግ ወይም በሚያደርጉበት ጊዜ የሥራ ጫና፣ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ የቁሳቁስ (የማቴሪያል) እጥረት፣ የጊዜ እጥረት እና የተማሪዎች አመለካከት ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸው ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

## 5.2 የመፍትሔ ሐሳቦች

ከላይ የቀረቡትን የጥናቱን ውጤቶች መሠረት በማድረግ የሚከተሉት አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፤

1. ተከታታይ ምዘናን በአግባቡ ለመተግበር እቅድ ማዘጋጀትና በእቅዱም መመራት ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ በተተኳሪ መምህራን የተከታታይ ምዘና እቅድ

በማዘጋጀት እና በኮርስ ቢጋሮቻቸው ላይ የምዘና ትግባራትን አላማ እና የሚሰጡበትን ጊዜ አቅዶ በማስፈር ረገድ ችግሮች ይታያሉ። ስለዚህ ተማሪዎች የሚመዘኑባቸውን የምዘና ተግባራት አላማና ምዘናዎቹ የሚሰጡበትን ጊዜ በግልፅ አውቀው ራሳቸውን ማዘጋጀት እንዲችሉና ለትምህርቱ ትኩረት እንዲሰጡ መምህራን የተከታታይ ምዘና እቅድ ቢያዘጋጁ እና በኮርስ ቢጋሮቻቸው አማካኝነት ለተማሪዎቻቸው ቢያሳውቁ፣

2. ጥናቱ ያተኮረባቸው መምህራን የተለያዩ የተከታታይ ምዘና ዘዴዎችን መጠቀማቸው የሚበረታታ ቢሆንም የራስ ምዘና፣ የፕሮጀክት ምዘና፣ ስነደ ትምህርት ወዘተ ስልቶችን ተግባራዊ እንደማያደርጉ፣ የቡድን ስራን መጠቀም እንደሚያዘወትሩ ተረጋግጧል። ስለዚህ እነዚህ ስልቶች ለቋንቋ ትምህርት በተለይም ለስነ-ልሳን እና ለበሳል ድርስት ትምህርቶች ያላቸውን ከፍተኛ የሆነ ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት ፣የቡድን ስራዎች ውጤት በተወሰኑ ተማሪዎች ላይ ብቻ እንዳይወሰን በመከታተል፣ መምህራን የተለያዩ የምዘና ስልቶችን አፈራርቀው በመጠቀም ተማሪዎች የተለያዩ ክሂሎችን ማዳበር የሚችሉበትን መንገድ ቢያመቻቹ፣

3. የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ፈጣንና ወቅቱን የጠበቀ ምጋቤ ምላሽ መስጠታቸው ተገቢ እና የሚበረታታ ነው። ነገር ግን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጣቸው ስህተትን ወይም ትክክለኛውን መልስ ማሳወቅ ላይ ያተኮረ መሆኑ ተረጋግጧል። ይህ ደግሞ ተማሪዎች ሁልጊዜ ድክመታቸውን እንጂ ጠንካራ ጎናቸውን ለይተው እንዲያውቁት አያስችልም። ስለዚህ መምህራን በሁሉም ተማሪዎች የምዘና ተግባራት ላይ ምጋቤ ምላሽ ቢሰጡ፣ ምጋቤ ምላሹም ተማሪዎች ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን እንዲለዩ እና የመማር ፍላጎታቸው እንዲጨምር የሚያደርግ እንዲሆን ቢያደርጉ፣

4. መምህራን የመመዘኛ መስፈርቶችን በመጠቀም ለተማሪዎች ስራዎች ተገቢ እና ትክክለኛ ነጥብ መስጠታቸው ጥሩ ነው። ነገር ግን መስፈርቶችን በማዘጋጀት ወይም በማውጣት ሂደት ተማሪዎችን እንዳማያሳትፉና መስፈርቶቹንም ለተማሪዎች እንደማያሳውቁ ተረጋግጧል። ስለዚህ ተማሪዎች የሚሰጧቸውን የምዘና ተግባራት በመስፈርቶቹ መሰረት በትክክል እንዲሰሩ እና ለሚያገኙትም ውጤት ወይም ነጥብ ትክክለኛት ወይም ተገቢነት እርግጠኛ እንዲሆኑ፣ መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለተማሪዎች ቢያሳውቁ እና ከተማሪዎች ጋር በመመካከር መስፈርቶችን ቢያዘጋጁ፣

5. በተከታታይ ምዘና ሂደት የሚሰበሰቡ የተማሪዎች ውጤቶችን በመስፈርት ላይ ተመስርቶ የመተርጐም (Criterion-referenced) ዘዴን በመጠቀም የሚተረጉሙት

የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህራን ብቻ እንደሆኑ ተረጋግጧል። ስለዚህ የወሎ ዩኒቨርሲቲ መምህራንም የተከታታይ ምዘናን አላማ ለይቶ በማወቅ አላማውን ለማሳካት የሚያስችለውን የውጤት መተርጎሚያ (Criterion-referenced) ዘዴን ተግባራዊ ቢያደርጉ፣

6. ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የተማሪዎችን የትምህርት ሁኔታ መከታተያ እና ሰነደ ትምህርት መዛግብትን እንደማይጠቀሙ፣ እንዲሁም የወሎ ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪ መምህራን ቅፆች የምዘና ስልቶቹን አይነት የሚገልፁ እንዳልሆኑ ተረጋግጧል።ስለዚህ እነዚህ ተግባራት ተከታታይ ምዘናን ለመተግበር ወሳኝ መሆናቸው ታውቆ በዩኒቨርሲቲዎቹ የሚመለከታቸው አካላት መምህራንን በተለያዩ ስልጠናዎችና ማበረታቻዎች በመደገፍ የተማሪዎችን የትምህርት ሁኔታ መከታተያና ስነደ ትምህርት መዛግብትን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ጥረትና ክትትል ቢያደርጉ፣

በተጨማሪም በወሎ ዩኒቨርሲቲ ተከታታይ ምዘና እንዲተገበር ማዘዝ ብቻ ሳይሆን ልክ እንደ ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ በተለያዩ የተከታታይ ምዘና ስልቶች መሰረት የተሸነሸኑ የውጤት ማጠራቀሚያ ቅፆችን ለመምህራን አዘጋጅቶ መስጠትና በዚህም አማካኝነት ተተግባሪነታቸውን መቆጣጠርና መፈተሽ ቢችሉና መምህራንም የራሳቸውን ጥረት ቢያደርጉ፣

7. ተተኳሪ መምህራን ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት የተለያዩ ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸው በጥናቱ ተረጋግጧል። ስለዚህ ተተኳሪ ዩኒቨርሲቲዎች የመምህራን ቁጥር በመጨመር የመምህራንን የሥራ ጫና የመቀነስ፣ ተማሪዎችን ዘግይቶ በመቀበል ምክንያት የሚፈጥረውን የጊዜ እጥረት የማስተካከል፣ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎችን ቁጥር የማመጣጠን፣ አስፈላጊ ማቴሪያሎችን በበቂ ሁኔታ የማቅረብ፣ ስራ ቢሰሩ፣ መምህራንም በትምህርት ክፍላቸው ውስጥ እርስ በርስ በመወያየት፣ልምድ በመለዋወጥ ተማሪዎችንም በማወያየት ችግሮቹን ለማቃለል ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉ።

# ዋቢ ጽሑፎች

ሰለሞን ተሰማ ። (1987)። "የብጤ እርማት ተግባራዊነትና ውጤታማነት፤ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ገላጭ ጥናት።" ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

በድሩ ከድር። (1994) ። *የትምህርት ተከታታይ ምዘና ግምገማ ጽንሰ ሐሳቦችና ቴክኒኮች*። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ተስፋ አከለ። (2000)። "የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ፤ በትግራይ ክልል በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች።" ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ታጠቁ ታደለ እና ሌሎች። (1996)። *የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተከታታይ ምዘና ጋይድ*። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ትምህርት ሚኒስቴር ።(1986) ። *አጠቃላይ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ* ። አዲስ አበባ፣ በት.መ.ማ.መ.ድ. ።

ትምህርት ሚኒስቴር። **(1999)**። *የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ* ። አዲስ አበባ፣ በት.መ.ማ.ማ.ድ።

አልማዝ ኃይሉ። (1999)። "አራተኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ።" ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

AED/BESO II. (2006). "A Concise Manual for Developing and Impleme nting Continuous Assessment in Teacher Education.Institutions and Primary Schools of Ethiopia". Addis Ababa.(unpblished).

Aggrawal, J.C. (1994). *Essential of Educational Psychology.* New Delhi: Vikas Publishing Company.

Airisian, P. W. (1991). *Classroom Assessment.* New York: Mc Grow-Hill, Inc.

Bachman, L.F. (1990). *Fundamental Consideration in Language Testing.* Oxford, OUP.

Bekalu Atnafu. (2007). "An Evaluation of The Implementation of Continuous Assessment (CA): The Case of St. Mary's University College." *IER Flambeau*. Vol. 14, No. 2, PP. 31-42.

BESO II.(2003). "Continuous Assessment Implementation in First cycle Schools." Teachers Module 2 (Revised). Addis Ababa. (Unpublished).

Bogale Tessema. (1994). "Continuous Assessment: Its Validity, Reliability and Feasibility." M.A Thesis, AAU, (unpublished).

Brooks,V.(2002). *Assessment in Secondary Schools: Recording, Reporting and Accountability*. Buckingham: Open University Press.

Brown, G. et al. (1997). *Assessing Student Learning in Higher Education*. London: Routledge.

Brown, S. and Knight P. (1994). *Assessing Learners in Higher Education*. London: Routiedge.

Chappell, C. and D. Douglas. (1993). *A New Decade of Language Testing Research*. Alexandria, Virginia.

Curzon, L. (1990). *Teaching in Further Education: An Outline of Principles and Practices*. London: Cassel, Educational Ltd.

Dessalegn Chalchisa. (2004). "Continuous Assessment in Lower Cycle Primary School." *IER Flambeau*. Vol. 12, No.1, PP.1-8.

Dessalegn Chalchisa and Girma Lemma .(2009). *Measurement and Evaluation: Manual for Higher Education Institution*. Addis Ababa: AAUP.

Elington, H. and Earl, S. (1997). "Making Effective Use of Continuous Assessment and Portfolios." Retrieved from File://apu.qca.ac.uk /Ciced/ch.25,htm.56k.

Farrat, J.S. (1980). *Principles and Practice of Education*. Cambridge, CUP.

Gipps, Caroline. (1994). *Beyond Testing: Towards a Theory of Educational Assessment.* London: The Falmer Press.

Gronlund, N. E and Linn, R. L. (1990). *Measurement and Evaluation in Teaching.* New York. Macmillan Publishing. Inc.

Harmer, J. (2001). *The Practice of English Language Teaching (3rd ed).* Harlow: Pearson Educational Ltd.

Harris, M. (1997). "Self Assessment of Language Learning in Formal Settings." *ELT Journal.* Vol. 5, No. 1, PP. 12-20.

Heaton, J.B. (1990). *Class Room Testing.* London: Longman Group Limited.

Hughers, A. (1989). *Testing for Language Teacher.* Cambridge: CUP.

ICDR. (2004). "Continuous Assessment and its Application." A.A. MOE, (Unpublished).

Joy, D. P. et al. (2003). "Continuous Assessment: A Practical Guide for Teachers." USAID Bureau for Economic Growth, Agriculture and Trade Office Education. (Unpublished).

Lissitz, R.W. and Schafer, W.D.(2000). *Assessment in Educational Reform: Both Means and Ends.* Boston: Allyn and Bacon.

MOE. (1996). *Guidelines for Continuous Assessment (Grade-10 English).* Addis Ababa: Berhanena Selam Printing Enterprise.

Murphy, P. (1996). *Integrating Learning and Assessment Contemporary Issues in Teaching and Learning.* London: Open University Press.

Nitko, J.A. (2004). *Continuous Assessment in Teacher Education.* Washington, DC: Academy for Educational Development.

Norris, J, M. (2000). "Purposeful Language Assessment: Selecting The Right alternative Test." *English Teaching Form,* Vol. 38, No.1.

Pacheler, N. and Field, K. (2001). *Learning to Teach Modern Foreign Language in the Secondary School. (2nd* ed.). New York: Routledge Falmer.

Puhl, C.A. (1997). "Develop, Not Judge: Continuous Assessment in The ESL classroom." *English Teaching Forum* . Vol. 35, NO. 2, PP. 2-9

Richards, J.C. and Lockhart, C. (1994). *Reflective Teaching in Second Language Classroom*. Cambridge: CUP.

Shaaban, K. (2001). "Assessment of Young Learners." *English Teaching Forum*. Vol. 39, No.4, PP. 16-33.

Shepard, L.A. (2000). "The Role of Assessment in a Learning Culture." *Educational Research*, vol. 29, No. 7, PP. 4-14.

Tamene Olana. (2007)."Factors Affecting the Implementation of Contin uous Assessment in Selected Western Oromia Government School Teachers Training College." M.A. Thesis, AAU, (Unpublished).

Teshome Demissie. (2001). "Assessment of Pupils' Achievement in the Teaching of English: Training and Practice in Focus."*The Ethiopian Journal of Education*. Vol. xxi, No. I, PP. 25-48.

Ur, P. (1996). *A Course in Language Teaching*. Oxford: OUP.

Wilkin, L. (1991). *The Assessment of Performance and Competence: A Practical Guide for Trainees*.London: Stanley Thornes Publishers, Ltd.

www.equip23.net/.../cA-practical-Guide-Teachers.Pdf-Similar.

Zergahun Chafamo. (2007). "An Investigation into the Implementation of Continuous Assessment by EFL Instructors: A Case of Hosanna College of Teacher Education." M.A. Thesis, AAU (Unpublished).

# አባሪዎች

አባሪ አንድ

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቋንቋዎች ጥናት ተቋም
# በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል
# የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሀ ግብር

## የመምህራን ቃለመጠይቅ

የዚህ መጠይቅ አብይ አላማ በደብረብርሃን እና በወሎ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ትምህርት ክፍል የስነ-ልሳንና የበሳል ድርሰት ትምህርቶችን /Course/ የሚያስተምሩ መምህራንን የተከታታይ ምዘና አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ ከእነዚህ ትምህርቶች መምህራን መካከል እርስዎ አንዱ በመሆነዎ ለዚህ መጠይቅ ተመርጠዋል፡፡ ለቃለ መጠይቁም ፍቃደኛ በመሆነዎ በቅድሚያ ላቅ ያለ ምስጋናን አቀርባለሁ፡፡

የመምህራን አጠቃላይ መረጃ፡-

1. የሚያስተምሩበት ዩኒቨርሲቲ ስም፡- ____________________
2. ፆታ፡-____________________
3. የትምህርት ደረጃ፡-____________________
4. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ፡- ____________________
5. በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ አስተምረዋል፡- ____________
6. በሳምንት የሚያስተምሩት (ክሬዲት) ሰዓት ብዛት፡- ____________
7. የሚያስተምሩት ትምህርት /Course/ ስም ፡-____________
8. ከማስተማር በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ሌላ የሚሰሩት ስራ አለዎት?

   ________________________________________

9. ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን፡- ____________
10. ቃለ መጠይቁ የተጀመረበት ሰዓት፡- ________የተጠናቀቀበት ሰዓት______

1. በእርስዎ አመለካከት ተከታታይ ምዘና ማለት ምን ማለት ነው?
2. በተከታታይ ምዘና አተገባበር ዙሪያ ያገኙት ስልጠና አለ? ካለ ስልጠናውን እንዴት ሊያገኙ ቻሉ?
3. እርስዎ ለሚያስተምሩት ትምህርት/ Course/ ተከታታይ ምዘና የሚያገለግል ወይም አስፈላጊ ይመስለዎታል? ከመሰለዎት በሚያስተምሩት ትምህርት ላይ ይተገብሩታል?
4. የተከታታይ ምዘና እቅድ እና የኮረስ ቢ.ጋር አዘጋጅተው ይጠቀማሉ? የሚጠቀሙ ከሆነ በእቅድዎ እና በቢ.ጋርዎ ውስጥ የምዘና ተግባራትን አላማ፣ዘዴ እና ጊዜ በግልጽ ይዘረዝራሉ?
5. ከተከታታይ ምዘና ስልቶች ወይም ዘዴዎች መካከል የትኞቹን ይጠቀማሉ? እንደ አጠቃቀመዎ ደረጃ በቅደም ተከተል ይግለጹ? እነዚህንስ ተግባራት በሚሰጡበት ጊዜ ለተማሪዎች ግልጽ ማብራሪያ ይሰጣሉ?
6. ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው እንዲመዝኑ ወይም እንዲገመግሙ ያደርጋሉ? እርስ በርስ እንዲገማገሙና አስተያየት እንዲለዋወጡ ያደርጋሉ? በምን መልክ?
7. የትምህርቱን አላማ መሰረት ያደረጉ የመመዘኛ መስፈርቶች ያዘጋጃሉ? በማዘጋጀት ሄደቱስ ተማሪዎችን ያሳትፍሉ ? መስፈርቶቹንስ ለተማሪዎች ያሳውቃሉ?
8. ተከታታይ ምዘና ከተለምዷዊው ፈተና (ከማጠቃለያ ፈተና)በተሻለ ሁኔታ ለርስዎም ሆነ ለተማሪዎች ያስገኘው ጠቀሜታ አለ? ካለ ይዘርዝሩ?
9. ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ /Feed back/ ይሰጣሉ? የሚሰጡ ከሆነ መቼ እና ምን ላይ በማተኮር ይሰጣሉ?
10. ለተማሪዎች የምዘና ተግባራት ነጥብ /ማርክ/ ለመስጠት የሚጠቀሙበት ዘዴ አለዎት? ካለዎት ምን አይነት ዘዴዎችን ይጠቀማሉ?
11. በተከታታይ ምዘና ሂደት የሚገኘውን መረጃ ወይም የተማሪዎችን ውጤት ይተረጉማሉ? የሚተረጉሙ ከሆነ የትኛውን ዘዴ ይጠቀማሉ?
12. የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ውጤት እንደምዘናው አይነት መዝግበው ይይዛሉ? የሚገኘውንስ መረጃ ለምን ለምን አገልግሎት ያውሉታል?
13. በማስተምረው ትምህርት ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረጌ ተማሪዎች የታለሙ ክሂሎችን ማዳበር ችለዋል ብለው ያስባሉ? ያብራሩ?
14. ተከታታይ ምዘናን ለመተግበር ወይም በሚተገብሩበት ጊዜ የሚያጋጥመዎት ችግሮች አሉ? ካሉ ይግለጿቸው?
15. በመጨረሻ ተከታታይ ምዘና በትክክል እንዲተገበር ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

1. የሚያስተምሩበት ዩኒቨርሲቲ ስም :- ደብረብርሃን አባሪ ሁለት
2. ፆታ:- ወ
3. የትምህርት ደረጃ:- MA
4. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ:- TeAM
5. በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ አስተምረዋል:- ሁለት ዓመት
6. በሳምንት የሚያስተምሩት (ክሬዲት) ሰዓት ብዛት:- 12
7. የሚያስተምሩት ትምህርት /course/ ስም:- Amharic syntax
8. ከማስተማር በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ሌላ የሚሰሩት ስራ አለዎት? የትምህርት ክፍሉ ሊቀመንበር ነኝ
9. ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን:- 22-03-03
10. ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ሰዓት :- 8:00-8:50

ጥያቄ 1. በእርስዎ አመለካከት ተከታታይ ምዘና ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ: እ... በእኔ አመለካከት ተከታታይ ምዘና active learing ዘዴን ተጠቅመን ወይም ተከትለን የምጠቀምበት የምዘና ሂደት ነው:: ትምህርት እየተሰጠ በሂደት የሚሰጥ ነው:: አላማውም በማስተማር ሂደት የሚመጡ ችግሮችን ለማሻሻል ነው:: የተማሪውን የመማር ሂደት ለመቆጣጠር በተለያዩ ስልቶች የሚደገፉ ነው:: ለምሳሌ በምልከታ አማካኝነት መምህሩ ችግር ካለ ሊፈታ ይችላል:: የቃል ጥያቄ ሊጠይቅ ይችላል:: ተማሪዎችን interview ሊያደርግ ይችላል:: የክፍል ውስጥ Activity Asignment ሊሰጥ ይችላል:: የተለያዩ ቴክኒኮችን በመጠቀም ሊተገበር ይችላል::

ጥያቄ 2. በተከታታይ ምዘና አተገባበር ዙሪያ ያገኙት ስልጠና አለ? ካለ ስልጠናውን እንዴት ሊያገኙ ቻሉ?

መልስ: በተከታታይ ምዘና አተገባበር ዙሪያ ያገኘሁት ስልጠና አለ:: ይህም በዩኒቨርሲቲው በመጀመሪያ ለማስተማር ወደ ክፍል ከመግባታችን በፊት ለ5ቀን የሚሰጥ ስልጠና አለ:: ያንን ወስጃለሁ:: በተጨማሪም HDP ስልጠና ወስጃለሁ:: (የ5ቀኑ ስልጠና ስለ Active learing እና ስለ Continous Assessment ነው::

ጥያቄ 3. እርስዎ ለሚያስተምሩት ትምህርት/ Course/ ተከታታይ ምዘና የሚያገለግል ወይም አስፈላጊ ይመስለዎታል? ከመሰለዎት በሚያስተምሩት ትምህርት ላይ ይተገብሩታል? የሚተገብሩትስ በየትኛው የመማር-ማስተማር ደረጃ ነው?

መልስ፡ ለማስተምረው ትምህርት ተከታታይ ምዘና ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ:: በመሆኑም እተገብረዋለሁ:: የምተገብረውም በመማር ማስተማሩ ሂደት ነው:: ትምህርቱ በመካሄድ ላይ እያለ ነው:: መጀመሪያም መጨረሻም ላይ ሊሆን ይችላል ግን more የምተባበረው:: during ላይ ነው::

ጥያቄ 4. የተከታታይ ምዘና እቅድ እና የኮረስ ቢጋር አዘጋጅተው ይጠቀማሉ? የሚጠቀሙ ከሆነ በእቅድዎ እና በቢጋርዎ ውስጥ የምዘና ተግባራትን አላማ፣ዘዴ እና ጊዜ በግልጽ ይዘረዝራሉ?

መልስ፡ እ ... ተከታታይ ምዘና እቅድ እና የኮርስ ቢጋር አዘጋጅቼ እጠቀማለሁ:: በዚህም ውስጥ የምዘና ተግባራትን አላማ፣ ዘዴና ጊዜ በግልፅ እዘረዝራለሁ::

ጥያቄ፡5 ከተከታታይ ምዘና ስልቶች ወይም ዘዴዎች መካከል የትኞቹን ይጠቀማሉ? እንደ አጠቃቀመዎ ደረጃ በቅደም ተከተል ይግለጹ? እነዚህንስ ተግባራት በሚሰጡበት ጊዜ ለተማሪዎች ግልጽ ማብራሪያ ይሰጣሉ?

መልስ፡ የምጠቀምባቸው የምዘና ዘዴዎች እንደ ኮርሱ ባህሪ ይለያያል:: እ ... እኔ ለማስተምረው ትምህርት ዩኒቨርሲቲው ካወጣቸው ዘዴዎች በተጨማሪ የምጠቀማቸው ዘዴዎች አሉ:: የቃል ጥያቄ በክፍል ውስጥ እጠይቃለሁ፤ወጥተው እንዲሰሩ አደርጋለሁ ፤feed back እሰጣለሁ፤ ከተማሪዎች ሃሳብ እቀላለሁ፣ በዚህም ተማሪዎች ትምህርቱን ምን ያህል እንደተረዱት አውቅበታለሁ:: 3-4 ደቂቃ የሚወስድ የክፍል ስራ እሰጣለሁ:: ይህም የተማሪዎችን ግንዛቤ እለካበታለሁ:: የቤት ስራ ፣ Asignment ፣ term paper፣ የቡድንና የግል ስራዎች ከ10 ከ10% የሚያዙ ይሰጣሉ:: በየምዕራፉ መጨረሻ ከ5% ሦሥት ጊዜ የሚያዙ quiz አሉ:: mid exam አለ:: እንደገና ከ5% attendance እና class activity አለ:: እነዚህ ሁሉ የተከታታይ ምዘና አካል ናቸው:: ለዚህም ትምህርት የምጠቀምባቸው ናቸው:: ነገር ግን እንዳስፈላጊነቱ ሊቀያየሩ ይችላሉ ለምሳሌ እንደ ትምህርቱ አይነት ገለፃ ብቻ ሰጥተሽ የምወጪበት ጊዜ አለ::

ጥያቄ፡ 6 ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው እንዲመዝኑ ወይም እንዲገመግሙ ያደርጋሉ? እርስ በርስ እንዲገማገሙና አስተያየት እንዲለዋወጡ ያደርጋሉ? በምን መልክ?

መልስ፡ ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው እንዲገመግሙ አደርጋለሁ:: አንዳንዴ እጠቀምበታለሁ:: እንዲሁም ከትምህርቱ መጨረሻ ቦርድ ላይ በመፃፍ ወይም በቃል ዛሬ ምን ተረዳሁ? ምንስ አልተረዳሁም? ያልተረዳሁትስ ለምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን በመንገር ተማሪዎች እራሳቸውን እንዲፈትሹ አደርጋለሁ:: ግን በጣም አልፎ አልፎ ነው እንደዚህ የማደርገው:: peer assessment ይኖራል ግን ችግሮች ስላሉበት ማለትም እርስ በርስ የመጠቃቀም ነገር ስለሚኖር ብዙም አልጠቀምበትም ::

ጥያቄ፡ 7 የትምህርቱን አላማ መሰረት ያደረጉ የመመዘኛ መስፈርቶች ያዘጋጃሉ? በማዘጋጀት ሂደቱስ ተማሪዎችን ያሳትፋሉ ? መስፈርቶቹንስ ለተማሪዎች ያሳውቃሉ?

መልስ፡ እ ... መስፈርት አዘጋጃለሁ :: ግን ተማሪዎች እንዲያውቁትና በዝግጅቱ እንዲሳተፉ አላደርግም:: የታረመበትን ሁኔታ ከታረመ በኋላ አሳውቃለሁ:: ለምን ትክክል ለምን ኤክስ እንደሆኑ አሳውቃለሁ::

ጥያቄ፡ 8 ተከታታይ ምዘና ከተለምዷዊው ፈተና (ከማጠቃለያ ፈተና)በተሻለ ሁኔታ ለርስዎም ሆነ ለተማሪዎች ያስገኘው ጠቀሜታ አለ? ካለ ይዘርዝሩ?

መልስ፡ በተማርኩት ትምህርት መሰረት የተከታታይ ምዘና ተከታይ ወይም አቀንቃኝ ነኝ:: እናም ተለምዷዊውን ምዘና ስንመለከት በሴሚስተሩ መጨረሻ የሚሰጥ በመሆኑ ተማሪው ትምህርቱን በደንብ እየተማረ ይሁን አይሁን ፣ችግር ይኑርበት አይኑርበት የምናቀው ነገር የለም:: የትምህርት ዘዴው ፣ የፈተና ዘዴው ትክክል ይሁን አይሁን አናውቅም ምላሹን የምናውቀው መጨረሻ ላይ በመሆኑ ተማሪው ካለፈ አለፈ ነው:: ከወደቀም ወደቀ ነው:: እ .... ይኼኛው ተከታታይ ምዘና ግን ተማሪው በየጊዜው የሚገመገም ፣የሚታይ በመሆኑ የማስተማር ዘዴ ለማስተካከል ፣ የግምገማ ዘዴን ለማስተካከል ፣ አፋጣኝ የሆነ ምላሽ ለመስጠት እጅግ በጣም አስተዋፅኦ ያደርጋል:: ስለዚህ ከዚህ አንፃር የድሮ ጋር ሊመጣጠን አይችልም::

ጥያቄ፡ 9 ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ /Feed back/ ይሰጣሉ? የሚሰጡ ከሆነ መቼ እና ምን ላይ በማተኮር ይሰጣሉ?

መልስ፡ እ ... ምጋቤ ምላሽ እሰጣለሁ:: የምሰጠውም ክፍል ውስጥ ወዲያው ለቃል ጥያቄ ምላሽ እሰጣለሁ:: ወረቀታቸውን አርሜ በምመልስበት ጊዜ እሰጣለሁ:: ስሰጥም ስህተታቸውን ወይም ጉድለታቸውን በመናገር ላይ አተኩራለሁ::

ጥያቄ፡10 ለተማሪዎች የምዘና ተግባራት ነጥብ /ማርክ/ ለመስጠት የሚጠቀሙበት ዘዴ አለዎት? ካለዎት ምን አይነት ዘዴዎችን ይጠቀማሉ?

መልስ፡ እንደምዘናው አይነት የማረሚያ መስፈርቶች ይለያያሉ:: ምክንያቱም ምዘናዎቹ የሚዘጋጁት የትምህርቱን አላማ መሰረት በማድረግ ነው:: ስለዚህ መስፈርቱ ተቀምጦ በአንፃራወነት ይታረማል:: ይህም የፃፍ ጥያቄ በሚሆንበት ጊዜ ነው::

ጥያቄ፡11 በተከታታይ ምዘና ሂደት የሚገኘውን መረጃ ወይም የተማሪዎችን ውጤት ይተረጉማሉ? የሚተረጉሙ ከሆነ የትኛውን ዘዴ ይጠቀማሉ?

መልስ፡ Fixed Scale ነው:: ስለዚህ Criterian Referenced ነው የምጠቀመው:: ከዚህ ውጤት በመነሳት ዝቅተኛ ውጤት ላመጡ ተማሪዎች ድጋፍ ይደረጋል:: እ ... በተከታታይ ምዘና ለወደቀ ተማሪ ተጨማሪ ድጋፍ ይደረጋል:: ይህም tutor በመስጠት ለማጠቃለያ ፈተና የተሻለ ውጤት እንዲያመጣ ያደርጋል:: final የወደቁ ተማሪዎች tutor ወስደው በድጋሚ ይፈተናሉ:: ይህንን ነገር ዩኒቨርሲቲውም የሚያዘው ነው:: ትምህርት በተጀመረ በ45 ቀን ውስጥ ተማሪዎች ተለይተው ደከም ያሉ ድጋፍ ይደረግላቸዋል::

ጥያቄ ፡12 የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ውጤት እንደምዘናው አይነት መዝግበው ይይዛሉ? የሚገኘውንስ መረጃ ለምን ለምን አገልግሎት ያውሉታል?

መልስ ፡መዝግቤ እይዛለሁ:: ቀደም ብሎም እንደገለፅኩት ለተለያዩ አገልግሎቶች አውለዋለሁ::

ጥያቄ ፡13 በማስተምረው ትምህርት ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረጌ ተማሪዎች የታለሙ ክሂሎችን ማዳበር ችለዋል ብለው ያስባሉ? ያብራሩ?

መልስ፡ ተከታታይ ምዘና ተግባራዊ በማድረጌ ተማሪዎቼ የታለሙ ክሂሎችን ማዳበር ችለዋል ብዬ በሚገባ አስባለሁ:: ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች ከክላስ እንዳይቀሩም ይረዳል::

ጥያቄ፡14 ተከታታይ ምዘናን ለመተግበር ወይም በሚተገብሩበት ጊዜ የሚያጋጥመዎት ችግሮች አሉ? ካሉ ይግለጿቸው?

መልስ፡ እ... እስካሁን የጎላ ችግር አላጋጠመኝም :: በተማሪዎች በኩል ትንሽ የመሰልቸት ሁኔታ አለ:: ምክንያቱም ስራ ስለሚበዛ :: ተማሪዎች

የሚፈልጉት class attend አድርገው መጨረሻ ላይ በጫት ሃይል ያጠራቀሙትን አንብበው መፈተን ነው:: የሥራ ጫና በጣም አለብኝ ግን የዚህ ጉዳይ አቀንቃኝ በመሆኔ ነገሮችን አመቻችቼ ተከታታይ ምዘናን እተገብራለሁ:: ስለዚህ በኔ በኩል ብዙም ችግር የለብኝም::

ጥያቄ፡ 15 በመጨረሻ ተከታታይ ምዘና በትክክል እንዲተገበር ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

መልስ፡መመምህራን በየጊዜው ስልጠና ማግኘት አለባቸው:: በየጊዜው update ማድረግ አለብን :: Resource ያስፈልጋል:: Reference ያስፈልጋል:: ተማሪዎች ስለዚህ ጉዳይ ቀድመው ማወቅ አለባቸው::

ጠያቂ :- እጅግ በጣም አመሰግናለሁ

መልስ :- ምንም አይደል::

1. የሚያስተምሩበት ዩኒቨርሲቲ ስም :- ደብረብርሃን
2. ፆታ:- ሴ
3. የትምህርት ደረጃ:- MA
4. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ:- TeAM
5. በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ አስተምረዋል:- ጀማሪ
6. በሳምንት የሚያስተምሩት (ክሬዲት) ሰዓት ብዛት:- 9
7. የሚያስተምሩት ትምህርት /Course/ ስም:- Amharic Advanced Writing Skill
8. ከማስተማር በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ሌላ የሚሰሩት ስራ አለዎት? የለኝም
9. ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን:- 25-03-03
10. ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ሰዓት :- 5:00 - 5:40

ጥያቄ 1. በእርስዎ አመለካከት ተከታታይ ምዘና ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ፡ እ ... ተከታታይ ምዘና በእኔ አመለካከት አንድን ተማሪ በፈተና ከመፈተን ይልቅ quiz የቡድን ስራ ወዘተ የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅመን ተማሪዎችን የምንመዝንበት ዘዴ ነው:: ምክንያቱም ተማሪውን በፈተና ብቻ በምንፈተትንበት ጊዜ በዚያን ጊዜ የተመቻቸ ሁኔታ ላይ ላይሆን ይችላል:: በተጨማሪም ሊታመም ይችላል::

ጥያቄ 2. በተከታታይ ምዘና አተገባበር ዙሪያ ያገኙት ስልጠና አለ? ካለ ስልጠናውን እንዴት ሊያገኙ ቻሉ?

መልስ፡ በዚህ ዙሪያ ያገኘሁት ስልጠና በዩኒቨርሲቲው ገና ስገባ ለ5ቀን ያህል ስልጠና ተሰጥቶኛል:: እንዲሁም አሁን HDP እየተማርኩ ነው::

ጥያቄ 3. እርስዎ ለሚያስተምሩት ትምህርት/ Course/ ተከታታይ ምዘና የሚያገለግል ወይም አስፈላጊ ይመስለዎታል? ከመሰለዎት በሚያስተምሩት ትምህርት ላይ ይተገብሩታል? የሚተገብሩትስ በየትኛው የመማር-ማስተማር ደረጃ ነው?

መልስ፡ ለማስተምረው ትምህርት ተከታታይ ምዘና ያስፈልጋል ብዬ አምናለሁ:: በትምህርቱም ላይ እየተገበርኩት ነው:: የምተገብረውም በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ነው::

ጥያቄ 4. የተከታታይ ምዘና እቅድ እና የኮረስ ቢጋር አዘጋጅተው ይጠቀማሉ? የሚጠቀሙ ከሆነ በእቅድዎ እና በቢጋርዎ ውስጥ የምዘና ተግባራትን አላማ፣ዘዴ እና ጊዜ በግልጽ ይዘረዝራሉ?

መልስ፡ እቅድና ኮርስ ቢጋር አዘጋጅቼ እጠቀማለሁ:: በዚህም ውስጥ የምዘና ዘዴዎችን፣ አላማና ጊዜ አካትታለሁ:: ዩኒቨርሲቲው የራሱ የሆነ አካሄድ ወይም የምዘና ዘዴዎችንና እያንዳንዳቸው ከምን ያህል ፐርሰንት መያዝ እንዳለባቸው ያስቀመጠው ነገር አለ:: በዛመሰረት ነው የምንሰራው:: ከዛ መውጣት አይቻልም::

ጥያቄ፡5 ከተከታታይ ምዘና ስልቶች ወይም ዘዴዎች መካከል የትኞቹን ይጠቀማሉ? እንደ አጠቃቀመዎ ደረጃ በቅደም ተከተል ይግለጹ? እነዚህንስ ተግባራት በሚሰጡበት ጊዜ ለተማሪዎች ግልጽ ማብራሪያ ይሰጣሉ?

መልስ፡ የምጠቀምባቸው ዘዴዎች እ … quiz group work በአብዛኛው እጠቀማለሁ:: እነዚህንም ስራዎች ለተማሪዎች ስሰጥ በቅድሚያ ስለ አሰራራቸው እናገራለሁ::

ጥያቄ፡ 6 ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው እንዲመዝኑ ወይም እንዲገመግሙ ያደርጋሉ? እርስ በርስ እንዲገማገሙና አስተያየት እንዲለዋወጡ ያደርጋሉ? በምን መልክ?

መልስ፡ ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በራሳቸው እንዲያርሙ የማድረግ ነገር በብዙም አላዘወትርም አልጠቀምም:: የቢጤ ምዘናውን ግን እጠቀማለሁ::

ጥያቄ፡ 7 የትምህርቱን አላማ መሰረት ያደረገ የመመዘኛ መስፈርቶች ያዘጋጃሉ? በማዘጋጀት ሂደቱስ ተማሪዎችን ያሳትፍሉ ? መስፈርቶቹንስ ለተማሪዎች ያሳውቃሉ?

መልስ፡ መስፈርቶች እጠቀማለሁ ወይም አዘጋጃለሁ:: ለተማሪዎቹም ቀድሚ አሳውቃለሁ:: በማዘጋጀቱ ሂደት ግን ተማሪዎችን አላሳትፍም::

ጥያቄ፡ 8 ተከታታይ ምዘና ከተለምዷዊው ፈተና (ከማጠቃለያ ፈተና)በተሻለ ሁኔታ ለርስዎም ሆነ ለተማሪዎች ያስገኘው ጠቀሜታ አለ? ካለ ይዘርዝሩ?

መልስ፡ ብዙ ጠቀሜታ ያስገኛል:: ከተማሪዎች አዲስ ነገር አገኛለሁ:: ተማሪዎች confidence ይኖራቸዋል:: ሀሳባቸውን የመግለፅ፣ የመጠየቅ፣ ፍርሃትን የማስወገድ ለውጥ አምጥተዋል:: የማፍለቅ ችሎታቸው ዳብሯል::

ጥያቄ፡ 9 ለተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ /Feed back/ ይሰጣሉ? የሚሰጡ ከሆነ መቼ እና ምን ላይ በማተኮር ይሰጣሉ?

መልስ፡ እ ... ምጋቤ ምላሽ እሰጣለሁ:: የምሰጠውም በክፍል ውስጥ በቃል በፈተናና በሌሎች ስራዎች ላይ በፅሁፍ ነው:: የማተኩረው ትክክለኛውን መልስና ስህተታቸውን በመናገር ነው::

ጥያቄ፡10 ለተማሪዎች የምዘና ተግባራት ነጥብ /ማርክ/ ለመስጠት የሚጠቀሙበት ዘዴ አለዎት? ካለዎት ምን አይነት ዘዴዎችን ይጠቀማሉ?

መልስ፡ ይህ ነው የምለው ዘዴ የለኝም :: ግን ለተማሪዎች ስራ ነጥብ የምሰጠው ባዘጋጀሁት መስፈርት መሰረት ነው::

ጥያቄ፡11 በተከታታይ ምዘና ሂደት የሚገኘውን መረጃ ወይም የተማሪዎችን ውጤት ይተረጉማሉ? የሚተረጉሙ ከሆነ የትኛውን ዘዴ ይጠቀማሉ?

መልስ፡ አዎ በዩኒቨርሲቲው አሰራር መሰረት መከተል ያለብን criterian referenced ዘዴን ነው::

ጥያቄ፡ 12 የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ውጤት እንደምዘናው አይነት መዝግበው ይይዛሉ? የሚገኘውንስ መረጃ ለምን ለምን አገልግሎት ያውሉታል?

መልስ፡ መዝግቤ እይዛለሁ:: ውጤቱንም ተማሪዎችን ለይቶ ለማወቅ ፣የተለያዩ ችግሮችን ለማስተካከልና እገዛ ለመስጠት እጠቀምበታለሁ::

ጥያቄ ፡13 በማስተምረው ትምህርት ተከታታይ ምዘናን ተግባራዊ በማድረጌ ተማሪዎች የታለሙ ክሂሎችን ማዳበር ችለዋል ብለው ያስባሉ? ያብራሩ?

መልስ፡ እገምታለሁ :: አሁን ባለው ሁኔታ ትምህርቱን ባልጨረሰውም ታላሚ ክሂሎችን እያዳበሩ ነው ብዬ አስባለሁ::

ጥያቄ፡14 ተከታታይ ምዘናን ለመተግበር ወይም በሚተገብሩበት ጊዜ የሚያጋጥመዎት ችግሮች አሉ? ካሉ ይግለጿቸው?

መልስ፡ ያጋጠሙ ችግሮች የተማሪዎች ቁጥር መብዛት እና የማቴሪያል እጥረት ናቸው::

ጥያቄ፡ 15 በመጨረሻ ተከታታይ ምዘና በትክክል እንዲተገበር ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

መልስ፡ ተከታታይ ምዘና ተግባራዊ እንዲሆን የተማሪዎች ቁጥር ተመጣጣኝ መሆን አለበት:: መምህሩ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል:: ተማሪዎችን መከታተል ምጋቤ ምላሽ መስጠት ወዘተ ማድረግ አለበት:: ዝግጅትም ማድረግ አለበት::

ጠያቂ :- እጅግ በጣም አመሰግናለሁ

መልስ :- ምንም አይደል::

1. የሚያስተምሩበት ዩኒቨርሲቲ ስም :- ወሎ
2. ፆታ:- ወ
3. የትምህርት ደረጃ:- MA
4. የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ:- descriptive and theoretical lingustic
5. በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ አስተምረዋል:- ሁለት ዓመት
6. በሳምንት የሚያስተምሩት (ክሬዲት) ሰዓት ብዛት:- 12
7. የሚያስተምሩት ትምህርት /course/ ስም:- Amharic syntax
8. ከማስተማር በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ሌላ የሚሰሩት ስራ አለዎት? የለኝም
9. ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን:- 05- 04- 03
10. ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ሰዓት :- 5:10 - 5:40

ጥያቄ 1. በእርስዎ አመለካከት ተከታታይ ምዘና ማለት ምን ማለት ነው?

መልስ፡ ተከታታይ ምዘና ማለት በየቀኑ የምናስተምረውን ትምህርት ተማሪዎች በሂደት መረዳታቸውን እየገመገምን የምናስተምርበት መንገድ ነው። ትምህርቱን መረዳታቸውን ለማወቅ የሚረዳ ነው። ጥያቄ በመጠየቅ ወዘተ የሚረጋገጥበት ዘዴ ነው።

ጥያቄ 2. በተከታታይ ምዘና አተገባበር ዙሪያ ያገኙት ስልጠና አለ? ካለ ስልጠናውን እንዴት ሊያገኙ ቻሉ?

መልስ፡ HDP ሰልጥኛለሁ። ግን በዚህ ዙሪያ ያገኘሁት ነገር አጥጋቢ አይደለም። ምክንያቱም ትምህርቱ በጣም ፍጥነት ስለነበረው መሰረታዊ ነገር አላገኘሁበትም።

ጥያቄ 3. እርስዎ ለሚያስተምሩት ትምህርት/ Course/ ተከታታይ ምዘና የሚያገለግል ወይም አስፈላጊ ይመስለዎታል? ከመሰለዎት በሚያስተምሩት ትምህርት ላይ ይተገብሩታል? የሚተገብሩትስ በየትኛው የመማር-ማስተማር ደረጃ ነው?

መልስ፡ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ከጊዜ እጥረት ጋር ላይሄድ ይችላል። ኮርሶቹን ለመሸፈን ሲባል በመጠኑ ነው የምተገብረው። ስተገብርም በሂደቱ ላይ እተገብራለሁ። በጥያቄና መልስ በክልፍ ስራ ወዘተ...

